# ጸሎትህ ኃይልን የተላበሰ ይሁን

ከዲ ኩሲ

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. ጸሎት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የሚካሄድ ተግባቦት ነው።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ይህ ትምህርት ወጣቶች ከእግዚአብሔር ጋር ለሚያደርጉት ተግባቦት የበለጠ የፈጠራ ጥበብ እንዲያዳብሩና በጸሎት ሕይወታቸው እንዲያድጉ ያግዛቸዋል።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. በብዙ ክርስቲያን ቡድኖች መካከል ጸሎት ብዙ ትኩረት ቢደረግበትም እምብዛም ተግባራዊ ሲሆን አይታይም። ስለ ጸሎት ብዙ ብንናገርም፣ ብዙ አንጸልይም። ለብዙ ሰዎች ጸሎት ሥርዓት ወይም ሊፈጸም የሚገባው ግዴታ ነው። ክርስቶስ ከሥርዓቶች ወጥተን ከርሱ ጋር ወደሚደረግ የንግግር ግንኙነት እንድንገባ ይፈልጋል።
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. ለመክፈቻ እንቅስቃሴ የሚያስፈልጉ ሙዞች።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)

1. የሙዝ ውድድር። ስለ ጨዋታው ማብራሪያ ከመስጠትህ በፊት እያንዳንዱ ቡድን የሚወክለው አንድ ተጫዋች እንዲመርጥ አድርግ። የተመረጡት ተጫዋቾች ሁሉ ወደተቀሩት ወጣቶች ፊታቸውን አዞረው ከመድረኩ ላይ ከጠረጴዛ ኋላ እንዲቆሙ አድርግ። ከእያንዳንዱ ተጫዋች ፊት ሙዝ አስቀምጥ። ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ እጆቻቸውን ወይም ክንዶቻቸውን ሳይጠቀሙ ሙዞቻቸውን በፍጥነት ልጠው መብላት አለባቸው። ሙዞቹ ተበልተው ሲያልቁ አሸናፊው ማን እንደሆነ ይገለጻል።
2. መሪውን መገመት። ስለ ጨዋታው ማብራሪያ ካደረግህ በኋላ ፈቃደኛ የሆነ አንድ ሰው ወደ ውጭ እንዲወጣ አድርግ። ከዚያ በኋላ የተቀሩት ወጣቶች ክብ ሠርተው በመቆም አንድ መሪ ይመርጣሉ። ቡድኑ መሪው የሚያደርገውን ነገር ያደርጋል። ወደ ውጭ የወጣው ልጅ ተመልሶ ከክቡ ውስጥ በመቆምና ወጣቶቹ የሚያከናውኑትን ተግባር በመመልከት መሪው ማን እንደሆነ ይገምታል። ሦስት ዕድሎች ይሰጡትና መሪውን ካወቀ መሪ የነበረው ልጅ ወደ ውጭ እንዲወጣ ይደረጋል። ከሦስት ሙከራዎች በኋላ መሪውን ካላወቀ፣ ወደ ውጭ የሚወጣ ሌላ ሰው ይመርጣል።



3. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው።)

ነገሩ የተከሰተው ከገና ቀደም ብሎ በዋለው ረቡዕ ዕለት ነበር። ሊሳ በማዕድ ቤት ውስጥ ለበዓሉ አንዳንድ ምግቦችን በመሥራት ላይ ነበረች። ቤቱ በግሩም የምግብ መዓዛ ታውዷል። የሊሳ ባለቤት የሆነው ኤርምያስ ከቤት ውጭ መኪናውን እየጠጋገነ ነበር። የምግቡ መዓዛ ወደ አፍንጫው ዘልቆ ስላወደው ብስኩት ለመብላት ፈልጎ ወደ ማዕድ ቤቱ ሄደ።

ማዕድ ቤቱ ውስጥ እንደገባም፣ «የማግዝሽ ነገር ይኖራል?» ሲል ጠየቃት። ሊሳ የሚያግዛት ነገር እንደሌለ እንደምትናገር ያውቃል። የጠየቃትም ይህንኑ መልስ እንደምትሰጠው ስለሚያውቅ ነበር። ኤርሚ በክፍሉ ውስጥ ወዲያ ወዲህ እያለ ድስቶቹን ሁሉ ተመለከተ። በመጨረሻም ወደ ምድጃው በመሄድ እየበሰለ ያለውን የአሳማ ሥጋ እጮልቆ ተመለከተ። ምግቡ ጣፋጭ ይመስላል። ከዚያ በላይ ግን ሁልጊዜም በየዓመቱ በዚህ ወቅት ወደ አእምሮው የሚዘልቀውን ጥያቄ አስታወሰው። «ሊሳ፣ ከዚህ በፊት ይኼን ነገር ጠይቄሽ ባላውቅም፣ ሁልጊዜም የአሳማውን ሥጋ ጫፍች ለምን ቆርጠሽ እንደምትጥይ አይገባኝም» ሲል ጠየቃት።

«አህ፣ ኤርሚ፣ የአሳማን ሥጋ ከማብሰል አስቀድሞ ጫፎቹን ቆርጦ መጣል እንደሚያስፈልግ ታውቅ የለ?» አለች።

«ለምን?»

«ስ... ለምን ቆርጬ እንደምጥለው አላውቅም። እናቴ ሁልጊዜም ይህንኑ ታደርጋለች። እኔ ግን ጠይቄያት አላውቅም። ይህ ዝም ብለህ የምታደርገው ነገር ነው። ለማወቅ ከፈለግህ ለምን እናቴን አትጠይቃትም። ከሦስት ሰዓት በኋላ እዚህ ትደርሳለች።»

በዚያን መሸት የሊሳ እናት ወደ ሁለት ሰዓት ገደማ መጡ። ለበዓሉ ብዙ ምግብ ይዘው ነበር የመጡት። ኤርሚም ፈጠን ብሎ ጥያቄውን አነሣ።

«እማማ፣ ሊሳ ሁልጊዜም የአሳማ ሥጋ ከማብሰሏ በፊት ጫፎቹን ቆርጣ ትጥላለች። ለምን እንደዚያ እንደምታደርግ ስጠይቃት ምክንያቱን አታውቅም። እርስዎም ይህንኑ ስለሚያደርጉ መልሱን እንደሚነግሩኝ ገልጻልኛለች» ሲል ጠየቃቸው።

የሊሳ እናት ትንሽ ግራ ተጋብተው ቆዩና፣ «የአሳማን ሥጋ ከማብሰል አስቀድሞ ጫፎቹን ቆርጦ መጣል እንደሚያስፈልግ ሁሉም ሰው ያውቃል» ሲሉ መለሱለት።

«ግን ለምን?» ኤርሚ።

«እኔ እንጃ። ከእናቴ እያየሁ ነበር ይህንን የማደርገው። ነገ በአራት ሰዓት እዚህ ስለምትሆን ለምን እሷን አትጠይቃትም?»

ኤርሚ የሥጋው ጫፎች ለምን እንደሚቆረጡ ለማወቅ ስለጓጓ የባለቤቱን አያት መምጣት በናፍቆት ሲጠባበቅ ቆየ።

በቀጣዩ ዕለት አምስት ሰዓት ላይ የሊሳ አያት ደረሱ:: ብዙ ዕቃ ባይዙም፣ ብዙ ምግብ ይዘው ነበር የመጡት:: ኤርሚ ከመጓጓቱ የተነሣ ገና ሰላምታ ተለዋውጠው እንዳበቁ፣ ለሊሳ አያት ጥያቄውን አቀረበላቸው::

የሊሳ አያትም ፈጠን ብለው፣ «ነገሩ ቀላል ነው:: ድስቴ ትንሽ ስለነበረች ሥጋውን ለመቀነስ ስል ነበር ጫፎቹን እየቆረጥሁ የምጥለው» ሲሉ መለሱ::

ሊሳና እናቷ ግን ያለ ምንም ምክንያት ነበር ለዓመታት የአሳም ሥጋን ጫፎች እየቆረጡ ሲጥሉ የነበሩት:: ከበስተጀርባው የነበረውን ፍች ሳያውቁ ሥርዓቱን ተከትለው ሲጓዙ ኖረዋል::

ሁላችንም እንደዚያ ዓይነት ነገሮችን እናደርጋለን:: ከብዙዎቹ ሥርዓቶቻችን በስተጀርባ ያሉትን ፍችዎች ረስተናል:: አንዳንድ ሥርዓቶችን (ለምሳሌ፣ የአሳማ ሥጋ ጫፎችን መቁረጥ) ማስወገድ አለብን:: አንዳንድ ሥርዓቶችን በተመለከተ ደግሞ ፍቻቸውን ማወቅ አለብን::

እስኪ ስለ አንዳንድ ሥርዓቶች እንነጋገርና መጀመሪያ የነበራቸውን ፍች ታውቁ እንደሆነ እንመልከት::

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (*መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙ*ባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ::)

1. የመጀመሪያው የሰንበት ቀን ቅዳሜ ሆና ሳለ አምልኮአችንን እሑድ ቀን የምናካሂደው ለምንድነው? *(መልስ: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት የተነሣው እሑድ ቀን በመሆኑ፣ ይህንኑ ክስተት ለማክበር ስንል እሑድ ቀና እግዚአብሔርን ተሰባስበን እናመልከዋለን::)*
2. የሰንበት ትምህርት ቤት የተመሠረተበት የመጀመሪያው ምክንያት ምን ነበር? *(መልስ: የልጆች የሥራ ሕግ ከመደንገጉ በፊት፣ ልጆች ሳምንቱን ሁሉ በፋብሪካ ውስጥ ስለሚሠሩ ትምህርት የማግኘት ዕድል አልነበራቸውም:: በዚህም ጊዜ ቤተክርስቲያን ልጆችን የማሰልጠንን ኃላፊነት ወሰደች:: በመሆኑም፣ ዛሬ የሰንበት ትምህርት የሚካሄድበት ምክንያት የሰንበት ትምህርት ከተጀመረበት ምክንያት ጋር አንድ ዓይነት እንዳልሆነ መመልከት ይቻላል::)*
3. የገናን በዓል የምናከብረው ለምንድነው?
4. የወጣቶችን ስብሰባዎች የምናካሂደው ለምንድነው?
5. ምግብ ጸልየን የምንበላው ለምንድነው?
6. ጸሎት የምንጸልየው ለምንድነው?
7. ጸሎት ምንድነው?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው::)



1. ማቴዎስ 6:5-8: *«ስትጸልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ:: ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኩራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና፣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋቸውን ተቀብለዋል:: አንተ ግን ስትጸልይ ወደ እልፍኝህ ግባ:: መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ:: በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል:: አሕዛብም በመናገራቸው ብዛት እንዲሰሙ ይመስላቸዋልና ስትጸልዩ እንደ እነርሱ በከንቱ አትድገሙ:: ስለዚህ አትምሰሉአቸው:: ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና::»* ከተራራው ስብከት የተወሰደው ይህ ምንባብ የጸሎት ሕይወታችንን ቀረብ ብለን እንድንመለከት ይጠይቀናል:: እስካሁን በምንጸልይበት መንገድ የምንጸልየው ለምንድነው? ባጠቃላይ ጸሎትን የምንጸልየውስ ለምንድነው? ክርስቶስ በተናገረው ቃል በዘመኑ የነበሩትን ሰዎች አስደንቋቸዋል:: እኛም በግልጽ ብንሰማው እውነትን ከእርሱ ልናገኝ እንችላለን::

አይሁዶች ጸሎት በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ያምኑ ነበር:: ከዚህም የተነሣ ብዙ ልማዶች ሊጎለብቱ ቻሉ:: 1) እያንዳንዱ አይሁዳዊ ሽማ የተባለውን የብሉይ ኪዳን ክፍል (ዘዳግም 6:4-9፣ 11:13-21፣ ዘኁልቁ 15:37-41) ጠዋት ከሦስት ሰዓት በፊትና ማታ ከሦስት ሰዓት በፊት መድገም ነበረበት:: 2) አንድን ጸሎት በቀን ሦስት ጊዜ መደጋገም ነበረባቸው:: 3) ለሁሉም ሁኔታ የተዘጋጁ ጸሎቶች ነበሯቸው:: 4) በጣም ሃይማኖተኛ ለሆኑት አይሁዶች የተወሰኑ የጸሎት ጊዜያት ተመድበው ነበር:: የትም ቦታ ቢሆን አጥባቂ ሃይማኖተኛ የሆነ አይሁዳዊ እነዚህ የተወሰኑት ሰዓቶች በሚደርሱበት ጊዜ ሲሠራ የቆየውን ነገር አቋርጦ መጸለይ ይኖርበታል:: አንዳንድ አይሁዶች ትጉህ ሃይማኖተኛነታቸውን ለሰዎች ለማሳየት ሲሉ እነዚህን ሰዓታት ሕዝብ በሚበዛባቸው ስፍራዎች በመገኘት ይጸልዩ ነበር:: 5) ብዙ መጸለይ የትልቅ «መንፈሳዊነት» ምልክት ተደርጎ ይወሰድ ነበር:: 6) ድግግሞሽ በጣም የተለመደ ነገር ነበር::

ትርጉም የሌለው ሥርዓት ወደሚሆንበት ደረጃ ላይ እስካልደረሰ ድረስ በተወሰነ መንገድ መጸለዩ ክፋት የለውም::

2. ማቴዎስ 6:9-15: *«እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ፣ በሰማያት የምትኖር፣ አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ፣ መንግሥትህ ትምጣ፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን:: የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን:: እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን:: ከክፉ አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን:: መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ አሜን:: ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፣*

የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና። ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ፣ አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።» ክርስቶስ ይህንን አባታችን ሆይ በመባል የሚታወቀውን ጸሎት የሰጠን ጸሎታችን ምን መምሰል እንዳለበት ለማስተማር እንደሚረዳ ምሳሌ አድርጎ ነው።

1. ይህ ጸሎት ረዥምና የቃላት ድግግሞሽ የበዛበት ሳይሆን ቀላል ነው።
2. ወደ እግዚአብሔር በፍቅር በመቅረብ፣ «አባታችን ሆይ» ይላል።
3. ወደ እግዚአብሔር በአክብሮት በመቅረብ፣ «ስምህ ይቀደስ» ይላል።
4. የእግዚአብሔር መጠቀሚያ ለመሆን መፍቀዱን ይናገራል። «ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን»
5. ያለፈውን፣ ያሁኑንና የወደፊቱን ለእግዚአብሔር አሳልፎ ይሰጣል። ያለፈው፣ «በደላችንን ይቅር በለን»፣ ያሁን፣ «የዕለት... ስጠን»፣ የወደፊት፣ «... አታግባን»። በዚህ ቀላል ጸሎት፣ ክርስቶስ ቀለል ያለ ጸሎት እንድንጸልይ አስተምሮናል። ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነው። ሥርዓት በእውነተኛ ሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ አትፍቀድለት። ከእግዚአብሔር ጋር የምትነጋገርባቸውን የተለያዩ መንገዶች ማግኘት ጀምር።

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች

1. ወጣቶች የሆነ ሥርዓታዊ ጸሎት (የምግብ ጸሎት፣ የመኝታ ጸሎት፣ የጠዋት ጸሎት [ቀኝ አውለኝ]፣ የመባ ጸሎት፣ የወጣቶች ስብሰባ የመክፈቻ ጸሎት እንዲጸልዩ ጠይቃቸው።
2. ለመጸለይ የሚመችህ ስፍራ የትኛው ነው?
3. ለመጸለይ የሚመችህ ጊዜ የትኛው ነው?
4. ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት የምንገናኝባቸው አዳዲስ መንገዶች የትኞቹ ናቸው? (ለምሳሌ፣ ንግግር፣ ማሰብ፣ አሳቦቻችንን በጽሑፍ ለእግዚአብሔር ማቅረብ፣ በመዝሙሮች አማካኝነት መጸለይ።)
5. እግዚአብሔር ከኛ ጋር ሊግባባ (ሊገናኝ) የሚችለው እንዴት ነው? (በስብከት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፣ በአሳቦችና በመዝሙሮች፣ በጽሞና መጻሕፍት።)
6. ከሰው ጋር መጸለይ ጥቅም አለው? (ማቴዎስ 18:19-20)

ሰ. መዝጊያ

ከእግዚብሔር ጋር በጸሎት ለመገናኘት ለሚያስችሉ አዳዲስ መንገዶች ክፍት በሆንን መጠን፣ ቀኑን ሁሉ ልንጸልይ እንደምንችል ይበልጥ እየተገነዘብን እንሄዳለን። እግዚአብሔር መላ ሕይወታችንን ለርሱ አሳልፈን እንድንሰጥ ይፈልጋል። ዕቅዶቻችንንና የትምህርት



ቤት ሥራዎቻችንን ለርሱ ልናካፍል እንችላለን። በመዝሙራችን፣ በገንዘባችንና በቃላችን አማካኝነት ለርሱ ያለንን ፍቅር ልንነግረው እንችላለን። በብዙ የተለያዩ መንገዶች ልንጸልይ እንችላለን። ነገር ግን ዋናው ነገር ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት መሆኑን ከዘነጋን ይህ ሁሉ ትርጉሙን ሊያጣ ይችላል።

ይህንን ክፍለጊዜ በጸሎት ፈጽም። 1) ወጣቶቹ የጸሎት ጥያቄዎች እንዲሏቸው ጠይቅ። በጥቁር ሰሌዳ ወይም በፖስተር ላይ የጸሎት ጥያቄዎቻቸውን ዘርዝር። 2) ከሦስት እስከ አምስት አባላት ባሏቸው ቡድኖች ከፋፍላቸው። 3) እነዚህን መመሪያዎች ስጣቸው: ሀ) ሁሉም ሰው በጸሎት ይሳተፋል። ለ) መጀመሪያ እንዲጸልይ የሚመረጥ ሰው አይኖርም። ሐ) ድምጹን ከፍ አድርጎ መጀመሪያ የሚጸልይ ሰው ስለ አንድ የጸሎት ጥያቄ ብቻ ይጸልያል። (ሌሎቹ ድምጻቸውን ሳያሰሙ ይጸልያሉ።) መ) ረዥም ጸሎት መጸለይ አያስፈልግም። አንድ ሰው ከሁለት ዓረፍተነገሮች በላይ መጸለይ የለበትም። ሠ) ከባባድ ቃላት መጠቀም አያስፈልግም። ረ) አሳብህንና ስሜትህን በቀጥታ ግለጽ እንጂ ግልጽ ያልሆኑትን ጸሎቶች አታድርግ።

ከአምስት ደቂቃዎች ያህል ጊዜ በኋላ፣ እግዚአብሔርን ለህልውናው በማመስገን መሪው በቀላልና አጭር ጸሎት ያጠቃልል።

## በጸሎት ውስጥ

# ኃጢአት መሆኑን እንዴት አውቃለሁ?

አለን ስኮት

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚጥስ ተግባር ስንፈጽም ወይም የእግዚአብሔርን ምሪት ሳለማግኘት ስንመርጥ በእግዚአብሔር ላይ እናምፃለን።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች ኃጢአትንና ለኃጢአት መፈተንን ለይተው እንዲያውቁና ድልነሺ ሕይወት እንዲኖሩ ለማገዝ።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ክርስቲያን ወጣቶች ከክርስቲያናዊ ሕይወታቸው ብዙ ሊጠብቁ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ ኃጢአትን ለኃጢአት ከመፈተን ለይተው ለማወቅ ስለሚቸገሩ በቀላሉ ይሸነፋሉ። ባመዛኙ፣ «ይኼ ነገር ኃጢአት ነው?» ሲሉ ይጠይቃሉ። መልስ ከመስጠታችን በፊት፣ «መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚያ ጉዳይ ምን ይላል?» እና «የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመጣስ ትፈልጋለህን?» ብለን ልንጠይቃቸው ይገባል። ወጣቶች በፈተናዎች፣ ሆን ተብሎ በሚፈጸም ኃጢአትና ሳይታሰብ በሚፈጸም አለመታዘዝ መካከል ያሉትን ልዩነቶች ማወቅ አለባቸው።
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. በቅርብ ጊዜ የታተሙ ጋዜጦች።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)

1. የጋዜጣ ላይ አሰሳ። ወጣቶቹን በቡድን ከፋፍለህ ተመሳሳይ ጋዜጦችን ስጣቸው። ክፍለጊዜው ከመጀመሩ በፊት፣ በጋዜጣው ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ዘርዝር። ዝርዝሩ የሰዎችን ስሞች፣ ፎቶች፣ መረጃዎች፣ ማስታወቂያዎች፣ ወዘተ. ሊያካትት ይችላል። ዝርዝሩን ለሁሉም ቡድኖች ስጣቸው። የተዘረዘሩትን ነገሮች በቀዳሚነት ከጋዜጣው ላይ ያገኘ ቡድን አሸናፊ ይሆናል።
2. የጋዜጣ ውድድር። ወጣቶቹ ከመነሻ መስመር ኋላ በሁለት ሰልፎች እንዲቆሙ አድርግ። ከክፍሉ ጥግ የግብ መስመር አብጅ። እያንዳንዱ የቡድን አባል (አንድ ጊዜ አንድ ሰው) በጋዜጦቹ ላይ እየተረማመደ ወደ ግቡ ይሄዳል። ለእያንዳንዱ ቡድን ሁለት ገጽ ጋዜጦች ይሰጡታል። አንደኛውን ገጽ ሲረግጡ ሁለተኛውን ከፊታቸው ትዘረጋላቸዋለህ። እግራቸው ከጋዜጣው አልፎ መሬት ከረገጠ ከእንደገና ይጀምራሉ። ከግቡ መስመር ላይ ከደረሱ፣ ሁለቱንም ጋዜጦች ይዘው በመመለስ ለተረኛው የቡድናቸው አባል ይሰጡታል። በቀዳሚነት ሁሉም አባላቱ ከግቡ መስመር የደረሱለት ቡድን አሸናፊ ይሆናል።
3. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው።)

ከዚህ በፊት እነዚህን ጥያቄዎች ጠይቀህ ታውቃለህ? አንድ ነገር ኃጢአት መሆኑን እንዴት ታውቃለህ? መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የማይጠቅሰው ነገር ቢሆንስ? ኃጢአት መሆኑን ሳላውቅ ባደርገውስ? ኃጢአት ከፈጸምሁ በኋላም ክርስቲያንነቴ ይቀጥላል? እነዚህ በየቀኑ የሚያጋጥሟችሁ ጠቃሚ ጥያቄዎች ናቸው። ሁልጊዜም ምክር ለመጠየቅ ጊዜ አይኖራችሁም። ለዚህም ነው አሁን ጊዜ ወስደን ወደፊት ውሳኔዎችን ለመስጠት የሚያስችሉንን መምሪያዎች መመልከት ያለብን። በሚከተለው ታሪክ ውስጥ እያንዳንዱ ሰው የምንማርባቸውን ምርጫዎች ያካሂዳል።

ሚስዝ ሚኬይ ዳንኤል ያመለጠውን ትምህርት እንዲያሟላ ተማሪዎቹ ከተለቀቁ በኋላ እዚያው አቆዩት። ውጭ ጠብ በተነሣ ጊዜ በታሪክ ክፍል ውስጥ የነበሩት ዳንኤልና ሚስዝ ሚኬይ ብቻ ነበሩ። ሚስዝ ሚኬይ ዳንኤል ሥራውን እንዲቀጥል ከነገሩት በኋላ ሌሎች መምህራንን ለመርዳት ወደ ውጭ ወጡ። በዚህ ጊዜ ዳንኤል ወደ አስተማሪዋ ጠረጴዛ አምርቶ በመጭው ዓርብ የሚወስዱትን ፈተና አየ። ከፈተናው አጠገብ የጥያቄቹ መልሶች የተጻፉበት ወረቀት ነበር። በፍጥነት መልሶቹን ከገለበጠ በኋላ፣ አስተማሪው ከመመለሳቸው በፊት ከዴስኩ ላይ ቁጭ ብሎ ጠበቃቸው።

በቀጣዩ ቀን ዕረፍት ሰዓት ላይ ያጋጠመውን ሁኔታ በመግለጽ፣ መልሱን ለአራት ጓደኞቹ ለመሸጥ እንደሚፈልግ ተናገረ። ዳንኤል፣ መሐመድና አልፎ ክርስቲያኖች አልነበሩም። ነገር ግን ሮጀርና ናትናኤል ክርስቲያኖች ነበሩ። ሁሉም በተመሳሳይ የቤተክርስቲያን የወጣቶች ቡድን ውስጥ ነበሩ።

መሐመድ በእግር ኳስ ቡድኑ ውስጥ ለመሰንበት ጥሩ ውጤት ማምጣት ስለነበረበት የመልሱን ቅጂ ገዛ። አልፎ መልሶቹን ባይገዛም በፈተናው ቀን ከመሐመድ ጎን ተቀምጦ እሱ ሳያውቅ እየኮረጀ ሠራ። ሮጀር መልሱን ካለመግዛቱም በላይ ከሌላ ሰውም ለመኮረጅ አልሞከረም። ዳንኤልንና መሐመድንም ለማጋለጥ አልፈለገም። ናትናኤል ምን ማድረግ እንዳለበት ስላላወቀ በፈተናው ዕለት አሞኛል ብሎ ከቤት ዋለ። ሚስዝ ሚኬይ ሌላ ፈተና እንደሚሰጡትና መልሱን የመግዛት እድል እንደማይኖረው ያውቅ ነበር።

መ. የመወያያ ጥያቄዎች(መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

1. ከአምስቱ ልጆች ከሁሉም የተሻለ እርምጃ የወሰደው ማነው? ከሁሉም የከፋ እርምጃ የወሰደውስ? በቅደምተከተል ዘርዝራቸው።
2. ሮጀርና ናትናኤል ሳለመከረጅ ቢወስኑም ለመምህሯ አለመናገራቸው ትክክል ነው? ለምን?
3. ይህ መልሱን በጥንቃቄ ባለማስቀመጣቸው ምክንያት የተከሰተ የመምህሯ ብቻ ጥፋት ይመስልሃል? ለምን?
4. በዚያን ዕለት በዕረፍት ሰዓት ከዳንኤል ጋር አብረህ ብትሆን ኖሮ ምን ታደርግ ነበር? ለምን?
5. በታሪኩ ውስጥ ኃጢአት ለመሥራት የተፈተኑትን ልጆች ስም ዘርዝር። ያጋጠማቸው ፈተና ምን እንደነበረ ግለጽ።
6. ኃጢአት የፈጸመው ማን ይመስልሃል? ለነዚህ ልጆች ፈተና ወደ ኃጢአትነት የተለወጠው መቼ ይመስልሃል?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)

ያዕቆብ 1:13-15። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በፈተና ወይም በምኞት የሚጀምረውን ሂደት በግልጽ ያሳያል። ተገቢ ያልሆነ ምኞት ስናስተናግድና ሽሽተን ሳናመልጥ ስንቀር፣ በቀላሉ ኃጢአትን እንፈጽማለን። ይህም ወደ መንፈሳዊ ሞት ይመራናል። መንፈሳዊ ሞት ደግሞ ከእግዚአብሔር ይለየናል። በዚህ ጊዜ ተስፋችን የሚሆነው በያዕቆብ 4:7-8፣ 1ኛ ዮሐንስ 1:9 እና 2:1-2 የተሰጠው ቃል ይሆናል። (አንድ ሰው እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንዲያነብላችሁ ጠይቅ።) ይህ የፈተና፣ የኃጢአትና የንስሐ ሁኔታ በዳዊትና ቤርሳቤህ ታሪክም ሊብራራ ይችላል (2ኛ ሳሙኤል 11 እና 12)። ዳዊት በተፈተነ ጊዜ ከፈተናው በመሸሽ ፈንታ ወደፊት ገፋበት። በ2ኛ ሳሙኤል 12:13 ላይ የሚገኘው የዳዊት ኑዛዜ ለታሪኩ በጣም ጠቃሚ ነው። (ይህን ጥቅስ አንብብ።)

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች

1. ኃጢአትና ፈተና የሚለያዩት እንዴት ነው?
2. አንድ የምናደርገው ነገር ኃጢአት እንደሆነና እስከ ዛሬ ግን ሳንገነዘብ እንደቆየን ስንረዳ፣ ምን ልናደርግ ይገባል?
3. እግዚአብሔር የሚያጋጥሙንን ፈተናዎች ሁሉ ዝርዝሮ ያላስቀመጠው ለምን ይመስልሃል? (እንደ ፈተና መከረጅና የሚኮረጅን ሰው ማጋለጥ ዓይነት።)
4. ከአንዳንድ ፈተናዎቻችን የምናመልጠው እንዴት ነው? (ጊዜ ካላችሁ፣ ወጣቶቹ የሚጋፈጧቸውን ፈተናዎች ወይም ሁኔታዎች እንዲዘረዝሩ አድርግ። መልሶቻቸውን በዝርዝር ጻፍና እነዚህ ፈተናዎች ወደ ኃጢአት እንዳይወስዷቸው ምን ሊያደርጉ እንደሚገባቸው ተወያዩ። ለምሳሌ፣ ዳንኤል መልሶቹን ለናትናኤል ለመሸጥ በፈለገ ጊዜ፣ ናትናኤል ለዳንኤል



መሳሳቱንና ለአስተማሪዋ የፈተናው መልስ በተማሪዎች እጅ መግባቱን እንደሚገልጽላቸው ሊነግረው ይችል ነበር።

ሰ. መዝጊያ

እግዚአብሔር ኃጢአት ስንሠራ ለመያዝና ለመኮነን በመጠባበቅ ላይ ያለ አምላክ አይደለም። እርሱ የኃጢአት ወጥመዶችን እንድንገነዘብና ከኃጢአት እስራት ነጻ ሆነን እንድንኖር ይፈልጋል። ከኃጢአት ለመራቅ የሚከተሉት ጠቃሚ መርሆች ናቸው።

1. ወደ ኃጢአት የሚመራውን ፈተና ለይተህ እወቅ። ለአንተ ከባድ የሆነው ፈተና ለሌላ ሰው ያን ያህል ላይሆን ይችላል። የተወሰኑ ፈተናዎችን ለማሸነፍ ምሥጢሩ ይህ የተወሰነ ፈተና ለአንተ ከባድ የመሆኑን እውነታ ለራስህና ለእግዚአብሔር ማሳወቅና ፈተናውን ለማሸነፍ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተለየ እገዛ እንደምትፈልግ መግለጽ ነው።
2. የሕይወትን ፈተና በምትጋፈጥበት ጊዜ ሁሉ የእግዚአብሔርን መንገድ ለመከተል ቁረጥ። ሙሉ ለሙሉ ራስህን ለእግዚአብሔር አሳልፈህ ስጥተሃል ማለት ከቶውንም አትፈተንም ማለት አይደለም። ነገር ግን በፈተና መካከል እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንዳስታጠቀህና እንደሚያስታጥቅህ በመገንዘብ፣ ባለማቋረጥ በአሸናፊነት ልትኖር እንደምትችል ያሳያል።
3. የእግዚብሔርን ትእዛዝ እንደተላለፍህ ስታውቅ ወዲያውኑ ይቅርታውን ጠይቅ። ፈተናው ወደ ኃጢአት ከመራህ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይቅር እንዲልህ በመጠየቅ ቆም ብለህ ጸልይ። ከእንግዲህ በጌታ እገዛ ይህን ኃጢአት ደግመህ እንደማትሠራው ተማመን። በተመሳሳይ ኃጢአት እንደገና ከተፈተንህ የበፊቱን ገጠመኝ አስታውሰህ፣ «ጌታ ከዚህ በፊት ለዚህ ኃጢአቴ ይቅርታ አድርጎልኛል። ደግሜ ልበድለው አልችልም!» በል።

በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ይቅርታ የሚያስፈልጋቸው አንዳንድ ወጣቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ከነዚህ ወጣቶች ጋር አብረህ ጸልይ። ለአንዳንዶች ይህ ምናልባትም ከልባቸው ንስሐ ገብተው የሚድኑበት የመጀመሪያው ልምምድ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር በቡድንህ ውስጥ የሚሠራውን የመሪነት ተግባር በንቃት ተከታተል።

# ለትችት ወይም ለስደት ምላሽ የምንሰጠው እንዴት ነው?

ከአለን ሰኮት

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. ለትችትና ስደት የምንሰጠው ምላሽ የክርስቶስን ምሳሌነት የተከተለ መሆን ይኖርበታል::
2. የትምህርቱ ዓላማ .. አላግባብ የሆነ ትችት ወይም ስደት በሚያጋጥምበት ጊዜ ዓለማውያን ከሚሰነዝሩት «መልሶ ማጥቃት» የተለየውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አማራጭ ለወጣቶች ማሳየት::
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ወጣቶቻችን በየቀኑ ካለመብቃትና ከዝቅተኛ የማንነት ግምት ጋር ይታገላሉ:: ትችት ብዙውን ጊዜ በውስጡ የተወሰነ እውነት ስለሚያቅፍ፣ ወጣቶች በቀላሉ ሊሸነፉ ይችላሉ:: ሰው በተፈጥሮው ለትችት የሚሰጠው ምላሽ መልሶ ማጥቃት ነው:: ይህ ግን ክርስቶስ የሰጠን ምሳሌ አይደለም:: ወጣቶች ብዙውን ጊዜ ከክርስቶስ ምሳሌነት ጋር የሚቃረን ምክር ጥሩዎች ናቸው ከሚባሉ መምህራን፣ ከጓደኞቻቸው ወይም ከወላጆቻቸው ይቀበላሉ:: ስለሆነም፣ ወጣቶች ምላሾቻቸውን መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረው መንገድ መገምገም አለባቸው:: ክርስቶስ በተደጋጋሚ የቀራጥነት እርምጃዎችን ወስዷል:: ይህንን ያደረገው ግን ለሰዎች ባለው ፍቅር ተነሣሥቶ ነው::
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. ለጥያቄዎችና መልሶች መጻፊያ የሚያስፈልጉ ወረቀቶች፣ እርሳሶችና መጽሐፍ ቅዱሶች::

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል::)

1. ጥያቄዎችና መልሶች:: ለሁሉም ወጣቶች አንዳንድ ወረቀት ስጣቸው:: ግማሾቹ ወጣቶች «እንዴት» የሚል ቃል የታከለባቸውን ጥያቄዎች እንዲጽፉ ንገራቸው:: (ለምሳሌ፣ ሙዝ እንዴት ትልጣለህ?) የተቀሩት ግማሽ ወጣቶቹ ለማያውቁት ጥያቄ መልስ ይጽፋሉ:: (ለምሳሌ፣ በሞቀ ውኃ ውስጥ በመጨመር::) የሁለቱንም ቡድኖች ሥራዎች በመሰብሰብ፣ አንድ ጥያቄና አንድ መልስ እያከታተልህ አንብብ:: ውጤቱ በጣም አስቂኝ ሊሆን ይችላል:: እንደገና ጥያቄዎቹን መልሶች፣ መልሶቹን ጥያቄዎች በማድረግ ልትዝናኑ ትችላላችሁ::
2. የቡድን ዝማሬ::

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው::)



ክርስቲያኖች ከሌሎች ሰዎች ጋር መጣላት እንደሌለባቸው ለሁሉም ግልጽ ነው:: ወዲያ ወዲህ እያልን ከማንወዳቸው ሰዎች ጋር ስንጣላ አንውልም:: ነገር ግን ክርስቲያን ሌሎች ሲሳለቁት ወይም ሲያጠቁት መልሶ ማጥቃት አለበት ወይ? ክርስቲያን መታገሥ ያለበት ምን ያህል ነው? ክርስቲያኖች ሰዎች ፈሪዎች ናቸው ብለው እስከሚያስቡ ድረስ ዝም ማለት አለባቸው? በዚህ ታሪክ ውስጥ አንድ ወጣት ያጋጠመውን ችግር አድምጡ::

ቪክተር ጃክን ከአዳራሹ ጥግ ሲመለከት ለመደበቅ ሞከረ:: ምናልባት ጃክ ሳያየው ያልፍ ይሆናል:: ጃክ በትምህርት ቤት ውስጥ የዱሪዬ ልጆች መሪ ነበር:: ነገር ግን ጃክ ለክርስቲያኖች ወይም ብዙ ጊዜ እንደሚጠራቸው ለቤተክርስቲያን አዘውታሪዎች የተለየ ጥላቻ ያለው ይመስላል:: ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ በቪክተርም ሆነ በሌሎች ክርስቲያን ልጆች ላይ ይሳለቃል:: ጃክ ያለፈ መስሎት ቪክተር መጽሐፎቹን ሰብስቦ ለመሄድ ፊቱን አዞረ:: በዚህም ጊዜ ከጃክ ጋር ተፋጠጡ::

«እሺ፣ ቄሱ፣ ታያለህ:: በመጽሐፍህ ልትመታኝ ነበር» አለና የቪክተርን መጻሕፍት ገፋ:: በዚህ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ የቪክተር መጻሕፍት ከወለሉ ላይ ተዘረገፉ:: ከዚህ በፊት ጃክ በቪክተር ላይ ያላገጠበት ቢሆንም፣ ቪክተር ምንም ምላሽ አልሰጠውም ነበር:: አሁን ግን መጽሐፍ ቅዱሱን ስለጣለበት በዝምታ ሊያልፈው አልቻለም:: ቪክተር ጃክን በመገፍተር፣ «መጽሐፍ ቅዱስን መሬት ላይ ልትጥል አትችልም!» ሲል ጮኸበት::

በዚህ ጊዜ የመግቢያ ደወል በማቃጨሉ፣ ጃክ፣ «ይህንን ከክፍል ስንወጣ እንቀጥላለን፣ ቄሱ:: ማንም እኔን ሊገፈትረኝ እንደማይችል አሳይሃለሁ!» ሲል ጮኸ::

ቪክተር በዕረፍት ሰዓት ከክርስቲያን ጓደኞቹ ጋር ተቀምጦ ሳለ ድካም ይሰማው ነበር:: ለጓደኞቹ ያጋጠመውን በመግለጽ፣ ምን ማድረግ እንዳለበት ጠየቃቸው::

ዴብ፣ «ልትመታ ትችላለህ:: አንድ ሰው ለዚያ ልጅ ትምህርት መስጠት አለበት» ሲል በችኮላ መለሰ::

ዲማካቶ፣ «አይሆንም:: ዝም ብለህ ጸልይለት:: ከመታውማ እንዴት ክርስቲያናዊ ፍቅር ሊያውቅ ይችላል?» ሲል ተቃወመ::

አን፣ «እኔ ከዴብ ጋር እስማማለሁ:: ራስህን ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስህን መከላከል አለብህ:: መጽሐፍ ቅዱስን እንደዚያ ሲያደርግ ዝም ካልን ይህን ቅዱስ መጽሐፍ እንዴት ሊያከብር ይችላል?» አለች::

«እኔ አንተን ብሆን ለምክትል ዳይሬክተሩ ነግሬ ችግር ውስጥ እከተዋለሁ:: ያን ጊዜ ከማን ጋር እንደተጣላ ይገባዋል!» የሚል ቃል ከአዲት ታከለ::

ክልኒተን በበኩሉ፣ «ምንም ምርጫ የለህም። የትምህርት ሰዓት ሲያልቅ መስክርለት። ከመታህ ሌላውን ጉንጭህን አዙርለት። በተጨማሪም፣ ስለገፈተርኸው ይቅርታ ልትጠይቀው ይገባል» ሲል ተናገረ።

«ምክራችሁ ጥሩ ነበር። ግን ጃክ ቢመታኝስ? ይኼ ስለ እግዚአብሔር የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድነው? ተመትቼ ራሴን ከሳትሁ በኋላ ብዙም ልመሰክር አልችልም!» አለ ቪክተር።

*መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙ ባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)*

1. ለቪክተር ከሁሉም የሚሻለው የማን ምክር ነው? ምክራቸውን በደረጃ ከ1-5 አስቀምጥ። በዚህ ደረጃ ለምን እንዳስቀመጥህ አብራራ።
2. በዚያ ሁኔታ ቪክተር እንደ ክርስቲያን ምን እንዲያደርግ ትመክረዋለህ?
3. በቪክተር ቦታ ብትሆን ምን ታደርጋለህ?

*ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)*

ሉቃስ 9:51-56: *«የሚወጣበትም ወራት በቀረበ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን አቀና። በፊቱም መልእክተኞችን ሰደደ። ሄደውም ሊያሰናዱለት ወደ አንድ ወደ ሳምራውያን መንደር ገቡ። ፊቱም ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚሄድ ስለነበረ አልተቀበሉትም። ደቀመዛሙርቱም ያዕቆብና ዮሐንስ አይተው፣ ጌታ ሆይ፣ ኤልያስ ደግሞ እንዳደረገ እሳት ከሰማይ ወርዶ ያጥፋቸው እንል ዘንድ ትወዳለህን? አሉት። እርሱ ግን ዘወር ብሎ ገሠጻቸውና፣ ምን ዓይነት መንፈስ እንደሆናችሁ አታውቁም። የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም አለ። ወደ ሌላ መንደርም ሄዱ።»* ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በምታነቡበት ጊዜ፣ በቀልና መልሶ ማጥቃት ክርስቲያናዊ መንገዶች እንዳልሆኑ ትመለከታላችሁ። ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ የሰማርያን መንደር እንዲያጠፋ ያቀረቡለትን አሳብ አልተቀበለም። ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የክርስቶስን ምሳሌነት እንድንከተል ያበረታቱናል። ለመብታችን ወይም ክብራችንን ለማስጠበቅ ብሎ መፋለም ክርስቲያናዊ መንገድ አይደለም። የክርስቲያን ኃላፊነት ለእውነት በቆራጥነት መቆም ነው። ነገር ግን ቆራጥነት ሽብርተኝነትን አያጠቃልልም። ለክፋት የምንሰጠው ምላሽ የእግዚአብሔርን ፍቅር ፍንትው አድርጎ ማሳየት አለበት። ተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች: ሮሜ 12:14-21፣ 1ኛ ጴጥሮስ 2:20-24፣ 3:9-17።

*ረ. የመወያያ ጥያቄዎች*



1. የቪክተርና የጃክ ታሪክ ከሉቃስ 9:51-56 ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?
2. ይህን ምንባብ ካነበብህ በኋላ ክርስቲያን መልሶ ማጥቃት ያለበት መቼ መሆን አለበት ትላለህ?
3. አሁን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በመመሥረት ለቪክተር ምን ምክር ትሰጠዋለህ?
4. ከፍተኛ የአካል ጉዳት ቢደርስብህ ቢሆን ምን ዓይነት ምላሽ ትሰጣለህ?

*ሰ. መዝጊያ*

ክፍለጊዜውን እያጠቃለልህ ሳለ፣ ወጣቶቹ ለጠብ የሚያነሳሷቸውን ሰዎች ወይም ሁኔታዎች እንዲያስቡ ጠይቃቸው። ይህም በትምህርት ቤት፣ በሥራ ቦታ ወይም በቤት ውስጥ የሚያጋጥማቸው ሰው ሊሆን ይችላል። ከዚያም በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ እንዲያስቡ ንገራቸው።

1. የራሴን መብቶችና ክብር ለመጠበቅ ስል ብቻ መጣላት አለብኝ?
2. ለዚህ ሰው ክፋት ምላሽ ምን መልካም ነገር ላደርግለት እችላለሁ?
3. ሊለወጥ የሚገባውና ካልተለወጠ ምስክርነቴን ሊያደናቅፍ የሚችል ባሕርይ በሕይወቴ ውስጥ አለን?

አንተም የወጣቶች መሪ እንዲለወጥ የምትፈልገው ሁኔታ ኖሮህ ብታካፍላቸው ወጣቶቹ ተመሳሳይ እርምጃ ለመውሰድ ይነሣሣሉ። ወጣቶቹ ያሏቸውን ጥያቄዎች ወይም ችግሮች እንዲያካፍሉ ፍቀድላቸው። በጸሎት ፈጽም።

*ሸ. አማራጭ የማቅረቢያ መንገድ*

የቪክተርንና የጃክን ታሪክ በምታነብበት ጊዜ፣ የቪክተር ጓደኞች ምክር የሚሰጡበት ክፍል ጋ ስትደርስ ማንበብህን አቁም። እያንዳንዱ ወጣት ለቪክተር የራሱን አስተያየት እንዲጽፍ አድርግ። ከዚያም አሳባቸውን እርስ በርሳቸው እንዲካፈሉ አድርግ። ለምን እንደዚያ ዓይነት ምላሽ እንደሰጡ ጠይቃቸው። የመጽሐፍ ቅዱስን ምንባብ ካነበብህ በኋላ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ለቪክተር አስተያየቶቻቸውን እንዲጽፉ ጠይቃቸው። በዚህ ጊዜ ከጥቅሱ የተወሰነውን ክፍል እንዲጠቅሱ አሳስባቸው።

*<u>በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና! አይዞህ! አትፍራ! አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን? ኢያሱ 1:9</u>*

## ሀብታችን ተቆጣጥሮናል?

ከዲ. ኬሲ.

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. ሀብት ማፍራቱ ስሕተት ባይሆንም፣ ሀብታችን እንዲቆጣጠረን ማድረግ የለብንም።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ይህ ትምህርት ወጣቶች ስለ ገንዘብ በቀረቡት መርሆች አማካኝነት የንብረት አስተዳዳሪነትን (የመጋቢነትን) መርህ እንዲገነዘቡ ያደርጋል።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ዛሬ በአንዳንድ ወንጌላውያን አብያተክርስቲያናት ውስጥ ስለ ገንዘብ የተሳሳተ ትምህርት የሚያስተምሩ ወገኖች አሉ። አንዳንዶች መጽሐፍ ቅዱስን የሚያምን አማኝ ሁሉ ባለጸጋና ጤናማ ይሆናል ብለው ያስተምራሉ። አንዳንዶች ደግሞ በቂ እምነት ካለን የምናምነውን ነገር ሁሉ ልናገኝ እንችላለን ይላሉ። እነዚህ ሰዎች ልባችን የፈለገውን ነገር ሁሉ በመምረጥ፣ ስሙን በመጥራትና የኛ እንደሆነ በማወጅ ከእግዚአብሔር ልንቀበል እንችላለን ብለው ያስባሉ።
   መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሀብት የሚያቀርበው አመለካከት ግን ከዚህ የተለየ ነው። ስለ ገንዘብ ከሚናገሩት ዓበይት የመጽሐፍ ቅዱስ መርሆች አንዱ ክርስቲያኖች ስለ ገንዘብና ሀብት ሚዛናዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያስተምራል። ይህ ትምህርት በቁሳዊነት ላይ በማተኮር ወጣቶች በታማኝነት የራሳቸውን አመለካከት እንዲመዝኑና ስለ ገንዘብና ሀብት ተገቢውን የእሴት ሥርዓት እንዲገነቡ ለማገዝ ይጥራል። አንድ ሰው በቀላሉ በሌለውና ዳሩ ግን በሚመኘው ሀብት ቁጥጥር ሥር ሊውል እንደሚችል አትዘንጋ።
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. የመጸዳጃ ወረቀት፣ የሚለጠጡ ላስቲኮች፣ ጽሑፍ ያልሰፈረባቸው ወረቀቶች፣ እርሳሶች።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)

1. በኃይል መንፋት። በያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ከአራት እስከ ስምንት ተጨዋቾች እንዲኖሩ አድርገህ ወጣቶችን ከፋፍል። ለእያንዳንዱ ቡድን መሪ አንድ የመጸዳጃ ወረቀት አድል። የመጸዳጃ ወረቀቱ ድርብ ከሆነ፣ ይህንን ጨዋታ ቀለል ባለ ወረቀት ማካሄዱ ስለሚቀል ነጣጥለህ ስጣቸው። ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ፣ የቡድን መሪዎቹ ከወንበር ላይ ወጥተው የመጸዳጃ ወረቀቶቹን ከቡድኑ አባላቱ ከፍ አድርገው ይጥላሉ። የጨዋታው ዓላማ የትኛው ቡድን ወረቀቱን በትንፋሽ እየገፋ በአየር ላይ ብዙ እንደሚያቆይ መመልከት ነው። ወረቀቱ ከሰው ላይ ካረፈ፣ በሁለት ሰከንዶች ውስጥ በትንፋሽ ተገፋፍቶ መነሣት አለበት። ካልሆነ ቡድኑ ከጨዋታ ውጭ ይሆናል።
2. ተለጣጭ ላስቲክ። ስለ ውድድሩ ማብራሪያ ከመስጠትህ በፊት እያንዳንዱ ቡድን ሁለት ሁለት ተጨዋቾችን እንዲመርጥ ጠይቅ። ተጨዋቾቹ በክፍሉ ውስጥ ወዳሉት ወጣቶች ፊታቸውን አዙረው በመድረኩ ላይ ይሰለፉ። የአንድ ቡድን ተጨዋቾች አጠገብ ለአጠገብ መቆም አለባቸው። ለእያንዳንዱ ተጫዋች የሚለጠጥ ላስቲክ አድል። ተጨዋቾቹ እነዚህን ላስቲኮች በራሳቸው ላይ ያደርጋሉ። ከኋላ በኩል ተለጣጭ ላስቲኩ እስከ አንገታቸው ድረስ መውረድ አለበት። ከፊታቸው በኩል እስከ አፍንጫቸው ጫፍ ድረስ መድረስ አለበት። የጨዋታው ዓላማ ራስን በማወዛወዝ ላስቲኩን ከአንገት ላይ ማውረድ መቻል ነው። ጨዋታው አንተ በምትሰጣቸው ምልክት ይጀመራል። ከእያንዳንዱ ቡድን ሁለት ሰዎች በተሳካ ሁኔታ ላስቲኩን አንገታቸው ላይ እስኪያወርዱ ድረስ ውድድሩ እንደሚቀጠል አስረዳቸው።
3. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው።)

ወጣቶች ጥያቄዎችን መመለስ ያስደስታቸዋል። ለእያንዳንዳቸው ወረቀትና እርሳስ አድል። ወደ ታች ከ1-15 ያሉትን ቁጥሮች እንዲጽፉ ንገራቸው። ጥያቄዎችን ትጠይቃቸውና ውሸት ሲሆን «0»፣ እውነት ሲሆን «1»፣ በጣም እውነት ሲሆን ደግሞ «2» ቁጥር እንዲጽፉ ንገራቸው።

1ኛ ጥያቄ፡ ብዙውን ጊዜ ሌሎች ሰዎች ያላቸው ነገር እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ።

2ኛ ጥያቄ፡ ሰዎች፣ «ትልቅ ሰው ለመሆን አንድ ነገር የግልህ ማድረግ አለብህ» በሚሉበት ጊዜ፣ ያንን ነገር መግዛት ያስፈኛል።

3ኛ ጥያቄ፡ ወላጆቼ መኪና ወይም ቆንጆ ቤት ቢኖራቸው ኖሮ የበለጠ እኮራባቸው ነበር።

4ኛ ጥያቄ፡ ሱቆችን በምጎበኝበት ጊዜ ሁሉ አንዳንድ ነገሮችን እገዛለሁ።

5ኛ ጥያቄ፡ አንድ ከልቤ የምወደው ነገር ካየሁ የግሌ ለማድረግ እገደዳለሁ።

6ኛ ጥያቄ፡ ድሆችን ለመርዳት ከሁሉም የሚሻለው መንገድ ድሆችን ለሚረዳ ድርጅት ገንዘብ መስጠት ይመስለኛል።

7ኛ ጥያቄ፡ ስጦታ በመስጠት ለሰዎች ያለኝን ፍቅር እገልጻለሁ።

8ኛ ጥያቄ: ትልቅ ስሆን ግዙፍ ቤት፣ ውድ መኪናና ብዙ ገንዘብ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ::
9ኛ ጥያቄ: ጥሩ ስሜት የሚሰማኝ ኪሴ ውስጥ ገንዘብ ሲኖር ነው::
10ኛ ጥያቄ: ሀብታም ለመሆን ትልቅ ፍላጎት አለኝ::
11ኛ ጥያቄ: የወላጆቼ ሀብትና ቤት እንደ ሌሎች ሰዎች የሚያስደንቅ ሆኖ በማይገኝበት ጊዜ ኃፍረት ይሰማኛል::
12ኛ ጥያቄ: ከዋንኞቹ ፍርሃቶቼ አንዱ የገንዘብ እጥረት ነው::
13ኛ ጥያቄ: አንድ ሰው ሬድዮናችንን ወይም ቴለቪዥናችንን ቢሰርቅ በጣም የማዝን ይመስለኛል::
14ኛ ጥያቄ: ነገሮችን ለሰዎች ማዋስ ያስቸግረኛል::
15ኛ ጥያቄ: አንዳንድ ጊዜ በቂ ገንዘብና ሀብት የማገኝበት ጊዜ ይመጣ ይሆን? እያልሁ አስባለሁ::

(የሚከተለውን ለወጣቶቹ አካፍላቸው::)
የ1ኛ፣ 2ኛና 3ኛ ጥያቄዎችን መልሶች ደምር:: እነዚህ ጥያቄዎች ትልቅ ደረጃን ስለመፈለግ የሚያስረዱ ናቸው:: ብዙውን ጊዜ ሌሎችን ለማስደነቅ እንፈልጋለን:: ይህ አመለካከት እንዲቆጣጠረን ካደረግን፣ ቁሳዊነት ይሰለጥንብናል:: በነዚህ ጥያቄዎች 4 ነጥብ ወይም ከዚያ በላይ ካመጣህ፣ ምናልባትም ከትልቅ ደረጃ ላይ የመድረስ ፍላጎትህ ከእግዚአብሔር ጋር በምታደርገው ግንኙነት ላይ መሰናክል እየፈጠረና ከሀብትህ ቁጥጥር ሥር እንድትሆን እያደረገህ ሊሆን ይችላል:: ዝቅተኛ ነጥብ ካገኘህ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለመድረስ ብዙም ፍላጎት የለህም ማለት ነው:: ነገር ግን 1 ወይም 2 ያልሃቸውን ጥያቄዎች እንደገና ተመልከትና ለምን እንደዚያ እንዳደረግህ በጥልቀት አስብበት::

የ4ኛና 5ኛ ጥያቄዎችን መልሶች ደምር:: እነዚህ ጥያቄዎች ምን ያህል በሰዎች ግፊት እንደምትነዳ ያሳያሉ:: ብዙ ሻጮችና የማስታወቂያ ድርጅቶች በስሜት የሚነዱትን ሰዎች በመጠቀም የመተዳደሪያ ገቢ ያገኛሉ:: በስሜት መገፋት ሁልጊዜም ከሚፈለገው በላይ መግዛትን ወይም ገንዘብ ማውጣትን ያስከትላል:: ለነዚህ ጥያቄዎች ያገኘኸው ውጤት 1 ወይም 2 ከሆነ፣ ትንሽ በስሜት መገፋት ያጠቃሃል ማለት ነው:: 3 ቀይም 4 ካገኘህ፣ ምናልባትም ገንዘብህን በመልካም ሁኔታ ለማስተዳደር አልቻልህም ማለት ነው::

ለ6ኛና 7ኛ ጥያቄዎች የሰጠሃቸውን መልሶች ደምር:: አንዳንድ ጊዜ ስጦታዎችን ወይም ገንዘብን መስጠት የፍቅር ምትክ የሚሆንበት ጊዜ አለ:: ስጦታን መስጠት የፍቅር ተግባር ሊሆን ቢችልም፣ አንዳንድ ጊዜ ግን ራሳችንን ለመስጠት ባለመፈለጋችን ስጦታዎችን ልንሰጥ እንደምንችል ግልጽ ነው:: ሀብት ከግንኙነቶች የበለጠ ዋጋ



የሚያወጣው ቁሳውያን ስንሆን ነው:: በነዚህ ጥያቄዎች ከ3 ወይም 4 በላይ ካገኘህ ስለ መስጠት ያለህን አስተሳሰብ እንደገና መገምገም ይኖርብሃል::
ከ8ኛ እስከ 11ኛ ላሉት ጥያቄዎች የሰጠሃቸውን መልሶች ደምር:: ይህ የዓለማችን ዓይነተኛ ክፍልና በተመሳሳይ ጊዜ ለመንፈሳዊ ጤንነታችን አደገኛ በመሆኑ ትኩረት የሚሰጠው ምድብ ነው:: ብዙ ሰዎች ራሳቸውን የሚለኩት በሀብታቸው መጠን ነው:: «ብዙ ሀብት ካለኝ ብዙ ተፈላጊነት ይኖረኛል» የሚለው አስተሳሰብ በብዙ ሰዎች ልብ ውስጥ ተሰንቅሮ የሚገኝ ቢሆንም፣ የተሳሳተ ነው:: ብዙ ሰዎች «ትክክለኛ» የሚባሉ ነገሮች ከሌሏቸው ራሳቸውን ከውዳቂዎች ተራ ይመድባሉ:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህ እውነት እንዳልሆነ ያስረዳል:: እኛ ክርስቶስ የሞተልን ሰዎች እንደመሆናችን፣ ዋጋችን ከፍ ያለ ነው:: ለራሳችን ወይም ለሌሎች ሰዎች የምንሰጠው ግምት ከገንዘብ ጋር መያያዝ የለበትም:: በነዚህ ጥያቄዎች ከ4 እስከ 8 ነጥብ ካመጣህ ኢየሱስ ክርስቶስ ለማንነት ከበረታ ያለህን አስተሳሰብ ሊለውጠው ይገባል ማለት ነው:: እግዚአብሔር ፈጣሪህ እንደሆነና እርሱም እንደማይሳሳት አስታውስ:: የሰብአዊነት ዋጋህ በምታደርጋቸው ነገሮች ወይም ባለህ ሀብት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፣ ነገር ግን <u>በፈጠረህ</u> አምላክ ላይ የሚደገፍ ነው::

ከ12ኛ እስከ 15ኛ ላሉት ጥያቄዎች የሰጠሃቸውን መልሶች ደምር:: አንዳንድ ጊዜ ሀብት አስተማማኝ ሕይወት እንድንኖር ይረዳናል:: ብዙ ሀብት ሲኖረን ብዙ እንደተደላደልን እናስባለን:: ከእግዚአብሔር ይልቅ በነገሮች ወይም በገንዘብ ላይ እንደገፋለን:: ሀብት ለዘላለም አይኖርም:: እንዲያውም አብዛኞቹ ሀብቶች ፈጥነው የሚጠፉ ናቸው! በመሆኑም በገንዘብ ላይ መደገፍ የውሸት መተማመኛ በመሆኑ ከእግዚአብሔር ጋር ያለህን ግንኙነት ያበላሻል:: ከ1 እስከ 3 ነጥብ፣ በቁሳዊ ነገሮች ላይ በመጠኑ እንደምትደገፍ ያሳያል:: ከ4 እስከ 8 ነጥቦች ካገኘህ በሀብት ወይም በገንዘብ ላይ በጣም ትደገፋለህ ማለት ነው::

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ::)
1. ትልቅ ደረጃ የሚፈልግ ሰው ምን ዓይነት እንደሆነ ግለጽ::
2. ምርጥ ልብሶችን የመልበስ ፍላጎት ስሕተት ነውን? ለምን?
3. በስሜት መገፋት ከሚገባው በላይ ገንዘብ እንድናወጣ የሚያደርገን እንዴት ነው? ምሳሌዎችን ስጥ::
4. ገንዘብ ከመስጠት ሌላ ድሆችን እንዴት ልንረዳ እንችላለን?

5. ለአንድ ሰው ያለህን ፍቅር ለመግለጽ ከፈለግህ፣ ከስጦታ ውጭ ምን ልትሰጥ ትችላለህ?
6. የማንነታችን ዋጋ ሲመሠረት የሚገባው ምን ላይ ነው?
7. ስለራስህ ጥሩ ስሜት እንዲሰማህ የሚያደርጉ ምን ዓይነት ነገሮችን ታደርጋለህ?
8. ብዙ ገንዘብ በእግዚአብሔር ላይ እንዳንደገፍ ሊያደርገን ይችላል? ከሆነ፣ እንዴት?
9. አንድ ሰው ብዙ ደመወዝ እያገኘ በእግዚአብሔር ላይ ሊደገፍ ይችላልን?

*ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች* (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)

አስፈላጊው ነገር ብዙ ገንዘብ መያዛችን ሳይሆን፣ ለገንዘባችን ያለን አመለካከት ነው። ሰው ውጫዊ ነገሮችን ያያል። እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል። ለገንዘብና ለሀብት ያለን አመለካከት ወሳኝ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ባለጸግነትና ገንዘብ ደጋግሞ ይናገራል። ብዙዎቹ የመጽሐፈ ምሳሌ ምንባቦች ስለ ሀብት የሚናገሩ በመሆናቸው፣ ጠቃሚ መምሪያዎችን ሊሰጡን ይችላሉ።

ምሳሌ 8:17-21: *«እኔ የሚወድዱኝን እወዳለሁ። ተግተው የሚሹኝም ያገኙኛል። ብልጥግናና ክብር በእኔ ዘንድ ነው። ብዙ ሀብትና ጽድቅም። ፍሬዬም ከምዝምዝ ወርቅ ይሻላል። ቡቃያዬም ከተመረጠች ብር። እኔ በጽድቅ መንገድ እሄዳለሁ። በፍርድም ጎዳና መካከል። ለሚወዱኝ ርስት አወርሳቸው ዘንድ፣ ቤተመዛግብታቸውንም እሞላ ዘንድ።»* ምሳሌ ምዕራፍ 8 የሚናገረው ስለ ጥበብ አስፈላጊነት ነው። ቁሳዊነት የተሳሳቱ ነገሮችን የማስቀደም ውጤት ስለሆነ፣ ይህ ምንባብ በጣም አስፈላጊ ነው። ሀብት አስተሳሰባችንን በሚቆጣጠርበት ጊዜ እግዚአብሔርን ለማየት እንቸገራለን። ነገር ግን አስቀድመን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን ብንሻ፣ ሌሎች ነገሮችም (ምግብና ልብስ) ይሰጡናል።

ይህ ምንባብ የእግዚአብሔር ጥበብ ዘላቂ ብልጽግናንና ሀብትን እንደሚያስገኝ ይናገራል። ገንዘብና ሀብት በራሳቸው ዘላለማዊ እሴት ስለሌላቸው፣ በመጋቢያነት ብቻ የምንገለገልባቸው ነገሮች ናቸው። ሁልጊዜም ግንኙነቶች ከሀብቶች፣ ሰዎችም ከገንዘብ ይልቃሉ። የገንዘብ ፍቅር በቀላሉ የእግዚአብሔርን ስፍራ ሊወስድ ይችላል። ይህም ወደ ጥፋት የሚመራ መንገድ ነው። ነገር ግን ሀብትን በተገቢ ስፍራ ላይ ብናስቀምጥ፣ ልንደሰትበትና እግዚአብሔር እንዳቀደው ልንጠቀም እንችላለን። ገንዘብ እንድንጠቀምበት እንጂ እንድናመልከው የተሰጠን ነገር አይደለም።

*ረ. የመወያያ ጥያቄዎች*



1. ገንዘብን በየትኛውም መንገድ ብናገኝ ችግር አለው? (ምሳሌ 10:2፣ 16:8፣ 28:6)
2. ከእግዚአብሔር ይልቅ በሀብት ላይ መደገፍ አደገኛ የሚሆነው ለምንድነው? (ምሳሌ 11:14፣ 11:28)
3. ስግብግብነት ምንድነው?
4. ወጣቶች የሚስገበገቡት እንዴት ነው?
5. መጽሐፈ ምሳሌ ስለ ስግብግብነት የሚናገረውን ከ11:26፣ 15:27፣ 28:22፣ 8:25 አንብብ።
6. ለድሆች ኃላፊነት አለብን? (ምሳሌ 11:25፣ 14:21፣ 21:13፣ 28:27)
7. ለገንዘብና ሀብት ምን ዓይነት አመለካከት ሊኖረን ይገባል?
8. ከቁሳዊነት ራሳችንን እንዴት ልንጠብቅ እንችላለን?

*ሰ. መዝጊያ*

ለገንዘብና ሀብት ተገቢውን አመለካከት መያዝ መልካም የንብረት አስተዳዳሪነት (መጋቢነት) ነው (ማቴዎስ 25:14)። ይህ አገልጋይ የንብረት አስተዳዳሪነት እንጂ ባለቤት አይደለም። እግዚአብሔር ያለን ሀብት ሁሉ ባለቤት ሲሆን፣ እኛ አስተዳዳሪዎች ነን።

በጥረት የተገኘውን ገንዘባችንን ባንክ ቤት ውስጥ በምናስቀምጥበት ጊዜ፣ ባንኩ የገንዘባችን አስተዳዳሪ ይሆናል። ባንኩ በገንዘቡ በአስተዋይነት እንዲነግድና በምንፈልግበት ጊዜ እስከነ ወለዱ እንዲመልስልን እንጠብቃለን።

በተመሳሳይ መንገድ እግዚአብሔር ሀብቱን ሰጥቶናል። እኛ የገንዘቡና የንብረቱ አስተዳዳሪዎች ነን። በማንኛውም ጊዜ፣ በአደራ የሰጠንን ገንዘብ እስከነ ወለዱ እንድንመልስለት ሊጠይቀን ይችላል። እኛ እግዚአብሔርን ማገልገል አለብን እንጂ እርሱ እኛን ሊያገለግል አይገባም። አሥራት በእግዚአብሔር ላይ መደገፋችንን የሚያመለክት ነገር ነው። ይህ የኃላፊነታችን ፍጻሜ ሳይሆን ጅማሬው ብቻ ነው።

ሀብትህ እስካልተቆጣጠረህ ድረስ፣ ሀብት ማግኘቱ ስሕተት አይደለም። የሚከተሉት ሐሳቦች ስለ ገንዘብና ሀብት ልብ ልንላቸው የሚገቡ ናቸው።

1. የምትችለውን ያህል ገንዘብ ሠርተህ አግኝ። የራሳችንን ወይም የሌሎችን መንፈሳዊ ወይም ሥጋዊ ጤንነት በመጉዳት ገንዘብን ለማግኘት መጣር ባይኖርብንም፣ ታማኝነት በተሞላበት ሥራ የቻልነውን ያህል ገንዘብ ልናገኝ እንችላለን። እግዚአብሔር የሰጠንን ችሎታና ብቃት በሚገባ መጠቀም አለብን።
2. የምትችለውን ያህል ገንዘብ አጠራቅም። ውድ ችሎታዎችንና ገንዘብን አታባክን። የሚያስፈልግህን ብቻ እየተጠቀምህ፣ የተቀረውን አጠራቅም።

3. የምትችለውን ገንዘብ ሁሉ ስጥ:: ገንዘብን በማግኘትህ ወይም በማጠራቀምህ አንድ ነገር እንዳደረግህ አታስብ:: አንድ እርምጃ ወደፊት ካልሄድህ ይህ ሁሉ ምንም አይደለም:: ሰጪ መሆን አለብህ::

እግዚአብሔር የሀብታችን ጌታ እንዲሆን በመጸለይ ፈጽም::

ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል
ምን ይጠቅመዋል?
ማቴ. 16:26



## እርስበርሳችን መደጋገፍ አለብን
ከማርክ ፒቸር

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. የክርስትና ሕይወት ለብቻችን የምንኖረው አይደለም:: ስለሆነም፣ ወጣቶች በክርስቲያናዊ ጉዟቸው እርስበርሳቸው ሊደጋገፉ ይገባል::
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ይህ ትምህርት በክርስትና እርስበርስ መደጋገፉ አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ፣ ወጣቶች በየቀኑ እርስበርሳቸው የሚደጋገፉባቸውን ተግባራዊ መንገዶች ያስተምራል::
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. አንዳንድ ጊዜ የክርስትናን ሕይወት በራሳችን ጥረት ብቻ መኖር አለብን ብለን እናስባለን:: እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ማንም ብቻውን ክርስቲያናዊ ሕይወት ለመኖር መጣር የለበትም:: መጽሐፍ ቅዱስ በየዕለቱ ከክርስቶስ ጋር በምናደርገው ጉዞ እርስበርሳችን መደጋገፍ እንዳለብን ያስተምራል:: በመተባበር ውስጥ ብርታት እንዳለ ማስታወስ አለብን:: ለጸሎትና ለማበረታቻ አንዳችን በሌላችን ላይ መደገፍ አለብን:: አንዳንድ ጊዜ አንድ ወዳጅህ እየጸለየልህ መሆኑን ማወቁ ራሱ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መጽናናትን ይፈጥራል::
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. እርሳሶችና ወረቀት::

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል::)

1. ታሪክን በደቂቃ:: በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ሦስት አባላት እንዲኖሩ አድርገህ ክፈላቸው:: እያንዳንዱ የቡድን አባል በአንድ ደቂቃ ውስጥ የሕይወቱን ታሪክ በሙሉ ላለበት ቡድን አባላት እንድናገር ጠይቅ:: ከ3 ደቂቃዎች መጨረሻ ላይ በክፍሉ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች በሙሉ ታሪካቸውን ተናግረው መጨረስ አለባቸው::
2. የስም ጨዋታ::ሁሉም ወጣቶች በክብ ቅርጽ እንዲቀመጡ አድርግ:: (ብዙ ወጣቶች ካሉ ሁለት ወይም ከዚያ የሚበልጡ ክቦች ሠርተው ሊቀመጡ ይችላሉ::) ይህን ጨዋታ የሚጀምር ሰው ለራሱ አንድ የፈጠራ ስም ይመርጣል:: ለምሳሌ፣ የመጀመሪያው ልጅ ስም ጆርጅ ከሆነ፣ ራሱን «ደጉ ጆርጅ» ብሎ ሊያስተዋውቅ ይችላል:: ከዚያም ሁለተኛይቱ ልጅ ራሷን ካስተዋወቀች በኋላ የመጀመሪያውን ልጅ ስም መናገር አለባት:: «ስሜ ደስተኛይቱ ሐና ይባላል:: እሱ ደጉ ጆርጅ ይባላል::» በክቡ ውስጥ ወደ መጨረሻው ልጅ በምትደርስበት ጊዜ፣

የመጨረሻው ልጅ ራሱንና ከመጀመሪያው ጀምሮ በክቡ ዙሪያ የሚገኙትን ልጆች በሙሉ ያስተዋውቃል::

3. በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ሦስት አባላት እንዲኖሩ አድርገህ ክፈላቸው:: ለእያንዳንዱ ልጅ ወረቀትና እርሳስ አድል:: እያንዳንዱ ልጅ ባለፈው ዓመት መንፈሳዊ ሕይወቱ ምን ይመስል እንደነበረ የሚያሳይ ካርታ ወይም ሠንጠረዥ እንዲሠራ ጠይቅ:: የሚከተለው ለዚህ ምሳሌ ሊሆን ይችላል::




ወጣቶች ይህን ካርታ ለሌሎች የቡድኑ አባላት የሚያካፍሉበትን ጊዜ ስጣቸው::

4. የቡድን ዝማሬ::

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው::)

ከጥቂት ዓመታት በፊት ሩበን ወልች የተባለ ደራሲ <u>ሌሎች ሰዎች አያስፈልጉንም</u> የሚል መጽሐፍ ጽፎ ነበር:: የክርስትናን ሕይወት ለመኖር ግን ሌሎች ሰዎች ያስፈልጉናል:: ይህ ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ በቂያችን አይደለም ማለት አይሆንም:: ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በአካባቢያችን ባሉት ሌሎች ሰዎችም አማካኝነት ይሠራል ማለት ነው:: በመንፈሳዊ ሕይወታችን ይረዱን ዘንድ በወዳጆቻችን ላይ በምንተማመንበት ጊዜ ድጋፍና ብርታት እናገኛለን:: የምናደንቃቸውን ሰዎች ለመምሰል መፈለጋችን እውነት ቢሆንም፣ ብዙ ጊዜ አብረውን የሚያሳልፉትን ሰዎች እንደምንመስልም ግልጽ ነው:: ስለሆነም፣ ብዙ ጊዜህን የምታሳልፈው ከኢየሱስ ጋር ከሚመላለሱ ሰዎች ጋር ከሆነ፣ አንተም ይህንኑ የምታደርግበት ሰፊ ዕድል ይኖርሃል::

ይህም አንዳችሁ ሌላችሁን የምታስተናግዱበት መንገድ አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል:: መጽሐፍ ቅዱስ አንዳችን ሌላውን ማነጽ እንጂ መጉዳት እንደሌለብን ያስተምራል:: እስኪ ስለዚህ ጉዳይ ለአንድ አፍታ እናስብ:: እስኪ እርስበርሳችሁ የምትለዋወጧቸውን አንዳንድ ንግግሮች እንዘርዝርና ገንቢዎች ወይም አፍራሾች መሆናቸውን እንመልከት::

በጥቁር ሰሌዳ ወይም በወረቀት ላይ ሁለት ዓምዶችን አዘጋጅ: 1) ገንቢ፣ 2) አፍራሽ:: ወጣቶቹ ብዙውን ጊዜ የሚጠቀሙባቸውን ሐረጎች፣ ዓረፍተነገሮችና ስሞች እንዲነግሩህ አበረታታቸውና በተገቢው ዓምድ ላይ ጻፍ::



ለቀልድ ያህል (እንዲሁም ቁምነገር ለማስተማር)፣ ሁለት ወጣቶች በ«አፍራሽ» ዓምድ በተጻፉት ሐረጎችና ዓረፍተነገሮች ተጠቅመው እንዲነጋገሩ አድርግ:: የወጣቶቹ የመወያያ ርእስ ቤተክርስቲያን እንዲሆንና ስለ ቤተክርስቲያን በሚነጋገሩበት ጊዜ በዚህ ዓምድ ሥር የተጠቀሱትን ሐረጎችና ዓረፍተነገሮች እንዲጠቀሙ ንገራቸው:: (ከሦስት እስከ አምስት ደቂቃዎችን ስጣቸው::)

የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በመጠየቅ፣ ሁሉም ወጣቶች ለዚህ ሁኔታ ምላሽ እንዲሰጡ ጠይቅ:: 1) እንደዚያ ሲነጋገሩ መስማቱ ምን ስሜት አሳደረባችሁ? 2) ዛሬ ወደዚህ ቡድን የተቀላቀለ አዲስ ወጣት ቢኖር ሌላ ቀን ወደዚህ ኅብረት ተመልሶ የሚመጣ ይመስላችኋል? 3) እነዚህ ሁለት ወጣቶች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ለማገዝ የተከሰተ ሁኔታ ነበር?

አሁን ሁለት ወጣቶች ከገንቢ ዓምድ ሥር የተዘረዘሩትን ቃላት ተጠቅመው እንዲነጋገሩ አድርግ:: ለወጣቶቹ ከላይ ያነሣሃቸውን ጥያቄዎች ደግመህ አቅርብላቸው::

አንዳንድ ጊዜ የምንነጋገርባቸው ቃላት የሚያስከትሏቸውን አደጋዎች አናጤንም:: አፍራሽ ሳይሆን ገንቢ ሚና እንጫወት ዘንድ አንዳችን ሌላችንን እንሻለን::

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ::)

1. አንዳንድ ሰዎች ጥሩ ያልሆኑትን ቃላት በሌሎች ላይ የሚሰነዝሩትን ለምንድነው?
2. ሰዎች አሉታዊ አስተያየቶችን ብቻ ቢሰነዝሩብህ፣ ምን ይሰማሃል?
3. ሌሎችን ለመግለጽ የምትጠቀምባቸውን ሐረጎች በመጠቀም አንድ ሰው አንተን ቢገልጽህ ምን ይሰማሃል?
4. አፍራሽ ቃላትን ብቻ በመጠቀም የሚነጋገር የወጣቶች ቡድን ምን ይሆናል?
5. ገንቢ ቃላትን ብቻ በመጠቀም የሚነጋገር የወጣቶች ቡድን ምን ይሆናል?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው::)

1. ሮሜ 12:10፡ የአንድ ቤተሰብ አባላት ስለሆንን በቤተክርስቲያን ውስጥ እርስበርስ መዋደዳችን አስፈላጊ ነው:: እግዚአብሔር አባታችን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ ወንድማችን እንደመሆኑ፣ ሁላችንም በክርስቶስ ወንድማማቾችና እህትማማቾች ነን:: ስለሆነም፣ እንደማይተዋወቁ ሰዎች ልንሆን አንችልም::

በቤተክርስቲያን ውስጥ የቤተሰቡ አካል መሆን አለብን፡፡ ሁላችንም ሌላውን ሰው ሁሉ ከራሳችን በላይ ብናከብር በወጣት ቡድናችን ውስጥ ምን ይከሰት ይሆን? ክርስቶስ የኖረው በዚህ ዓይነት ሁኔታ አልነበረምን?

2. ሮሜ 15:5-7: እርስ በርሳችን መቀባበል አለብን፡፡ ይህ ግን በአጋጣሚ የሚከሰት ሳይሆን፣ ጥረትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህ ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ማሰብን ይጠይቃል፡፡ ሰዎች ከአሉታዊና አቃቂር ማውጣት ከሰፈነበት ድባብ ይልቅ ፍቅርና መቀባበል ባለበት ቤተክርስስቲያን ውስጥ ቢያመልኩ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የበለጠ ያድጋሉ፡፡ ተስማምተን ለመኖር በማንችልበት ጊዜ ለዓለም ምን ዓይነት ምስክርነት እየሰጠን ነው?
3. ዮሐንስ 15:12: እግዚአብሔር የፈጠረን እርስ በርሳችን እንድንዋደድ ነው፡፡ ይህ እርሱ ለልጆቹ የወጠነው ዕቅድ ስለሆነ፣ ተግባራዊ ማድረጉ የኛ ሥራ ነው፡፡ በቡድናችን ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ሁሉ ልክ እንደ ክርስቶስ ሌሎችን ቢወዱ፣ ምን ያህል እንለወጥ ነበር?

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንደሚሉት፣ የወጣቶች ቡድናችን ምን ዓይነት መሆን አለበት? «ምርጥ» የወጣቶች ቡድን ሊጠቀምባቸው የሚገባቸውን ቃላትና ሐረጎች ዘርዝሩ፡፡ ቡድናችን አሁን ባለበት መልኩ ሲሆን ከሚገባው ደረጃ ምን ያህል ይቀረዋል?

ረ. መዝጊያ

ሁላችንም ለክርስቶስ ለመኖር እርዳታን እንፈልጋለን፡፡ ስለሆነም፣ እርስ በርሳችሁ መረዳዳታችሁ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ይህንንም በተለያዩ መንገዶች ልታከናውኑ ትችላላችሁ፡፡

1. በትምህርት ቤት አብራችሁ ልትሆኑ ትችላላችሁ፡፡ በኅብረት ውስጥ ብርታት እንዳለ አትዘንጉ፡፡
2. እንዳችሁ ለሌላችሁ የቸርነትን ተግባር ልታከናውኑ ትችላላችሁ፡፡
3. ከአፍራሽ ይልቅ ገንቢ ቃላትንና ተግባራትን ልትጠቀሙ ትችላላችሁ፡፡

ኤፌሶን 4:2 እንደሚለው፣ *«በትሕትና ሁሉና በየዋሀት በትዕግሥትም እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ፡፡»* ሌሎች ክርስቲያኖችን የምናስተናግድበት በጣም አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ ምክንያቱም፣

1. አንዳችን ሌላችንን የምናስተናግድበት መንገድ (ትክክለኛ ከሆነ) ዓለማውያን የተለየን ህዝቦች መሆናችንን ይገነዘባሉ፡፡
2. አንዳችን ሌላችንን የምናስተናግድበት መንገድ እያንዳንዱ ሰው ስለራሱ በሚሰማው ስሜት ላይ ለውጥ ያስከትላል፡፡



3. አንዳችን ሌላችንን ስለምናስተናግድበት መንገድ ክርስቶስ ተራ አስተያየት ሳይሆን ጥብቅ ትእዛዝ ሰጥቶናል፡፡ እርሱ የኛ ትክክለኛ ግንኙነት ግድ የሚለው አምላክ ነው፡፡
4. አንዳችን ሌላችንን የምናስተናግድበት መንገድ ክርስቶስን በትክክል መከተላችንን ወይም አለመከተላችንን ለሌሎች የሚያሳይ ምልክት ነው፡፡

ይህን ስብሰባ ከማጠቃለላችን በፊት፣ ሁለት ሁለት እየሆንን ለተወሰነ ጊዜ (ለአንድ ወር፣ ለስድስት ወራት፣ ወዘተ.) አንዳችን ስለሌላችን የቃል ኪዳን ጸሎት እናደርጋለን፡፡ በቀን ውስጥ አንዳችሁ ስለሌላችሁ የምትጸልዩበትን ሰዓት ወስኑ፡፡ ለምሳሌ፣ «እኔ ለአንተ 4:30 ወይም 1:30 ላይ እጸልያለሁ፡፡) ትልቁ ነገር እያንዳንዱ ሰው ከሌላ ሰው የጸሎት ድጋፍ እየተደረገለት መሆኑን ማወቁ ነው፡፡ ክርስቶስ ለርሱ እንድንኖር ጠርቶናል፡፡ እርሱ እንዳደረገው እርስበርሳችን ብንደጋገፍና ብንስተናገድ፣ ክርስቶስ በትክክል የሰዎችን ሕይወት እንደሚለውጥ ለዓለም ልናሳይ እንችላለን፡፡

# እምነትህን ማሳደግ

## ከዳግ ራንያን

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን እምነት ሁሉ ይሰጠናል።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ይህ ትምህርት ወጣቶች እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን እንዲገነዘቡና ቃሉ (በጽሑፍ የሰፈረው፣ በቃል የተነገረውና በሕይወታችን የምንለማመደው) የግላዊ እምነት መሠረት መሆኑን እንዲገነዘቡ ያግዛል።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ወጣቶች አንድን ነገር ከመቀበላቸው በፊት በልምምድ ወይም በስሜት ሕዋሳቶቻቸው አማካኝነት (በመስማት፣ በማየት፣ በመቅመስ፣ በማሽተት፣ በመዳሰስ) ለማወቅ ይፈልጋሉ። ስለሆነም፣ «ነገሩ እንዲህ ነው» ማለት ብቻ ሳይሆን የሚያምኑበትን መሠረት መጣል ያስፈልጋል። በእግዚአብሔር ላይ የሚጣለውም እምነት እንዲሁ ነው። ከልባቸው ለማመን የሚችሉት ከመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል ሲማሩና በሕይወታቸው የመንፈስ ቅዱስን ምስክርነት ሲለማመዱ ነው።
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. መሐረብ።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)

1. ስም የመጥራት ጨዋታ። ይህን ጨዋታ ለማካሄድ የወጣቶቹ ቁጥር ቢበዛ ወይም ቢያንስ ችግር የለውም። ሁኔታው አመቺ ከሆነ ወጣቶቹ በክብ ቅርጽ ይቀመጡ። የመጀመሪያው ልጅ የአንድን ሰው ስም ከነአባቱ ይጠራል። ቀጣዩ ልጅ በሦስት ደቂቃዎች ውስጥ የመጀመሪያው ልጅ በጠራው ሰው አባት ስም የመጀመሪያ ፊደል የሚጀምር ስም እስከነ አባት ይጠራል። (ለምሳሌ፣ የመጀመሪያው ልጅ «ኤልቪስ ፕሬስሊ» የሚል ስም ቢጠራ፣ ሁለተኛው ልጅ «ፕሬይዝ ንደሎሹ» ሊል ይችላል።) በሦስት ሰከንዶች ውስጥ ይህን መርህ በተከተለ መንገድ ስም ለመጥራት ያልቻለ ሰው ከጨዋታ ውጭ ይሆናል። ጊዜ ካለህ አንድ ሰው ብቻ እስኪቀር ድረስ ጨዋታውን ልትቀጥል ትችላለህ። እስከ መጨረሻው ከጨዋታ ውጭ ሳይሆን የቀረው ልጅ አሸናፊ ይሆናል።
2. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው።)

እምነት .. ሁላችንም እምነትን ለማግኘት፣ ለመጠበቅና ለሌሎች አሳልፈን ለመስጠት እንታገላለን። ተራሮችን ስለሚያናውጥና ድልን ስለሚሰጠን እምነት. የሚናገሩትን መዝሙሮች እንዘምራለን። ነገር ግን እንዴት እምነትን ማግኘት፣ መጠበቅና ለሌሎች አሳልፎ መስጠት እንደሚቻል ብዙዎቻችን አናውቅም።

እስኪ የአንድን ወጣት አማኝ እምነት እንመልከት። ቶድ፣ ክሬግና ዴላ ወደ አንድ ቤተክርስቲያን የሚሄዱ ወጣቶች ናቸው። ቶድ ብዙ ጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን ባይመጣም፣ በዛሬው የጉባኤ መዝገያ ላይ ወደ መድረኩ



ወጥቶ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ሰጥቷል። ቶድ ከአዲስ ሕይወቱ ጋር ሲታገል፣ ክሬግና ዴላ ጸሎት ሊያስተምሩት እየሞከሩ ናቸው።

ቶድ ባለፈው ክረምት ወደ ካምፕ ከሄደበት ጊዜ አንሥቶ እንደ ክርስቲያን ሊመላለስ ስላልቻለ፣ በራሱ በቂ እምነት እንደሌለው ተናገረ። በዚህ ጊዜ ክሬግ እምነቱ በእግዚአብሔር እንጂ በራሱ ሊሆን እንደማይገባ ገለጸለት። ቶድ በእግዚአብሔር እንደሚያምንና ነገር ግን እምነቱ ለምን ፈተናን ለመቋቋም እንደማያስችለው አጥብቆ እንደሚያስብ ተናገረ። ዴላ በእምነቱ እንዳደገ እስኪሰማው ድረስ አብረው ሊጸልዩ እንደሚችሉ ተናገረች። ክሬግ ቶድ አዎንታዊ አስተሳሰብን ቢይዝ እምነቱ ሊያድግ እንደሚችል ገለጸለት። ዴላ እጆቻቸውን እያይዘው እያወዛወዙ ቶድ እምነቱ እንደጠነከረ እስኪሰማው ድረስ፣ «እምነት ድል ነው» የሚል መዝሙር እንዲዘምሩ ጠየቀች።

ቶድ ግን ምንም ማድረግ እንዳለበት አላወቀም።

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

1. ክሬግና ዴላ ቶድን ለመርዳት ያደረጉት ጥረት ምን ያህል አጥጋቢ ነበር?
2. ክሬግና ዴላ ለቶድ በሰጧቸው ምክሮች ላይ ተወያዩ።
3. የቶድ ዓይነት ስሜት ተሰምቶህ ያውቃል? ከሆነ፣ ለምን እንዲህ ዓይነት ስሜት እንደተሰማህ አብራራ።
4. ቶድን እያማከርህ ብትሆን ምን ትለዋለህ?
5. ስለ እምነት የሰማሃቸውና ያነበብሃቸው ነገሮች ካሉ ግለጽ።

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)

1. ኤፌሶን 2:8: *«ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና። ይህም የእግዚአብሐሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም።»* በእግዚአብሔር ጸጋ (የኛ ጥረት ያልታከለበት ፍቅር) አማካኝነት እምነት ደኅንነትን ከእጃችን ያስገባዋል። ይህ ደኅንነትና ደኅንነትን የሚያስገኝልን እምነት ሁለቱም ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጡልን ስጦታዎች ናቸው። ልናምን እንችል ዘንድ እምነታችንን የሚሰጠን እግዚአብሔር መሆኑን መረዳቱ ጠቃሚ ነው።
2. ዕብራውያን 11:1: *«እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፣ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።»* ጳውሎስ ዘወር ባለ አገላለጽ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት በእምነታችን ላይ የሚጫወቱትን ጠቃሚ ሚና ማስረዳቱ ነበር። «እርግጠኛ የሆንነባቸው ነገሮች» እግዚአብሔር በቃሉ ይሆናሉ ያላቸው ናቸው። (ለምሳሌ፣ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት።) «ተስፋ» በሚለው ቃል ውስጥ የሚገኘው እርግጠኛ አለመሆን እነዚህ ነገሮች የሚከሰቱበትን ጊዜ በትክክል አለማወቅን ያሳያል። «የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ» የሚለው እምነታችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተጻፉት ነገሮች ላይ (ለምሳሌ፣ የክርስቶስ የዓለም መፈጠር፣ ታላቁ የጥፋት ውኃ፣ የክርስቶስ መወለድ፣ መነሣትና ወደ ሰማይ ማረግ) እንደሚደገፍና በከፊልም የነዚሁ ነገሮች ውጤት እንደሆነ ያሳያል። እምነታችን የእውቀት ምትክ እንዲሆን የታሰበ

ሳይሆን፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት መጀመር የሚገባው ነው። ያለ እግዚአብሔር ቃል እውቀት፣ እውነተኛ እምነት ሊኖር አይችልም።

3. ሮሜ 10፡17፡ *«እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው። መስማትም ከእግዚአብሔር ቃል ነው።»* ጳውሎስ እምነት የክርስቶስን ታሪክ ከመስማትና ለልባችን ለሚናገረው መንፈስ ቅዱስ ምላሽ ከመስጠት እንደሚመጣም ይናገራል።

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች

1. እምነት ማመን ብቻ ነውን?
2. ያለ እምነት መዳን ይቻላልን?
3. የእምነታችን መሠረት መሆን ያለበት ምንድነው?
4. የእምነታችን ማረፊያ ማን መሆን አለበት?
5. እምነትን እንዴት እናገኛለን?
6. እነዚህ ጥቅሶች ስለ እምነት የነበረህን አስተሳሰብ በመጠኑም ቢሆን ለውጠውታልን? ከሆነ፣ እንዴት?

ሰ. መዝጊያ

ሁላችንም ስለ እምነት ጥያቄዎች አሉን። በዚህ ትምህርት እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ፣ ብሎም እምነታችን በእግዚአብሔር፣ በፍቅሩና በኃይሉ ላይ ማረፍ እንዳለበት ተመልክተናል። በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት የምናሳድግባቸው አንዳንድ መንገዶች ከዚህ በታች ተሰጥተዋል።


1. የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ማንበብ፣ ማጥናትና በቃል መያዝ። ጳውሎስ በሮሜ 10፡17 የተናገረውን አስታውስ፡ *«እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው። መስማትም ከእግዚአብሔር ቃል ነው።»* የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ስታነብ፣ ስታጠናና በቃልህ ስትይዝ፣ በእግዚአብሔር ላይ ያለህ እምነት ያድጋል። ይህን ለመጀመር የሚሻለው ክፍል የእምነት ምዕራፍ የሆነው ዕብራውያን 11 ነው። በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ውስጥ እምነት ምን እንደሆነና በሰዎችም ሕይወት ውስጥ ምንን እንደሚያስከትል ትመለከታለህ።
2. መጋቢው የሚያቀርባቸውን ስብከቶች በጽሞና ተከታተል። የማኅበረምእመናንህ መንፈሳዊ መሪ የሆነው መጋቢ፣ አንተን ወደ እግዚአብሔር የሚያስጠጋና በእግዚአብሔር ላይ ያለህን እምነት የሚያሳድግ ስብከት ለማዘጋጀት ብዙ ጊዜ ያጠፋል።
3. መንፈስ ቅዱስ በመጽሐፍ ቅዱስና በሚሰበከው ቃል አማካኝነት ሲመራህ ታዘዘው። ታዛዥነት ምትክ የለውም። እውነተኞቹ የእምነት ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እውነትን በሚገልጥላቸው ጊዜ የሚታዘዙት ናቸው። እግዚአብሔርን ይበልጥ በታዘዝኸው ቁጥር እርሱም እምነትህን ያሳድግልሃል።
4. እምነትህን ተግባራዊ አድርግ። እምነት በተግባር የምትፈጽመው ነገር ነው። እግዚአብሔር ለርሱ የምንኖር የእምነት ሰዎች እንድንሆን ይፈልጋል። እምነት አለህ? ከሆነ፣ በሥራ ቦታ፣ በትምህርት ቤትና በቤት ተጠቀምበት። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መመዘኛዎች ላይ የተመሠረተ ሕይወት ኑር። ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ አንድን የተስፋ ቃል በምታነብበት ጊዜ፣ «ይህ እውነት እንደሆነ አምናለሁ።



ለእኔ የተሰጠኝ የተስፋ ቃል እንደሆነ አምናለሁ። ይህ የተስፋ ቃል እውነት እንደሆነ በማመን እኖራለሁ» በል።

በጸሎት ፈጽም።

ዕብራውያን



11

## የስኬት አባዜ

### ከኤድ ሮቢንሰን

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. የሕይወት ስልትና የሥራ ስኬት በእግዚአብሔር የምርጥነት መመዘኛ የተወሰነ ነው።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች «የስኬታማነትን» ምንነት አውቀው የሕይወትና የሥራ ውሳኔዎቻቸውን እንዲያሳልፉ ለማገዝ።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. አንዳንድ ሰዎች የሌሎችን ሀብት በመመልከት ስኬታማነታቸውን ይናገራሉ። ለአንዳንዶች ስኬት ማለት ከሚፈልጉበት ደረጃ ላይ መድረስ ነው። ዛሬ ለወጣቶች የሚሰጠው ተዘውታሪ ምክር፣ «ልትሆን የምትችለውን ሁሉ ሁን» «የምልዓትን ስሜት የሚፈጥርልህን ነገር አድርግ» የሚል ነው። እነዚህ ነገሮች የተሳሳቱ ባይሆኑም፣ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ካዘጋጀው ዕቅድ ጋር አይስተካከሉም። መመዘኛው ራስን ለእግዚአብሔርና ከዚያም ለሌሎች አሳልፎ መስጠት ነው። ወጣቶች የሕይወት ስልትና የሥራ ውሳኔዎችን በሚያሳልፉበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን የስኬት/የምርጥነት መመዘኛ መጠቀም ይኖርባቸዋል።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)

1. ግርግር። ለዚህ ጨዋታ እኩል አባላት ያሏቸው አራት ቡድኖች ያስፈልጋሉ። ሁሉም ቡድኖች ወደ ክፍሉ አንድ ጥግ ወይም የመጫወቻ ሜዳ ይሄዳሉ። ምልክት በሚሰጥበት ጊዜ እያንዳንዱ ቡድን አባላቱን ሳይነጣጥል የታዘዘውን እንቅስቃሴ እያደረገ በተቻለው ፍጥነት ዝግዛግ (ሰያፍ) እየሠራ ወደ ተቃራኒ ጥግ ይሄዳል። ሁሉም አባሎቹ ቀድመው ወደዚያኛው ጥግ የደረሱለት ቡድን የዙሩ አሸናፊ ይሆናል። የመጀመሪያው ዙር ወደዚያኛው ጥግ ዝም ብሎ ሩጦ መድረስ ሊሆን ይችላል። ከዚያ በኋላ እንደ ወደኋላ መራመድ፣ ሌሎችን ከጀርባ ላይ አዝሎ መሄድ፣ እንደ እንቁራሪት መዝለል፣ ያሉትን እንቅስቃሴዎች ሊያደርጉ ይችላሉ። ከክፍሉ መሀል ላይ ቡድኖቹ ሌሎቹን ቡድኖች አቋርጠው ለማለፍና አሸናፊ ለመሆን በሚሞክሩበት ጊዜ ከፍተኛ ግርግር እንደሚፈጠር ግልጽ ነው።
2. የዓረፍተነገር ውድድር። እንደ ወጣቶችህ ቁጥር መጠን፣ ሁሉም ወይም የተወሰኑት ብቻ ይህንን ጨዋታ ሊያካሂዱ ይችላሉ።



የሚከተሉትን ሐረጎች በጥቁር ሰሌዳ ወይም በማጣበቂያ ቻርት ላይ ጻፍ።

- ገንዘብ እንደ ልብ ቢኖረኝ ኖሮ፣ ነገ ሄጄ.————————እገዛ ነበር።
- የምፈልገውን መሆን ብችል ኖሮ፣————————እሆን ነበር።

እያንዳንዱ ሰው ዓረፍተነገሩን አሟልቶ እንዲጨርስ አድርግ። ከነዚህ ምላሾች አንዳንዶቹ አስቂኝ፣ አስገራሚ ወይም ስሜት የማይሰጡ ይሆናሉ።

3. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው።)

ለብዙዎቻችን ስኬትና ምርጥነት አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። ብዙ ሰዎች ስኬትን የሚዳኙት በገንዘብ፣ በሥልጣንና በሀብት ላይ በመመርኮዝ ነው። አንድ ሰው በሥራ ቦታው እድገት ሲያገኝ፣ በትምህርት ከክፍሉ ቀዳሚውን ስፍራ ሲይዝ፣ አዲስ መኪና መግዛት ሲችል ተሳክቶለታል እንላለን። ነገር ግን፣ «የስኬትንና የምርጥነትን መመዘኛዎች የሚወስነው ማነው? መገናኛ ብዙሐን ነው? ባሕላችን? የኅብረተሰቡ ውሳኔዎች? ለአንዱ ዝቅተኛ የሆነው ነገር ለሌላ ምርጥ ሊሆን ይችል ይሆን?» እንደ ክርስቲያኖች፣ የስኬታማነት መስፈርታችን የእግዚአብሔር የምርጥነት መመዘኛ (ፍጹምነት እያልን አለመሆኑን አጢን) ሊሆን ይገባል።

እስኪ የትሼፖን ምሳሌ እንመልከት። ትሼፖ በቅርቡ ከሕግ ትምህርት ቤት የተመረቀ ክርስቲያን ነው። የተመረቀው በጥሩ ውጤት በመሆኑ፣ የተለያዩ የሕግ ድርጅቶች ሊቀጥሩት እንደሚፈልጉ ገልጸውለታል። ከነዚህ ድርጅቶች አንዱ ባመዛኙ ከትላልቅ ኮርፖሬሽኖች ጋር የሚሠራና ከፍተኛ ደመወዝ የሚከፍል ነው። ሁለተኛ ከሕዝባዊ ጉዳዮች ጋር የሚሠራና መጠነኛ ደመወዝ የሚከፍል ድርጅት ነው። ሦስተኛው በቀዳሚነት ከድሆች ጋር የሚገናኝ የሕዝባዊ መብቶች ጠባቂዎች ቢሮ ነው። ትሼፖ የትኛውን ሥራ እንደሚመርጥ መወሰን አለበት። እያንዳንዱ ሥራ የየራሱ ጥቅማጥቅሞችና እሴቶች አሉት። ትሼፖ «ስኬታማ» የሕግ ባለሙያ ለመሆንና ምርጥ ተግባር ለማከናወን ይፈልጋል።

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ ...

1. ለትሼፖ ምክር የምትሰጥ ቢሆን ምን ትለዋለህ?
2. የመጀመሪያውን፣ ሁለተኛውን ወይም ሦስተኛውን ሥራ ሊወስድ ይገባል የምትላቸውን አንዳንድ ጥሩ ምክንያቶች ልትዘረዝር ትችላለህ?

3. ትሼፖ ለየትኛው ድርጅት እንደሚሠራ ከመወሰኑ በፊት ሊያነሣቸው የሚገባቸው ጥያቄዎች ምን ምንድናቸው?
4. በራስህ አመለካከት፣ ትሼፖ የትኛውንም ሥራ መምረጡ ችግር ይኖረዋል? ለምን?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)

1. 1ኛ ጢሞቴዎስ 6:17-19: ጳውሎስ ሀብት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የስኬት መመዘኛ እንዳልሆነ ያስረዳል። የስኬታማ ክርስቲያንነት መመዘኛዎች ግን መልካም ምግባራት፣ ልግስና፣ ራስንና የራስ የሆነውን ሁሉ አሳልፎ መስጠትን የሚጠይቁ ናቸው። ትሼፖ ውሳኔውን በገንዘብ ላይ ከመሠረተ ትልቅ ስሕተት መሥራቱ ነው።
2. ማርቆስ 10:42-45: በሌሎች ሰዎች ላይ ተረማምዶ ከጫፍ ላይ መድረስ የእግዚአብሔር አሳብ አይደለም። እንዲያውም እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቱ የስኬታማነት አሳብ ከቶ እንደሆነ ያስረዳል። (ያዕቆብ 5ን አንብብ።) ክርስቶስ ስኬታማ ክርስቲያን ከሁሉም በላቀ ሁኔታ የሚያገለግል እንደሆነ ያስተምራል። ትሼፖ ሊያነሣ ከሚገባቸው ጥያቄዎች አንዱ፣ «የሚገባኝን ያህል እንዳገለግል የሚያስችለኝ የትኛው ስፍራ ነው?» የሚል ይሆናል። ይህ እያንዳንዱ ክርስቲያን ራሱን ሊጠይቅ የሚገባው ጥያቄ ነው።
3. ማቴዎስ 25:19-21: በዚህ ምሳሌ ውስጥ ወሳኙ ጉዳይ የመክሊቱ ብዛት አይደለም። ምክንያቱም ጌታው አራት መክሊት ላለውም ባሪያ ተመሳሳይ ሙገሳ ሰጥቷል። በዚህ ዓውድ ውስጥ የስኬታማነት ምሥጢሩ ስጦታዎቻችንን የምንጠቀምበት መንገድ ነው። የባሪያዎቹ ስኬታማነት የሚለካው የተሰጣቸውን መክሊት ተጠቅመው ለጌታቸው ከፍተኛ ትርፍ በማምጣታቸው ነበር። ከባሮቹ አንዱ ተነሳሽነት የጎደለው በመሆኑ ምክንያት በተሰጠው መክሊት ስላልነገደበት ተቀባይነትን ሳያገኝ ቀርቷል። በአንዷ መክሊት ነግዶ ሁለት አድርጓት ቢሆን ኖሮ እንደ ሌሎቹ ሁሉ ሊመሰገን ይችል ነበር።

ከእግዚአብሔር የስኬት መመዘኛዎች አንዱ እርሱ የሰጠንን ነገር ለራሳችን ጥቅም ሳይሆን ለመንግሥቱ በሚገባ መጠቀማችን ነው። ምናልባትም ትሼፖ፣ «እግዚአብሔር የሰጠኝን ችሎታ በየትኛው ሥራ ላይ ልጠቀምበት ይገባኛል?» የሚል ጥያቄ ለራሱ ሊያቀርብ ይገባል።

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)



1. ከነዚህና ከምታስታውሳቸው ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፣ ለራስህ ሥራና የአኗኗር ስልት በምትመርጥበት ጊዜ ምን ዓይነት የስኬት መመዘኛዎችን ትከተላለህ?
2. የእግዚአብሔርን የስኬት መመዘኛዎች እንዳንጠቀም የሚከለክሉን ነገሮች ምን ምንድናቸው? የዕድሜ እኩዮቻችን የሚያደርሱብን ጫና? የገንዘብና ገንዘብ ሊገዛ የሚችላቸው ነገሮች ፍቅር? ዋስትና የማግኘት ፍላጎት? እለቃ የመሆን ፍላጎት?
3. ስለምትሰማራበት የሥራ መስክ አስበህ ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የስኬት መመዘኛዎች አሳብህን ለወጡት ወይስ አጠናከሩት? እንዴት?
4. ከነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንጻር፣ ትሼፖ ምን ሊወስን ይገባዋል?

ሰ. መዝጊያ

ስለምንሰማራበት የሥራ መስክና የአኗኗር ስልታችን የምንሰጣቸው ውሳኔዎች ሁለት እጅግ ወሳኝ ምርጫዎች ናቸው። እነዚህ ነገሮች ሕይወታችንን የምናሳልፍበትን ስፍራና ሁኔታ የሚወስኑ ናቸው። እንደዚህ ዓይነት ውሳኔዎች በጥልቅ ማሰብን የሚጠይቁ ናቸው። የዕድሜ እኩዮቻችን፣ መገናኛ ብዙኃንና ባሕል የሚያተኩሩበትን የስኬት ፈለግ በመከተል ውሳኔዎቻችንን ለማሳለፍ ልንፈተን እንችላለን። ውዳቂ ለመሆን የሚፈልግ ማንም እንደሌለ ግልጽ ነው። ሁላችንም ስኬታማዎች ለመሆን እንሻለን። ነገር ግን ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፣ እነዚህን ታላላቅ ውሳኔዎች በምንመርጥበት ጊዜ የእግዚአብሔርን የስኬት መመዘኛዎች ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባታችን ፍጹም ወሳኝ ጉዳይ ነው። ይህንኑ ለማድረግ ልንከተላቸው የሚገባ አንዳንድ ጠቃሚ መምሪያዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

1. እግዚአብሔር ስኬታማነትን የሚለካው ሥራውን እንድናከናውን የሰጠንን ስጦታዎች መጠቀማችንንና ምሪቱን መከተላችንን በመመልከት ነው። ቀዳሚው ዓላማችን የእግዚአብሔርን መንግሥት መገንባት ነው። ይህም በዓለም ውስጥ ለውጥ ማስከተልን የሚጨምር ነው።
2. ስኬት እጅግ ኃያል በመሆናችን አይወሰንም። ክርስቶስ ባሪያ እጅግ ስኬታማ ሊሆን እንደሚችል ገልጾአል። የስኬታችን የመለኪያ ዘንግ ሌሎችን በምናገለግልበት ጊዜ የሚታየው የሕይወታችን የኢንቬስትመንት ደረጃ ነው።
3. ገንዘብ ወይም ሀብት ስኬታማ አያደርገንም። ስኬት የሚገኘው ከመልካም ተግባር ብልጽግናና ከልግስና መንፈስ ነው።

ከነዚህ መምሪያዎች አንጻር፣ «ስኬታማ» ነው ብላችሁ የምታስቡት ሰው ይኖራል? የዚህ ሰው የሕይወቱ መለያ ባሕርያት ምን

ምንድናቸው? ይህንን ሰው ለራሳችሁ ሕይወት በምሳሌነት ልትጠቀሙ ትችላላችሁ? ይህ ማለት ለምሳሌነት የመረጣችሁት ሰው የሚሠራውን የሥራ ዓይነት ለመተዳደሪያነት ትመርጣላችሁ ማለት አይደለም። ነገር ግን እሱ የተጠቀማቸውን የስኬት መመዘኛዎች ትጠቀማላችሁ። በሕይወት ጎዳና ላይ የምንረማመድ ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፣ በእግዚአብሔር መመዘኛ ምርጥ መንገዶች ልንመላለስ ይገባል።

በጸሎት ፈጽም።



## ሱስ አስያዥ ዕፆች፡ መጠቀም ወይም መተው

ከማርክ ጊልሮይ

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. ሱስ አስያዥ ዕፆች ጎጂዎች ስለሆኑ መወገድ አለባቸው።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች ዕፆችን ላለመጠቀም ቁርጥ አቋም እንዲወስዱና በአቋማቸው ጸንተው የሚኖሩባቸውን ስልቶች እንዲነድፉ ለማገዝ።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ወጣቶችህ ዕፆችን መጠቀም ምን ያህል ጎጂና አውዳሚ እንደሆነ ያውቃሉ? ምናልባት ያውቁ ይሆናል! ብዙዎች ስለ ዕፅ ብዙም ግንዛቤ የላቸውም። ስለሆነም፣ የዕፅን ጉዳይ ቸል ብለው የሚተው ይመስላችኋል? በጭራሽ! ለምሳሌ ያህል፣ አንዳንድ ወጣቶች የአልኮል መጠጦችን መውሰድ ለጤናቸው ጎጂ እንደሆነ ቢያውቁም ከመጠጣት አይታቀቡም። ያንተ ተግባር ስለ ዕፅ ከተራ ሐቆች ያለፈ ማረጋገጫ ማቅረብና ወጣቶች ለምን ዕፅ እንደሚወስዱ ከቡድንህ አባላት ጋር መወያየት ይሆናል። ከዚህ በመነሣት ወጣቶችህ ዕፆችን ሳለመውሰድ ቁርጥ አቋም የሚወስዱባቸውን መንገዶች አብረሃቸው ልትወጥን ትችላለህ።
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. እርሳሶች፣ ወረቀትና የወረቀት ማያያዣ።

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)

1. ምሥጢራዊ ስሞች። ሁለት ወረቀቶች፣ እርሳስና ማያያዣ ለሁሉም ወጣቶች አድል። ለራሳቸው የምሥጢር ስም እንዲያዘጋጁ ጠይቃቸው። ማንም ሳያያቸው ይህንን ከአንደኛው ወረቀት ላይ ይጻፉ። ከዚያም ሁሉም ወጣቶች ወደ ግድግዳው ጥግ በመሄድ ምሥጢራዊ ስሞቻቸውን ከጀርባቸው ላይ ከለጠፉ በኋላ ጀርባቸውን ወደ ግድግዳው አዙረው እንዲቆሙ አድርግ። ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ ሁሉም ወጣቶች በክፍሉ ውስጥ በመዘዋወር ሊያዩ የሚችሏቸውን ምሥጢራዊ ስሞች ሁሉ ይጽፋሉ። ይህንንም የሚያደርጉት ከጀርባቸው ላይ ያለው የራሳቸው ምሥጢራዊ ስም ለሌሎች እንዳይታይ በመጠንቀቅ ይሆናል። ሁለት ደቂቃዎችን ያህል ስጣቸውና በዚህ ጊዜ ውስጥ ማን ብዙ ስሞችን ሊጽፍ እንደቻለ እይ።
2. የዓይነስውራን ስልፍ። ቡድንህን በፍጥነት በሁለት ወይም ከዚያ በሚበልጡ ቡድኖች ከፋፍል። ይህን ጨዋታ ለማካሄድ በአንድ ቡድን ውስጥ ቢያንስ አራት አባላት ሊኖሩህ ይገባል። በቡድኖች

ከከፋፈልሃቸው በኋላ ወጣቶቹ ዓይኖቻቸውን እንዲጨፍኑ ጠይቃቸው። «አጮልቆ ማየት አይቻልም!» እያልህ ደጋግመህ ንገራቸው። ምንም ድምጽ ሳያሰሙ በቁመታቸው ቅደምተከተል (አጫጭሮች ፊት፣ ረዣዥሞች ኋላ) እንዲሰለፉ ንገራቸው! ቡድኖቹ ሰልፋቸውን ያጠናቀቁ ሲመስላቸው «ተሰልፈናል!» እንዲሉ ንገራቸው። «ተሰልፈናል» ያለው ቡድን አባላት በትክክል በቁመታቸው ልክ ካልገቡ ሌሎቹ ቡድኖች ሰልፋቸውን ማስተካከላቸውን እንዲቀጥሉ ንገራቸው። ከሌሎች አስቀድሞ *በቁመት ተራ* ለመሰለፍ የቻለ ቡድን የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል።

3. አማራጭ ማስተማሪያ። በቤተክርስቲያንህ ውስጥ ፖሊስ ወይም ስለ ዕፆች የሚያውቅ ሰው ካለ፣ ስለ ጉዳዩ ማብራሪያ በመስጠት ለዚህ ትምህርት እገዛ እንዲያደርግ ጋብዘው።
4. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. የመወያያ ጥያቄዎች (*መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው* አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

1. ሱስ አስያዥ ዕፆች በትምህርት ቤትህ ችግር እየፈጠሩ ናቸውን? ከሆነ፣ ወጣቶቹ የሚጠቀሙባቸው ዋና ዋና ዕፆች የትኞቹ ናቸው?
2. ሰዎች ሱስ አስያዥ ዕፆችን ይጠቀማሉ? *(ለዚህ ጥያቄ ከወጣቶቹ መልሶችን ተቀበል። ከወላጆቻቸው ጋር ስለማይስማሙ፣ ወዘተ. የሚሉትን ምክንያቶች እንዲነግሩህ ጥያቄህን ወደነዚህ አቅጣጫዎች ምራ።)*
3. በሌላ በኩል፣ ሰዎች ሱስ አስያዥ ዕፆችን የማይጠቀሙባቸው ምክንያቶች ምን ምንድናቸው?

*መ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች*

አብዛኞቹ ዕፆችን አላግባብ የመጠቀም ሁኔታዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀሱም። የአልኮል መጠጦች ጉዳይ ግን በብዙ ቦታዎች ላይ ተጠቅሷል። እስኪ እነዚህን ምንባቦች በመመልከት ለሕይወታችን ጠቃሚ የሆኑትን *መርሆች* እንምዘዝ።

1. ምሳሌ 232:29-35: እዚህ ላይ አሳሳቢ ሆኖ የቀረበው ጉዳይ ከፍተኛ አስካሪ እንዲሆን ተደርጎ የሚዘጋጀው «የተደባለቀ የወይን ጠጅ» ነው። በቁጥር 33 እና 34 ውስጥ የተሣለውን ምስል በዓይነሕሊናህ ተመልከት። ገለጻው ከብዙዎቹ የሱስ አስያዥ ዕፆች ተጠቃሚዎች ጋር የሚመሳሰል ነው።
2. ገላትያ 5:19-23: ከዚህ ክፍል ሦስት ቃላት ማጤን አለብን። *ስካር* የኃጢአት ተፈጥሮ አካል በመሆኑ በክርስትና ሕይወት ውስጥ ተቀባይነት እንደሌለው ግልጽ ነው። እርኩሰት ብዙውን ጊዜ የወሲብ ኃጢአቶችን *ያመለክታል*። ይሁንና፣ የዚህ ችግር



*ሥሩ ያልተገታ ራስን የማርካት* ፍላጎት ነው። ፓርቲ የመጨፈር ዓይነት ፍላጎት። እነዚህ ሁለቱ በቁጥር 23 ከተገለጸው ራስን ከመግዛት ጋር ይቃረናሉ።

3. ኤፌሶን 5:15-18: የዚህ ክፍል ዋና አሳብ በነዚህ ክፉና አደገኛ ቀናት ውስጥ አስተዋይና ጠንቃቃ ሆኖ መኖር አስፈላጊ መሆኑን መግለጽ ነው። ጠንቃቃ መሆን ከሚቻልባቸው ነገሮች አንዱ አልኮል ጠጥቶ አለመስከር መሆኑ ተገልጾአል።

*ሠ. የውይይት መነሻዎች*

ከዚህ በታች በእውነተኛ ገጠመኞች ላይ የተመሠረቱ አምስት ታሪኮች ቀርበዋል። እያንዳንዱ ምሳሌ ካነበብህ በኋላ ተማሪዎችህ ምን ዓይነት የመፍትሔ አሳቦችን እንደሚያቀርቡ ጠይቃቸው። የክፍልህ ተማሪዎች በጭውውት መልክ የሚቀርቡትን ሁኔታዎች መመልከት የሚወዱ ከሆነ፣ ከክፍለጊዜው በፊት ለየምሳሌዎቹ ሁለት ሁለት ልጆችን መድብና በጭውውት መልክ ያቅርቡት።

1. ታናሽ እህትህ (ዕድሜዋ 11 ዓመት) ከጓደኛዋ ቤት ሄዳ ባደረች ጊዜ ከሦስት ጓደኞቿ ጋር በመሆን አልኮል እንደጠጡ ትነግርሃለች። መጠጡን በምትወስድበት ጊዜ ጥሩ ስሜት እንደተሰማትና ጠዋት ግን ሁኔታው እንዳንገሸገሻት ጨምራ ትነግርሃለች። በአካላዊ ሰውነቷም ሆነ በጥፋተኝነት ስሜት ክፉኛ ተሠቃይታ ነበር።
2. ትልቅ የአትሌቲክስ ችሎታ ያለው ጓደኛህ በአንድ የጨዋታ ውድድር ላይ አራት ስሕተቶችን ይሠራል። ወትሮ በጣም ጥሩ ስፖርተኛ ስለነበር፣ የሆነውን ሁኔታ ማንም አላመነም። በኋላ ግን አያሌ ሰዎች ምን ሲያደርግ እንደነበረ እየቀለዱ ሲነጋገሩ ትሰማለህ። ልጁ አንዳንድ ጊዜ ወደ ቤተክርስቲያን ቢመጣም፣ ያን ያህል ተሳታፊ አልነበረም።
3. አንዲት አዲስ ልጅ ከሌላ ቦታ መጥታ ወደዚሁ የወጣቶች ቡድን መምጣት ትጀምራለች። ልጅቱ ኃፍረት ስለሚሰማት ይህን ያህል ተሳትፎ አታደርግም። ሱስ አስያዥ ዕፆችን ትውሰድ አትውሰድ የምታውቀው ነገር የለም። ነገር ግን በትምህርት ቤት ይህንኑ ከሚያደርጉት ልጆች ጋር አብራ ትታያለች።
4. ጓደኛህ ብዙውን ጊዜ ቤት ውስጥ ብቻውን እንዲውል ይደረጋል። ልጁ ጥሩ ባሕርይ የነበረው ቢሆንም፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ «ለጨዋታ ያህል» ዕፆችን መውሰድ ጀምሯል። ከዚህ በፊት ራሱን ችግር ውስጥ እየዘፈቀ መሆኑን ብትነግረውም፣ «ወላጆቼ ፖሊስ እስካልደረሰብህ ድረስ ምንም ችግር የለውም ብለውኛል» ሲል መልሶልሃል።
5. አብራችሁ የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎችህ ከነበራችሁበት ጊዜ አንሥቶ ልጅቱ ጥሩ ጓደኛህ ነበረች። በቅርቡ 16 ዓመት

ከምላት በኋላ በወላጆቿ ላይ የማመፅና ከቤተክርስቲያን የመራቅ ምልክቶችን በማሳየት ላይ ትገኛለች። «እስኪ፣ ሐሺሽ እናጭስ፣ ቤንዚን እንሳብ ወይም ለአንድ ጊዜ ብቻ የሆነ ነገር እናድርግ። እስካሁን ምንም አስደሳች ነገር አድርገን ስለማናውቅ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚፈጥር ለማወቅ እፈልጋለሁ» ትልሃለች።

ሰ. *መዝጊያ*

1. *ፖስተሮች* .. የዛሬውን ትምህርት በፍጥነት ከልስ። *ሱስ አስያዥ ዕፆች ጎጂዎች ስለሆኑ መወገድ* አለባቸው በሚለው የትምህርቱ ትኩረት ላይ አጽንኦት ስጥ። አሁን ደግሞ ለእያንዳንዱ ቡድን ወይም ለእያንዳንዱ አነስተኛ ቡድን አንዳንድ ፖስተር ወይም ወረቀት አድል። ተማሪዎችህ ወጣቶች ከሱስ አስያዥ ዕፆች እንዲርቁ ያሳምኗቸዋል ያሏቸውን ማስታወቂያዎች ወይም መፈክሮች አዘጋጅተው በፖስተሮቹ ላይ ይጻፉ። ወጣቶች ዕፆችን ስለሚጠቀሙባቸውና ስለማይጠቀሙባቸው ምክንያቶች የተወያያችኋቸውን ነጥቦች አስታውሳቸው። የወጣቶቹን የሥራ መንፈስ ለማነሣሣት ያህል፣ ይህን እንቅስቃሴ በውድድር መልክ ልታዘጋጅና አሸናፊ የሆነው ፖስተር ሽልማት ከማግኘቱም በላይ በቤተክርስቲያን ግድግዳ ላይ እንዲሰቀል ልታደርግ ትችላለህ። ወይም ደግሞ ሁሉንም ፖስተሮች በክፍላችሁ ግድግዳ ላይ መስቀል ይቻላል። በቂ ጊዜ ከሌላችሁ፣ ተማሪዎቹ ፖስተሮቹን ወደ ቤታቸው ወስደው እንዲሠሩና በሚቀጥለው ሳምንት ይዘው እንዲመጡ ልታደርግ ትችላለህ።
2. የግል አስተያየት .. ተማሪዎችህ ዓይኖቻቸውን ጨፍነው ራሶቻቸውን ዝቅ እንዲያደርጉ ጠይቃቸው። ከዚያም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይቃቸው።
   ሀ. ወጣቶች ሱስ አስያዥ ዕፆችን የሚወስዱባቸውን ምክንያቶች በዝርዝር ተመልክተናል። ከዚያ ዝርዝር ውስጥ አንተን ለዕፅ ሊያጋልጥ የሚችል ሁኔታ አለን?

   ለ. ለዕፅ አጠቃቀም እንዳትጋለጥ ምን ማድረግ ይኖርብሃል? ወይስ እንዴት እርዳታ ልታገኝ ትችላለህ?
   ለዕፅ ምላሽ መስጠት የሚቻልባቸው ሦስት መንገዶች አሉ። ዕፅን ልትጠቀም፣ አላግባብ ልትገለገል ወይም ከመጠቀም ልትቆጠብ ትችላለህ። አንዳንድ ሰዎች አላግባብ ወደመገልገሉ ሳትሸጋገር ልትጠቀም እንደምትችል ይናገራሉ። ነገር ግን ከሁሉም የሚሻለው አማራጭ አለመጠቀም ነው። ዕፆችን ላለመጠቀም ቁርጥ ውሳኔ ለማድረግ ፈቃደኛ ነህን? ከሆነ፣ ይህን ብቻህን ማድረግ የለብህም። እግዚአብሔርን ኃይልን ይሰጥሃል። አሁኑኑ ስለዚሁ ጉዳይ ንገረው።



3. የመጨረሻ ድጋፍ .. ይኸው የጸሎት ዝንባሌ እንዲቀጥል አድርግ። ተማሪዎችህ ከዕፆች ፈተና ጋር የሚታገሉ ከሆነ፣ ልታነጋግራቸው እንደምትፈልግና ጊዜህን ችግራቸውን ለመቅረፉ ተግባር እንደምታውል ግለጽላቸው። ከቤተክርስቲያንህ ውስጥ ከዕፆች ጋር በተያያዘ ችግር ያለባቸውን ልጆች ለመርዳት የሚችሉትንና የሚፈልጉትን ሌሎች ሰዎችም ስም ንገራቸው። (ስማቸውን ለተማሪዎች ከመናገርህ በፊት ሰዎቹ ልጆቹን ለመርዳት ፈቃደኛ መሆናቸውን አረጋግጥ።) ከዚያም ጠቅላላውን ቡድን ለመደገፍ ፈቃደኛ የሆኑና በዕፅ አጠቃቀም ላይ አምንታዊ የዕድሜ እኩዮች ጫና ለማሳደር ራሳቸውን የሰጡ ተማሪዎች ወደፊት መጥተው ከአንተ ጋር እጅ ለእጅ እንዲያያዙ ጠይቃቸው። «በአንድነት... እናደርገውም!» የሚል አሳብ በወረቀት ላይ ጻፍና ፈቃደኛ የሆኑ ወጣቶች ፊርማቸውን እንዲያኖሩበት አድርግ።

ተጨማሪ ሥራዎች። ተጨማሪ ሥራ ለመሥራት የሚፈልጉ ወጣቶች ካሉህ፣ ከልጆች የሰንበት ትምህርት መምህር ጋር በመነጋገር ጥቂት ወጣቶች ለቤተክርስቲያንህ ልጆች ስለ ሱስ አስያዥ ዕፆች እንዲያስተምሩ ልታደርግ ትችላለህ። አጫጭር የአምስት ደቂቃ ትምህርቶችንና የመርጃ መሣሪያዎችን በማዘጋጀቱ ረገድ ወጣቶቹን መርዳት ይኖርብሃል። ትምህርቱ በእሑድ ጠዋት ወይም እሑድ ምሽት አምልኮ ላይ ሊቀርብ ይችላል። በመጨረሻም፣ ይህ የአንድ ጊዜ ትምህርት ብቻ ሳይሆን ክትትል የሚያስፈልገው መሆኑን አስታውስ።

## ዛሬ ዘላለም አይደለም

### ከራንዲ ክራከር

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. ወጣቶች የሕይወት ችግሮች ለዘላለም እንደማይኖሩና ራስን ማጥፋት ችግሮቻቸውን ለማስወገድ ተገቢ መፍትሔ እንዳልሆነ መገንዘብ ይኖርባቸዋል::
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች ራስን ስለማጥፋት አውቀው ይህንኑ ለማድረግ የሚያስቡትን ሰዎች እንዲረዱ ለማበረታታትና ከቡድኑ አባላት መካከል ለችግሮቻቸው መፍትሔ ለመሻት የሚጥሩትን ወጣቶች ለማገዝ::
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. በብዙ አገሮች ወጣቶች የሚሞቱት በቀዳሚነት ራሳቸውን በማጥፋት ነው:: ይህ ብዙውን ጊዜ በማኅበረሰባችን፣ በትምህርት ቤታችን ወይም በቤተክርስቲያናችን ውስጥ እስኪከሰት ድረስ ትኩረት የማይሰጠው ችግር ነው:: ራስን ማጥፋት የሚያስከትለውን ኃዘን ማስወገድ ይቻል ዘንድ ቀድሞውኑ ስለዚሁ ችግር መወያየቱ ጠቃሚ ነው:: የማኅበረሰቦቻችን ችግሮች የተወሳሰቡ ከመሆናቸው የተነሣ አንዳንድ ወጣቶች ሕይወት ልንኖር የሚገባት ወይም የወደፊቱን መልካም ሕይወት ተስፋ ማድረጉ ተገቢ ነው ወይ? ሲሉ ይጠይቃሉ::
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. መጽሐፍ ቅዱሶች፣ ወረቀት፣ እርሳሶች፣ ሁለት ቦርሳዎች::

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (እነዚህ እያንዳንዳቸው እንቅስቃሴዎች ወጣቶቹ አብረው እንዲጫወቱ የሚያግዙ ናቸው:: ነገር ግን በእያንዳንዱ ጨዋታ ወቅት አንድ ሰው ገለልተኛ እንዲሆን ይደረጋል:: ትምህርቱ ከመጠናቀቁ በፊት ገለልተኛ የተደረጉት ልጆች ገለልተኛ በተደረጉበት ሰዓት ምን ዓይነት ስሜት እንደተሰማቸው ያካፍሉናል:: ይህም በዓለም ውስጥ አንዳንድ ወጣቶች እንዴት የስሜት መጎዳት እንደሚደርስባቸው በጨረፍታ ለመመልከት ያስችለናል::)

1. ጓደኛውን ያጣ እንስሳ:: የእያንዳንዱን እንስሳ ስም በሁለት የተለያዩ ወረቀቶች ላይ ጻፍ:: ከዚያም በአንድ ወረቀት ላይ «ዳክዬ» የሚል ስም ጻፍ:: ለሁሉም ተማሪዎች የጻፍሃቸውን ወረቀቶች አድል:: ከዳክዬ በስተቀር ሁሉም እንስሳት በሁለት ሁለት ወረቀቶች ላይ መጻፋቸውን አረጋግጥ:: ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ ተማሪዎቹ ባገኙት ወረቀት ላይ የተጻፈውን እንስሳ ድምጽ በማሰማት ጓደኞቻቸውን ለማግኘት ይሞክራሉ:: ባገኟቸውም ጊዜ አብረዋቸው ከወለል ላይ ይቀመጣሉ:: «ዳክዬ» የተጻፈበትን ወረቀት ያገኘው ልጅ ግን ጓደኛውን ሳያገኝ በዳክዬ ድምጽ እየጮኸ መፈለጉን ይቀጥላል::
2. ለየት ያሉ ነገሮችን የማድረግ ውድድር:: ሁለት ሰዎች ወጣቶቹን በሁለት ቡድኖች እንዲያከፋፍሉ አድርግ:: ከክፍለጊዜው ቀደም ብሎ መጀመሪያ ሊመረጡ የሚችሉትን ልጆች ወደ መጨረሻ፣ በመጨረሻው ላይ ሊመረጡ የሚችሉትን በቀዳሚነት እንዲመርጡ ፍንጭ ስጣቸው:: እነዚህ ሁለት ቡድኖች ለየት ያሉ ነገሮችን የሚካሄድ ውድድሮችን እንዲያከናውኑ አድርግ:: ሁለት ቦርሳዎችን በመውሰድ ለየት ያሉ አስቂኝ ነገሮችን ጽፈህ አስቀምጥባቸው:: *(እነዚህ ለየት ያሉ አስቂኝ ነገሮች ጸጉሩን የተላጨ ሰው ራስ ማከክ፣ በወለል ላይ እግርን አጣምሮ በመቀመጥ መዝሙር መዘመር፣ ጫማ አውልቆ የቀኙን ለግራ የግራውን ለቀኝ ማድረግ፣ አራቱንም የክፍሉን ጥጎች (ኮርነሮች) እየዞሩ መንካት፣ ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ::)* አስቂኝ ነገሮችን በወረቀቶች ላይ በመጻፍ በቦርሳዎቹ ውስጥ አኑር:: በሁለቱም ቦርሳዎች አንድ ዓይነት ነገሮች ጽፈህ ማስቀመጥ እንዳለብህ አትርሳ:: «በዚህ ጨዋታ ውስጥ አትሳተፍ:: የሆነ ቦታ ሄደህ ተቀመጥ» የሚል ትእዛዝ የተጻፈባቸውን ሁለት ወረቀቶች በሁለቱም ቦርሳዎች ውስጥ ጨምር:: (አንድ ወረቀት በአንድ ቦርሳ ውስጥ::) ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ፣ ከየቡድኑ የመጀመሪያው ልጅ ቦርሳውን ከፍቶ አንድ ወረቀት ይወስድና በወረቀቱ ላይ የተጻፈውን ተግባር ይፈጽማል:: እሱ የተባለውን አከናውኖ ሲጨርስ፣ ቀጣዩ ልጅ ሌላ ወረቀት መዞ በማውጣት በወረቀቱ ላይ የሰፈረውን ትእዛዝ ይፈጽማል:: ጨዋታው እንዲህ እያለ ይቀጥላል:: በቦርሳው ውስጥ የሚገኙ ወረቀቶች የሚሰጧቸውን ትእዛዛት በቀዳሚነት አከናውኖ የሚጨርስ ቡድን የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል::
3. የቡድን ዝማሬ:: የቡድኑን አንድነት የሚያጠናክሩ መዝሙሮችን ዘምሩ::

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው::)

ሕይወት ልንኖር የሚገባት አይደለችም ብለው የሚያስቡ ብዙ ሰዎች አሉ:: በቤትና በትምህርት ቤት ብዙ ችግሮችን ስለሚጋፈጡ፣ ወደፊት ከዚህ የተሻለ ነገር ላናይ እንችላለን ብለው ይፈራሉ:: ስለሆነም፣ «ከዚህ ሁሉ ሞቼ ብገላገል ይሻለኛል» ብለው ያስባሉ:: ዛሬ ራስን ስለማጥፋት እንነጋገራለን:: ይህም ለችግሮቻቸው ራስን ማጥፋት መፍትሔ እንደሚሆን የሚያስቡትን ጓደኞቻችንን ለመርዳት ያስችለናል:: እስኪ ራስን ስለማጥፋት ምን ያህል እንደምታውቅ ለመረዳት በሚያግዙ የእውነት/ውሸት ጥያቄዎች እንጀምር::

1. በብዙ አገሮች ለወጣቶች ሞት ምክንያት የሚሆነው ቀዳሚ ችግር ራስን ማጥፋት ነው::
2. ራሳቸውን የሚያጠፉት የአእምሮ በሽተኞች ብቻ ናቸው::
3. አንድ ጊዜ ራሱን ለማጥፋት የሞከረ ሰው በሌላ ጊዜም ይህንኑ ሊያደርግ ይችላል::
4. ወጣቶች ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን የሚያጠፉት ከሰዓት በኋላ ጊዜ ነው::
5. ሁልጊዜም ራሳቸውን የሚገድሉ ሰዎች የማስታወሻ ወረቀት ጽፈው ይተዋሉ::
6. ራስን ስለማጥፋት ማንሣት ሰዎች ይህንኑ እንዲያደርጉ ሊገፋፋቸው ይችላል::
7. ራሱን ለማጥፋት የወሰነን ሰው አሳብ ማስለወጥ አይቻልም::
8. ራስን ስለማጥፋት የሚናገሩ ሰዎች ራሳቸውን አይገድሉም::
9. ራሱን የሚያጠፋ ሰው ብዙውን ጊዜ ማስጠንቀቂያዎችን ይሰጣል::
10. በአጠቃላይ ራስን ማጥፋት የተግባቦት መንገድ ነው::

(ለነዚህ ጥያቄዎች የተሰጡትን መልሶች አንብብና ወጣቶቹ የፈለጉትን አሳብ በመሰንዘር እንዲወያዩ አድርግ:: አንዳንድ ገጠመኞቻቸውን ወይም የተመለከቷቸውን ነገሮች ሊናገሩ ይችላሉ::)

1. እውነት:: በብዙ አገሮች ወጣቶች በቀዳሚነት የሚሞቱት ራሳቸውን በማጥፋት ነው:: ችግሩ ቀዳሚ ባልሆነባቸው አገሮች እንኳዋን ከዋንኞቹ የመሞቻ መንገዶች አንዱ ነው::
2. ውሸት:: ምንም ዓይነት የአእምሮ በሽታ ታሪክ ወይም ምልክት የሌላቸው ሰዎች ራሳቸውን ያጠፋሉ:: በሕይወታቸው ውስጥ የተከሰተ ነገር ሊሸከሙ ከሚችሉት አልፎ ጥልቅ ጭንቀት በሚፈጥርባቸው ጊዜ ራሳቸውን ለማጥፋት ይገደዳሉ::
3. እውነት:: ከባዱ ሙከራ የመጀመሪያው ነው:: ይኸው ሙከራ የተፈለገውን ለውጥ ወይም ትኩረት ካላስከተለ፣ ሌላ ሙከራ ሊቀጥል ይችላል::
4. እውነት:: ራስን የማጥፋት ተግባር ተደጋግሞ የሚከሰተው ከዘጠኝ እስከ አሥራ ሁለት ሰዓታት ባሉት ጊዜያት ውስጥ ነው:: ለዚህ ምክንያቱ ምናልባትም ወጣቶቹ የትምህርት ቤት ሰዓት አልቆ ወደ ቤታቸው በሚመለሱበት ጊዜ ብቸኝነት ስለሚሰማቸው ይሆናል::
5. ውሸት:: ብዙውን ጊዜ የምናገኘው ማስታወሻ ተግባሩን (አስክሬኑን) ብቻ ነው::
6. ውሸት:: አንድ ሰው በጭንቀት ውስጥ እንዳለ ከተገነዘብህ፣ የምታነሣበት ራስን የማጥፋት ጉዳይ ግለሰቡ በመጠኑም ቢሆን ካንተ አስቀድሞ ያሰበበት መሆኑ ግልጽ ነው:: ነገር ግን እሱ የሚያስበውን ነገር እንደምታውቅ መግለጽህ፣ ያለበትን ሁኔታ እንደምትገነዘብና እንደምታስብለት ያሳውቀዋል::
7. ውሸት:: ራሱን ለማጥፋት ለሚያስብ ግለሰብም ቢሆን ሞት አስፈሪ ነገር ነው:: ሌላ መንገድ እንዳለ በምትናገርበት ጊዜ ይህንን ማወቁ ሊሉቹን አማራጮች ከግንዛቤው ውስጥ እንዲያስገባ ይረዳዋል:: ነገር ግን ጉዳዩን አናንቀህ በማየት፣ «ይኼማ የጅልነት አሳብ ነው:: የልጅ ሥራ አትሥራ» ማለት የለብህም:: «ከወላጆችህ ጋር መስማማቱ ያስቸግርሃል አይደል?» ወይም «ስቲቭን በጣም ስለምትወጂው ነው አይደል ከሱ መለየቱ ልብሽን የሰበረው?» የሚሉትን ዓይነት ቃላት ተጠቀም:: ዋናው በችግሩ ውስጥ ያሉት ሰዎች ስሜት እንጂ ያንተ ስሜት አይደለም:: ያሉበትን ሁኔታ የምትገነዘብ መሆንህን የሚያመለክት ንግግር ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል::
8. ውሸት:: ብዙውን ጊዜ ዛቻው የድረሱልኝ ጥሪ ነው:: የፈለጉት እርዳታ በማይደርስበት ጊዜ ቁራጥነታቸውን ለማሳየት ሲሉ የዛቱትን ሊፈጽሙ ይችላሉ::
9. እውነት:: ራሳቸውን ከሚያጠፉት ሰዎች 80 በመቶዎቹ የሆነ ግልጽ ምልክት ያሳያሉ:: ነገሩ ግን ምልክቶቹን ለማወቅ ንቁ መሆንን ይጠይቃል:: አንድ ወጣት ጓደኛውን፣ «ራስህን ለማጥፋት ብትፈልግ እንዴት ታደርገዋለህ?» ሲል ጠየቀው:: ጓደኛው ራሱን እንዴት ሊያጠፋ እንደሚችል ከገለጸለት በኋላ ከሱ ተለይቶ በመሄድ የተሰጠውን ማብራሪያ ተግባራዊ አድርጎታል:: ሌላ ወጣት ደግሞ ከሁሉም በላይ ለሚወደው ጓደኛው፣ «ራስህን ለማጥፋት ብትፈልግ ከሁሉም አብልጠህ ለምትወደው ጓደኛህ ትነግረዋለህ?» ሲል ጠየቀው:: ጓደኛውም፣ «የምናገር ይመስለኛል» ካለ በኋላ፣ አሳቡን ቀይሮ፣ «የለም፣ ለመናገር የማፍር ይመስለኛል» አለው:: ይህን የሰማው ጓደኛውም አሳቡን ለሚወደው ጓደኛው ሳያካፍል ራሱን አጥፍቶ ተገኝቷል:: ራሱን የሚያጠፋ ሰው ከሚያሳያቸው ፍንጮች መካከል ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ጭንቀት፣ ከነገሮች ራስን ማግለል፣ ለረዥም ጊዜ ለመመገብና እንቅልፍ ለመተኛት አለመቻል፣ ብዙ ጊዜ ስለሞት መናገር፣ የባሕርይ መለወጥ፣ ራሳቸውን እንደሚያጠፉ መዛትና በሕይወት ተስፋ መቁረጥ ይገኙባቸዋል:: በምትሰጠው ብያኔ ተማመን:: ለአንድ ሰው፣ ማለትም ለወላጅ፣ ለጓደኞች፣ ለአስተማሪዎች ወይም ለመጋቢ ስለ ሁኔታው ተናገር:: ነገሩን ችላ ብሎ በመተው ለቀሪ ዘመናት ከመጸጸት ይልቅ የበለጠ ትኩረት ማድረግ (ግለሰቡ ራሱን የማያጠፋ ቢሆን) ይመረጣል::
10. እውነት:: ብዙውን ጊዜ ግለሰቡ በሕይወት እያለ ችል ያልነውን መልእክት ሲሞት እንረዳለን::

ሽግግር፡ ነገር ግን ራስን በመግደል የሚተላለፈው እውነተኛ መልእክት ምንድነው? ራሱን ለማጥፋት የሚያስብ ጓደኛህን እንዴት ትረዳዋለህ?

መ. ውይይት - ቡድኑን ሦስት አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ከፋፍል፡፡ ግማሾቹ ቡድኖች ወጣቶች ራሳቸውን ለማጥፋት እንዲያስቡ ሊያደርጉ የሚችሉትን ምክንያቶች ያስቡ፡፡ የተቀሩት ግማሾቹ ቡድኖች ራስን ማጥፋት ለየትኞቹም ችግሮች መፍትሔ ሊሆን የማይችልባቸውን ምክንያቶች ይዘረዝራሉ፡፡ ከዚያም አንደኛው ቡድን ችግሩን ሲያቀርብ፣ ሌላኛው ቡድን መፍትሔውን እንዲያቀርብ አድርግ፡፡ ባጋጠሙት ችግሮች የተጨነቀውን ሰው ለመርዳት ብዙ ድጋፍና ትዕግሥት እንደሚያስፈልግ ሁሉም ወጣቶች መገንዘባቸውን አረጋግጥ፡፡

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች

1. ማቴዎስ 26:69-27:10 .. በዚህ ክፍል በተመሳሳይ የሕይወት ገጠመኞች ውስጥ ያለፉ የሁለት ሰዎች ታሪኮች ተገልጸዋል፡፡ ሁለቱም የክርስቶስ ተከታዮች፣ ወደፊት ስለሚፈጽሟቸው ተግባራት ትንቢት የተነገረባቸውና ዳሩ ግን ተግባራቸውን ከመፈጸም ወደኋላ ያላሉ ሰዎች ነበሩ፡፡ ይሁዳ ክርስቶስን አሳልፎ ሲሰጥ፣ ጴጥሮስ ደግሞ ክዶታል፡፡ ሁለቱም የከፋ ውድቀት እንደደረሰባቸው ተሰምቷቸዋል፡፡ ነገር ግን ለሕይወት የሰጧቸው ምላሾች የተለያዩ ነበሩ፡፡ ጴጥሮስ ወደ ውጭ ወጥቶ መራራ ለቅሶ ሲያለቅስ (26:75)፣ ይሁዳ ግን ራሱን ሰቅሎ ሞተ (27:5)፡፡
2. እነዚህ ሰዎች የውድቀት ስሜቶች መግለጫዎች ናቸው፡፡ ወጣቶች በሕይወት ላይ ተስፋ እንዲቆርጡ የሚያደርጉ ብዙ ምክንያቶች አሉ፡፡ ይሁንና፣ አሁን እየሆነ ያለው ምንም ይሁን ምን አሁን ዘላለም አይደለም፡፡ ጴጥሮስ ከውድቀቱ ተመልሶ ለአንዲት ልጅ የካደውን ስም በሐዋርያት ሥራ 4:18-20 ውስጥ በድፍረት ሰብኮአል፡፡ ይሁዳ ግን የተሻለ ቀን የማየት ዕድል አልገጠመውም፡፡

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ፡፡)

1. በውድቀታቸው ጊዜ እነዚህ ሰዎች እያንዳንዳቸው ምን ተሰማቸው?
2. ለጴጥሮስ ውድቀቱ ቀላል ነበር? (ማቴዎስ 26:34-35 አንብብ)፡፡
3. አንደኛው ሕይወቱን ለማጥፋት የመረጠውና ሌላኛው በሕይወቱ የጨለማ ጊዜያት ውስጥ ጸንቶ ለመቆም የወሰነው ለምን ይመስልሃል?
4. በዛሬዎቹ ጨዋታዎች ላይ አንዳንዶቻችሁ ገለል ብላችሁ ለብቻችሁ እንድትቀመጡ በተጠየቃችሁ ጊዜ ምን ተሰማችሁ?



በዓለማችን ውስጥ እነዚህ ስሜቶች በአንዳንድ ሰዎች ሕይወት ልብ ውስጥ በቋሚነት የሚኖሩ ናቸውን?

5. ከየትኞቹም የሕይወት ሁኔታዎቻችን አንጻር «አሁን» ዘላለም (ማለትም የማይቀየር) ነውን?

ሰ. መዝጊያ

እነዚህን መሠረታዊ ነጥቦች ለተማሪዎችህ አንብብ፡፡ ይህ በርእስጉዳዩ ላይ የቀረበ ጥልቅ ጥናት ሳይሆን፣ በአሁን ጊዜ ወጣቶች የሚጋፈጡትን ችግር በመጠኑ የሚያስገነዝባቸው መሆኑን ግለጽላቸው፡፡ አንድ ሰው ራሱን ለማጥፋት የሚያስብ ከመሰለህ፣

1. ችግሮቹን ለመረዳት እየሞከርህ አድምጠው፡፡
2. ሊረዳው ለሚችል ሰው ሁኔታውን አሳውቅ፡፡
3. በሚቀጥሉት ቀናት በአካል በመገኘትና ስልክ በመደወል አበረታታው፡፡

አሁን ዘላለም እንዳልሆነና ራስን ማጥፋት ግን ነገሮችን ወደ ፍጻሜ እንደሚወስድ ተገንዘብ፡፡

በሕይወታቸው ውስጥ የተጋፈጡት ችግር ካለ ለመርዳት ዝግጁ መሆንህን ግለጽላቸው፡፡

በጸሎት ፈጽም፡፡

በፍጹም
አልጥልህም
አልተውህም!
እግዚአብሔር!

## የሐሰተኛ ሃይማኖቶች አደጋ
### ከማርክ ጊልሮይ

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. የሚያጋጥሙን ብዙ ሐሰተኛ ሃይማኖቶች እንዳያታልሉን መጠንቀቅ አለብን::
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች ስለ ሐሰተኛ ትምህርቶችና ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ሃይማኖቶች የተወሰነ መረጃ እንዲያገኙና የአንድን አስተምህሮ እውነተኝነት ወይም ሐሰተኝነት ለመወሰን የሚያስችሉ መምሪያዎችን እንዲማሩ ለማገዝ::
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ክርስቲያኖች በሁሉም አቅጣጫዎች እንደ ሞርሞኖች፣ የይሖዋ ምስክሮች፣ ከመንፈስ ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን የሚያካሂዱ ቡድኖች፣ የአያት ቅድማያት አምላኪዎች፣ ጠንቋዮች፣ የሰይጣን አምላኪዎች፣ እንደ እስልምናና ቡድሂዚም ያሉ ታላላቅ የዓለም ሃይማኖቶች፣ በሂንዱ/የምሥራቃውያን ፍልስፍና ላይ የተመሠረቱ ብዙ የኒውኤጅ ዓይነት ሃይማኖቶች ያጋጥሟቸዋል:: ራሳችንንና ወጣቶቻችንን ከነዚህ ጥቃቶች ለመጠበቅ ምን ልናደርግ እንችላለን? ይህን ችግር ለመቋቋም እምንታዊ አቀራረብ (ቃሉን በትጋት ማጥናትና ከአማኞች ማኅበረሰብ ጋር ኅብረት ማድረግ) እና አሉታዊ አቀራረብ (ክርስቲያናዊ ስላልሆኑት ሃይማኖቶች ማስጠንቀቂያዎችን መስጠት) አስፈላጊ ነው:: ይህንን የማስተማር አገልግሎት በምታካሂድበት ጊዜ የወጣቶችህን የማወቅ ጉጉት ለመጠቀም ሞክር::
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. ለእያንዳንዱ ተማሪ እርሳስ ወይም እስክብሪቶ፣ ወረቀትና መጽሐፍ ቅዱስ::

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል::)

1. እጅ ለእጅ መያያዝ:: ተማሪዎቹ ክብ ሠርተው እንዲቆሙ አድርግ:: (ከ12 የሚበልጡ ወጣቶች ካሉህ፣ ከ8 እስከ 10 የሚበልጡ ተማሪዎች በአንድ ቡድን ውስጥ እንዲገቡ አድርገህ ከፋፍል::) አንድ ልጅ የሌሎች ሁለት ልጆችን እጆች ይይዛል:: ሁለቱ እጆች የአንድ ሰው ወይም ከግራውና ከቀኙ ያሉት ልጆች እጆች መሆን የለባቸውም:: ተማሪዎቹ እንደተያያዙ አንድ ክብ እንዲሠሩ ንገራቸው::
2. ረድፎችን መሙላት:: ዘጠኝ ወንበሮችን (3x3) በሦስት ረድፍ አስቀምጥ:: ተማሪዎችህን በሁለት ቡድኖች ከፋፍል:: እያንዳንዱ ቡድን በየተራ አንድ አባሉን በመላክ ከወንበሮቹ በአንዱ ላይ እንዲቀመጥ ያደርጋል:: (ወንበሮቹ ሀ ወይም ለ የሚል መለያ ቢደረግላቸው ጥሩ ይሆናል::) በአንድ ረድፍ ሦስት አባላቱ ደርሰው የሚቀመጡለት ቡድን የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል:: ወንበሮቹን ሀ ወይም ለ ብለህ ካልለየህ ጨዋታው ከምታስበው በላይ አስቸጋሪ ይሆንብሃል:: ጨዋታውን የበለጠ ከባድ ለማድረግ ከፈለግህ፣ ቡድኖቹ የሚንቀሳቀሱበትን ጊዜ ልትወስንና እርስበርሳቸው እንዳይመካከሩ ልትከለክል ትችላለህ::
3. ምን ታውቃለህ? ለስላሳ ኳስ ይዘህ ና:: ተማሪዎቹ በክብ ቅርጽ እንዲቀመጡ አድርግ:: የዛሬው ትምህርት በሐሰተኛ ትምህርቶች («ኑፋቄዎች») ላይ እንደሚያተኩር ግለጽላቸውና ትምህርቱን ከመጀመራችሁ በፊት ተማሪዎቹ ስለ ኑፋቄዎች ምን ዓይነት ግንዛቤ እንዳለው ለማወቅ መፈለግህን ንገራቸው:: ይህን ትምህርት ከማጥናትህ በፊት ስለ ኑፋቄዎች ታውቅ የነበረውን አንድ ነገር ከነገርሃቸው በኋላ ያመጣኸውን ኳስ ወደ አንድ ልጅ ወርውር:: ልጁ ስለ ኑፋቄ የሚያውቀውን ከተናገረ በኋላ ኳሱን ወደ ሌላ ሰው ይወረውራል:: እሱም እንደዚያው ያደርጋል:: መልሶች መደጋገም እስኪጀምሩ ድረስ ይህ ጨዋታ ለአምስት ደቂቃዎች ያህል እንዲቀጥል አድርግ:: ወጣቶቹን ስላበረከቱት አስተዋጽኦ አመስግናቸውና ስለ ኑፋቄ ተጨማሪ ፈተና እንደሚጠብቃቸው ንገራቸው::
4. የቡድን ዝማሬ::

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው::)

ከዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ ያለውን ፈተና ለተማሪዎችህ በማቅረብ ትምህርቱን ጀምር:: ጥያቄዎቹን ፎቶኮፒ አድርገህ ልትሰጣቸው ወይም ጥያቄዎቹን እያነበብህ መልሶቹን በወረቀት ላይ እንዲጽፉ ልታደርግ ትችላለህ:: ጥያቄዎቹን እንዲመልሱ ከ7 እስከ 10 ደቂቃዎችን ከሰጠሃቸው በኋላ፣ መልሶቹን ከልስላቸው:: ከዚህ በታች በ«መ» ሥር የቀረቡት የመወያያ ጥያቄዎች ከፈተናው የቀጠሉ ናቸው::

የፈተናው መልሶች

1. ሠ 2. እውነት 3. ሠ 4. እውነት 5. ሠ 6. እውነት 7. ሠ
8. ረ 9. ሐ 10. ሠ 11. እውነት 12. ውሸት 13. ሐ. 14. ለ
15. ለ

መ. የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከዚህ ፈተና ውስጥ ያስገረመህ ነገር ምንድነው? ለምን?

2. ከኑፋቄ፣ ጥንቆላ፣ ወይም ክርስቲያናዊ ያልሆኑ አስተሳሰቦችን ከሚያስፋፉ ሰዎች ወይም ጽሑፎች ጋር ምን ዓይነት ትውውቅ እንደነበረህ ግለጽ:: ምን ዓይነት ምላሾች ሰጠህ?
3. ብዙ ሰዎች ወደ ኑፋቄዎች የሚሳቡት ለምን ይመስልሃል?
4. የኑፋቄዎች፣ የጥንቆላና ክርስቲያናዊ ያልሆኑ አስተሳሰቦች መበራከት ምን ያህል ሊያሳስበን ይገባል?
5. ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን እየገባን ሳለ፣ ራስህንም ሆነ ሌሎች የዚህ ቡድን አባላትን ከኑፋቄዎች ለመጠበቅ ምን ማድረግ ይቻላል ትላለህ?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች

እንቅስቃሴውን ለማስተዋወቅ ተማሪዎችህን በአራት ቡድኖች ከፋፍልና ለእያንዳንዱ ቡድን ከአንድ እስከ አራት ያሉትን ተራ ቁጥሮች ስጣቸው:: ሁሉንም ጥያቄዎች ከሁሉም የክፍሉ ተማሪዎች ጋር እንደምትወያይና ዳሩ ግን እነሱ በኃላፊነት የሚጠየቁት ለሰጠሃቸው ጥያቄ ብቻ መሆኑን ግለጽላቸው:: ከዚህ በታች ጥያቄዎቹና ሊያግዙህ የሚችሉ አጫጭር ማብራሪያዎች ቀርበውልሃል::

ተማሪዎቹ ለሌሎች የሚያካፍሏቸውን አሳቦች እንዲያዘጋጁ ከ7 እስከ 10 ደቂቃዎችን ስጣቸው::

1. *ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?* ቡድናችሁ የሚከተሉትን ጥቅሶች በማንበብ «ክርስቶስ ማነው?» ለሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት አለበት:: ዮሐንስ 1:1-2፣ ዕብራውያን 13:8፣ ዮሐንስ 10:30፣ ማቴዎስ 1:18-23፣ 11:27፣ ፊልጵስዩስ 2:6-11:: ኑፋቄዎች ይህን ጥያቄ እንዴት በተሳሳተ መንገድ እንደሚመልሱ የሚያሳይ ምሳሌ ስጡ:: *(እነዚህ ጥቅሶች የሚያሳዩት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው የሚለውን ጠቃሚ ክርስቲያናዊ አስተምህሮ ነው:: እርሱ ፍጡር ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር ለዘላለም አብሮ የኖረ ነው:: ኢየሱስ መልካም ሰው፣ ወይም እግዚአብሔር ከኛ የሚጠብቀውን አኗኗር የሚያሳይ ምሳሌ ብቻ አይደለም:: እርሱ ሥጋ የለበሰ አምላክ ነው:: ኑፋቄዎችና ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ሃይማኖቶች ተቀባይነት ካላቸው ክርስቲያናዊ እውነቶች ከሚያፈነግጡባቸው ቁልፍ መንገዶች አንዱ በኢየሱስ ላይ ያላቸው አመለካከት ነው:: ብዙዎቹ ለክርስቶስ ቀና አመለካከት አላቸው:: ጥሩ ሰው ነበረ ብለው ያስባሉ:: ግን እንደ አምላክ? ሊያድነን እንደሚችል ፈጣሪ? በፍጹም አይቀበሉም! ይህ በርግጥ ክርስቲያናዊ ካልሆኑ ሃይማኖቶች የሚጠበቅ ነው:: ነገር ግን ብዙውን ጊዜ የክርስትና አካል ነን ስለሚሉት ኑፋቄዎች መጠንቀቅ አለብን:: በእምነት ከእናንተ ለሚለዩ ሰዎች ማቅረብ ያለባችሁ መሠረታዊ ጥያቄ: ክርስቶስ ለእንተ ማነው? የሚል ነው::)*

ምሳሌ: የይሖዋ ምስክሮች ወልድ ከአብ ጋር እኩል አይደለም ይላሉ:: ክርስቶስ እግዚአብሔር አብ የፈጠረው የመጀመሪያው ፍጡር እንደነበረ ያስተምራሉ::

2. *ሰው በርግጥ ችግር አለበት?* ቡድናችሁ የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አንብቦ፣ «ሰው በርግጥ ችግር አለበት?» የሚለውን ጥያቄ መመለስ አለበት:: ኢሳይያስ 53:6፣ ሮሜ 3:23፣ 5:12-19፣ ኤፌሶን 2:1:: ኑፋቄዎች ለዚህ ጥያቄ በቂ ያልሆነ ምላሽ የሚሰጡበትን ሁኔታ የሚያመለክት ምሳሌ ስጡ:: *(መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ በትክክል ችግር እንዳለበት ይናገራል:: ሰዎች ሁሉ ኃጢአትን ስለሠሩ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ማግኘት ያስፈልጋቸው ነበር:: ይህ ደግሞ በሰው ልጅ ጥረት የማይገኙ ተራራ ነበር:: ኑፋቄዎች፣ ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ሃይማኖቶችና በአጠቃላይ ዓለማውያን ማኅበረሰብ ከክርስቲያናዊ እውነት የሚያፈነግጡበት ሁለተኛው ነጥብ ይኼ ነው:: በዓለማችን ላይ ጦርነቶች፣ አንዱ በሌላው ላይ የሚያስከትለው ሥቃይና ሌሎችም የሰውን ልጅ ችግር የሚጠቁሙ ብዙ ጉዳዮች በግልጽ ቢታዩም፣ ብዙዎች የሰውን ኃጢአተኝነት ወይም የኃጢአትን አሳሳቢነት ለመቀበል አይፈልጉም:: ብዙዎች ሰው በባሕርዩ መልካም እንደሆነ ይናገራሉ:: ይህ ግን እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ የሚሰጠውን ከፍተኛ ግምት ቸል ብለን እንድንተው ሊያደርገን አይችልም:: ይሁንና፣ መውደቃችንን ማስታወስ ይኖርብናል:: በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ፈጽመናል:: የተወለድነውም እግዚአብሔር ብቻ የሚያስወግደውን የኃጢአት ባሕርይ ይዘን ነው::)*

ምሳሌ: በሂንዱ እምነት፣ ሁላችንም አማልክት ነን:: ይህንንም ለመገንዘብ ንቁ አእምሮንና ምክንያታዊነትን ማስወገድ እንዳለብን ያስተምራሉ:: በነሱ እምነት፣ አማልክት መሆናችንን እንዳናይ የሚከለክሉን እነዚህ ሁለቱ ነገሮች ናቸው:: ብዙ ኑፋቄዎች (ክርስቲያን ሳይንስ፣ ኒው ኤጅና ሌሎችም) ይህንን አሳብ በተለያዩ መንገዶች ይተረጉሙታል::

3. *እንዴት ደኅንነትን ልናገኝ እንችላለን?* ቡድናችሁ የሚከተሉትን ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አውጥቶ በመመልከት «እንዴት ልንድን እንችላለን?» ለሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት አለበት:: ዮሐንስ 3:3፣ ሮሜ 3:24፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 15:4፣ ሮሜ 5:6-11፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 5:7:: ኑፋቄዎች ይህንን ጥያቄ በተሳሳተ መንገድ የሚመልሱበትን

ሁኔታ የሚያሳይ ምሳሌ ስጡ። *(ደኅንነትን ልናገኝ የምንችለው በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ለማካኝነት ነው። ይህም የእግዚአብሔር የጸጋ ተግባር ነው። የኛ ድርሻስ? እኛ ከኃጢአታችን ንስሐ የመግባትና የማመን ኃላፊነት አለብን። ነገር ግን እምነታችንም ራሱ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ራሳችንን ለማዳን አንችልም። ልንድን የምንችለው በክርስቶስ ጸጋ ብቻ ነው - ኤፌሶን 2:8-9። አብዛኞቹ ኑፋቄዎች ይህንን እውነት በመካድ ሰው በመልካም ሥራው ራሱን ሊያድን ይችላል ይላሉ። ለዚያውም ደኅንነት ካስፈለገው።)*
*ምሳሌ፡* ሞርሞኖች ሁሉም ሰው የኋላ ኋላ መልካምን ተግባር በማከናወን ወደ መንግሥተሰማይ እንደሚሄድ ያምናሉ። (አብዛኞቹ ይህንን መልካም ተግባር የሚያከናውኑት ከሞት ፀኋላ እንደሆነ ያምናሉ።) ነገር ግን እጅግ ከፍ ወዳለው ሰማይ ሊሄዱ የሚችሉት የሞርሞን እምነት ተከታዮች ብቻ ናቸው ይላሉ።

4. የሥልጣናችን ምንጭ ምንድነው? ቡድናችሁ የሚከተሉትን ጥቅሶች በማንበብ፣ «የሥልጣናችን ምንጭ ምንድነው?» ለሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት አለበት። 2ኛ ጢሞቴዎስ 3:16-17፣ 2ኛ ጴጥሮስ 1:20-21፣ ዕብራውያን 4:12፣ ኢሳይያስ 40:8፣ መዝሙር 119:105፣ ዘዳግም 6:11-13። ኑፋቄዎች ይህንን ጥያቄ እንዴት ትክክል ባልሆነ መንገድ እንደሚመልሱ የሚያሳይ ምሳሌ ስጡ። *(የክርስትና እምነት ዋንኛ አስተምህሮ የሚያርፈው መጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ሥልጣን ያለውና በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር የተጻፈ በመሆኑ ላይ ነው። እግዚአብሔር በ66 የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት አማካኝነት እንደተናገረን እናምናለን። ማንም መጽሐፍ ቅዱስን እንዳያብራራ ወይም በቃሉ መልእክት ላይ ጽሑፎችን እንዳያዘጋጅ አንከለከልም። ይሁንና፣ የሥልጣንን ስፍራ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ እኩል በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር የተጻፈ ነው ብለን እውቅና የምንሰጠው ሌላ መጽሐፍ የለም። ኑፋቄዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ላሉት መጻሕፍት ሥልጣን በመስጠት ይታወቃሉ። አንዳንዶች ለመጽሐፍ ቅዱስ እሴት እውቅና ቢሰጡም፣ የራሳቸውን አተረጓጎም ያክሉበታል።)*
*ምሳሌ፡* ሞርሞኖች የተቀደሱ ናቸው የሚሏቸው ብዙ መጻሕፍት አሏቸው። ከነዚህም መካከል የሞርሞን መጽሐፍ፣ ታላቅ ዋጋ ያለው እንቁ፣ ዶክትሪኖችና ቃል ኪዳኖች የሚሉ ይገኙባቸዋል። ክርስቲያን ሳይንስ የተሰኘው እምነት መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት በሜሪ ቤክር ኤዲ መጻሕፍት ላይ ይደገፋል። ዋንኛው መጽሐፍ ቅዱሳቸው



በዚህችው ሴት የተጻፈውና ሳይንስና ጤና (Science and Health) የተሰኘው ነው።
ማጠቃለያ፡ አንድ ሰው 1ኛ ዮሐንስ 4:1-3ን እንዲያነብብ በመጠየቅ ይህንን ክፍል አጠናቅቅ።

ረ. ውይይት
ብዙ የኑፋቄ አባላት ክርስቲያናዊ *ሥረመሠረት* አላቸው። የተሻለ ግንዛቤ ሊኖራቸው የሚገቡ ሰዎች ለምን ወደነዚህ ቡድኖች ይገባሉ? ሁለቱ ታላላቅ ምክንያቶች *የቤተክርስቲያን አካል ያለመሆን ስሜትና ያልተሟሉ ፍላጎቶች ወይም ስሜታዊ ጉዳቶች* ናቸው። አንዳንድ ምሳሌዎች ከዚህ በታች ተሰጥተዋል።

1. «ብትምህርት ቤትም ሆነ በቤተክርስቲያን ከሰዎች ጋር አልገጥምም ነበር። ይኼኛው ቡድን ግን ቤተኛ አድርጎ ተቀብሎኛል።»
2. «ፍቅረኛዬ በተለየችኝ ጊዜ፣ ከፍተኛ ስሜታዊ ጉዳት ስለደረሰብኝ የሚወደኝን የሆነ ሰው ወይም ቡድን ስፈልግ ነበር።»
(ይህንን ካነበብህላቸው በኋላ፣ ተማሪዎችህ ራሳቸውንና እንዱ ሌላውን እንዴት ሊጠብቅ እንደሚችል የመጣላቸውን አሳብ እንዲወረውሩ ጠይቃቸው። የሚጠቅሷቸውን አሳቦች መዝግብ።)

ረ. የተማሪዎች ምላሽ
ለተማሪዎችህ ወረቀትና እርሳስ አድል። የቅርብ ጓደኛቸው ወይም የቤተሰባቸው አባል ሰሞኑን ወደ ኑፋቄ ወይም ክርስቲያናዊ ያልሆነ ሃይማኖት እንደገባ ንገራቸው። (ወደየትኛው የሃይማኖት ቡድን እንደገባ ማሰብ ያስፈልጋቸዋል።) ከቡድኑ ለመውጣት የሚፈልግ ልጅ ደብዳቤያቸውን ለጓደኛቸው ወይም ለቤተሰባቸው አባል ለመውሰድ ዝግጁ መሆኑን ይናገራል። ተማሪዎቹ ጓደኛቸው ወይም የቤተሰባቸው አባል ወደ ቤተክርስቲያናቸው እንዲመለስ የሚጠይቅ ደብዳቤ እንዲጽፉ ጠይቃቸው።
ወጣቶቹ ደብዳቤዎቻቸውን እንዲጽፉ ከ8 እስከ 10 ደቂቃዎችን ከሰጠሃቸው በኋላ፣ ፈቃደኛ የሆኑት ሰዎች የደብዳቤዎች መልእክት ለክፍሉ ተማሪዎች እንዲያካፍሉ ጠይቅ። ይህንን ክፍል በችኮላ አትፈጽመው። ይህ የክፍለጊዜው እጅግ ጠቃሚ ክፍል ሊሆን ይችላል። ምናልባትም በሚቀጥለው ሳምንት የሌሎችን ተማሪዎች ደብዳቤዎች ለመስማት ቀጠሮ ልትይዝ ትችላለህ።

ሰ. መዝጊያ
ወጣቶች የሚከተሉትን አራት ጥያቄዎች በጸሎት መንፈስ ሆነው እንዲያሰላስሉ ጠይቃቸው።

1. የምታምነውን ለማወቅ ቁርጠኛ አቋም ይዘሃልን?
2. ክርስቶስን የሕይወትህ ጌታ አድርገህ ይዘሃልን?

3. የመጽሐፍ ቅዱስን ትእዛዛትና አስተምህሮዎች ትኩረት ሰጥተህ ተግባራዊ ታደርጋለህን?
4. በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ከሚያድጉ ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት ታደርጋለህን?

ሸ. አማራጭ እንቅስቃሴዎች

ይህ አንዳንድ ፈጠራ የታከለባቸው የማቅረቢያ መንገዶችን ለመሞከር የሚያመች ግሩም ትምህርት ነው! ከቤተክርስቲያንህ (ወይም ከምታስተምራቸው ወጣቶች) አንድ ወይም ከዚያ የሚበዙ አዋቂዎች ሐሰተኛ አስተማሪዎችን መስለው ወደ ክፍልህ እንዲመጡ ልትጋብዝ ትችላለህ። ግለሰቡ አዳዲስ አባላትን ለመመልመል የሚያስችል ንግግር እንዲያደርግና ለተማሪዎችህ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ ለመስጠት እንዲችል ስለሚወክለው የሃይማኖት ቡድን አጥጋቢ ምርምር እንዲያካሂድ ንገረው። ይህን እንቅስቃሴ ከትምህርቱ መጀመሪያ አቅርበው። ይህንኑ ትምህርት ከወጣቶችህ ጋር ለማጠቃለል አንድ ሳምንት ለመጨመር አስብ።

# እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል

ዮሐንስ 8:32



## ፈተና ስለ ሐሰተኛ ትምህርቶች

1. አንድ የይሖዋ ምስክር በቤተሰቦቹና በቤተክርስቲያኑ ዘንድ እንደሞተ የሚቆጠረው...

ሀ. ከሰዎች ደም ሲቀበል ለ. ለአገሩ ባንዲራ ሰላምታ ሲሰጥ ሐ. ኩላሊቱን ለሌላ ሰው ሲሰጥ መ. ወልድ ከአብ እኩል እንደሆነ ሲያምን ሠ. ሁሉም

2. በጥንቆላ ውስጥ ከሚሳተፉት ሰዎች ብዙዎቹ ሴቶች ሲሆኑ፣ በጣም የታወቀው የጥንቆላ ተግባር የኮከብ ቆጠራ ነው። እውነት/ሐሰት
3. የክርስቲያን ሳይንስ መሥራች የሆነችው ሜሪ ቤከር ኤዲ... ሀ. ትምህርቶቿ የእግዚአብሔር የመጨረሻ መገለጦች መሆናቸውን ተናግራለች ለ. ሞትና በሽታ በትክክል የሚፈጸሙ ነገሮች ሳይሆኑ የሰዎች የአእምሮ ቅዠቶች እንደሆኑ ገልጻለች ሐ. ክፉት የሚባል ነገር እንደሌለና ሰው ኃጢአትን እንዳልሠራ አስተምራለች መ. ክርስቶስ እንዳልሞተና በመቃብር ውስጥ ተደብቆ እንደነበር አስተምራለች ሠ. ሁሉም
4. ሞርሞኖች ትምባሆን፣ ሱስ አስያዥ ቅመሞችን (ካፌይን) እና ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም ወሲብ የሚቃወሙ ሲሆን፣ ጠንካራ ቤተሰቦችን ለመመሥረት ይጥራሉ። እውነት/ሐሰት።
5. የሞርሞን መጽሐፍ... ሀ. የአሜሪካ ሕንዶች የጠፉት አሥር የእስራኤል ነገዶች ዘሮች እንደሆኑ ይናገራል። ለ. ሞሮኒ የተባለ መልአክ ለጆሴፍ እስሚዝ እንደሰጠው ይናገራል። ሐ. ጆሴፍ እስሚዝ ኡሪምና ቱሚም የተባሉትን ጣምራ የወርቅ መነጽሮች አድርጎ እንደተረጎመው ያብራራል። መ. ሰው አምላክ ሊሆን እንደሚችል ይናገራል። ሠ. ሁሉም።
6. ሰይጣንን የሚያስከብረው የአምልኮ አገልግሎት ብላክ ማስ (black mass) ይባላል። እውነት/ውሸት
7. ወደ ክርስትና ለመለወጥ እጅግ አስቸጋሪ የሆነው የሃይማኖት ቡድን... ሀ. ሙስሊሞች ለ. ቡድሂስቶች ሐ. ሰይጣናውያን መ. በየትኛውም ሃይማኖት የማያምኑ ከሃዲያን
8. ኒው ኤጅ ሙቭሜንት... ሀ. ሁላችንም አማልክት ነን ይላል። ለ. ከመወለድህ በፊት እንደነበርህና ከሞትህም በኋላ እንደምትኖር ያስተምራል። ሐ. ሞት እንደሌለ ይናገራል። መ. እውነት ግለሰቡ የሚፈጥረው ነው። ሠ. ምንም ረ. ሁሉም
9. የይሖዋ ምስክሮች ክርስቶስ... ሀ. ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል ነው ይላሉ። ለ. የተፈጠረና ከማንም የማይበልጥ

መሆኑን ያስተምራሉ:: ሐ. ፍጡርና ሌሎችን ነገሮች የፈጠረ ነው ይላሉ::

10. ዩኒቴሪያኖች... ይክዳሉ:: ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ በእስትንፋሰ-እግዚአብሔር የተጻፈ መሆኑን:: ለ. የክርስቶስን አምላክነት:: ሐ. የክርስቶስን የመስቀል ላይ ሞት አስፈላጊነት:: መ. ምንም:: ሠ. ሁሉም::
11. ሞርሞኖች ደኅንነትን የሚያገኙት መልካም ተግባራትን የፈጸሙ ሰዎች ብቻ ናቸው ብለው ያምናሉ:: እውነት/ሐሰት::
12. የማርክሲዝም አባት የሆነው ካርል ማርክስ ንድፈሐሳቦቹን እንደ ሃይማኖት መሥርቷል:: እውነት/ሐሰት
13. ሞሐመድ... አስተምሯል:: ሀ. ብዙ የትዳር ጓደኛ መያዝ ኃጢአት እንደሆነ:: ለ. በአላህ ማመን ደኅንነትን እንደሚያመጣ:: ሐ. ሰው ለራሱ ኃጢአቶች ዋጋ መክፈል እንዳለበት:: መ. ምንም:: ሠ. ሁሉም::
14. ብሃግዋን ሽሪ ራጀኒሽ (Bhagwan Shree Rajnees) ... ያስተምራል:: ሀ. ከምድራዊ ፍላጎቶች ሙሉ በሙሉ መገለልን ለ. የወሲብ፣ ዕፅና ሌሎች ፍላጎቶችን መከተል አስፈላጊ መሆኑን
15. ቡድሂስቶች ሥቃይን የማብቂያው መንገድ... ነው ብለው ያምናሉ:: ሀ. ስለ ተፈጥሮ ኃይላት መማር:: ለ. ምንም ነገር አለመፈለግ:: ሐ. ማርሻል የጦርነት ጥበቦችን መለማመድ:: መ. ዮጋን መለማመድ:: ሠ. ምንም:: ረ. ሁሉም::



## መዝናናት ትክክል ነው ወይስ...?

### ከብሩስ አልድሃም

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. የመዝናኛ ምርጫዎቻችን ለክርስቶስ እንድንኖር ሲረዱን እንጂ ሲፈትኑን ወይም ክፋትን ወደ ሕይወታችን ሲያመጡ አይገባም::
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች የመዝናኛ ምርጫዎቻቸውን እንዲገመግሙ ለማበረታታት፣ ክርስቲያናዊ እሴቶችንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመዘኛዎችን እንዲገነዘቡ ለማገዝና ክርስቶስ ለሕይወታቸው ከሚፈልገው ነገር ጋር የሚጣጣሙ ምርጫዎችን የሚያካሂዱባቸውን መሣሪያዎች ለመስጠት::
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. የዛሬውን ዓለም ፍልስፍና በአንድ ቃል ማጠቃለል ቢያስፈልግ «ተዝናና!» የሚል እንደሚሆን አምናለሁ:: ወጣቶች በዚህ ባሕል ውስጥ ተዘፍቀው ምርጫዎቻቸውን ሁሉ ለስሜታቸው በሚሰጠው እርካታ ላይ ይመሠርታሉ:: አዎን፣ ክርስቶስ በሕይወታችን እንድንደሰት የሚፈልግ መሆኑን አምናለሁ:: ነገር ግን ለሕይወታችን የርሱ ቀዳሚ ዓላማ ምቾትን መስጠት ነው ብዬ አላምንም:: ትልቁ የርሱ ዓላማ በቅድስናና በፍቅር እርሱን እንድንመስል ማድረግ፣ እንዲሁም ዓለምን ከራሱ ጋር ማስታረቅ ነው:: ደስታ የዚያ ሂደት ውጤት ነው:: የትኛውም ዓይነት መዝናኛ በክርስቶስ ከማደጋችን አንጻር መገምገም አለበት::
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. መጽሐፍ ቅዱሶች፣ እርሳሶች፣ ወረቀት፣ ስድስት ካርዶች ወይም ወረቀቶች፣ ሦስት ጎድጓዳ ሳሕን የተቀቀለ ድንች፣ ሦስት ፎጣዎች፣ ጥቂት አሮጌ ጋዜጦች፣ ሦስት ትናንሽ ክብ ነገሮች::

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል::)

1. ከተቀቀለ ድንች ውስጥ ክብ ነገር መፈለግ:: ክፍለጊዜው ከመጀመሩ በፊት፣ ሦስት ጎድጓዳ ሳሕን የሚሆን ድንች (ወይም ሌላ ለስላሳና የሚጣበቅ ምግብ) አዘጋጅ:: እያንዳንዱ ጎድጓዳ ሳሕን የልጆቹን ፊት ለማስገባት እንዲችል ሰፊ መሆን አለበት:: ከእያንዳንዱ ጎድጓዳ ሳሕን ሥር አንዳንድ አነስተኛ ክብ ነገር አስቀምጥና ከላዩ ላዩ የተቀቀለውን ድንች ከምር:: እያንዳንዱ ቡድን አንድ ተሳታፊ እንዲመርጥ ጠይቅ:: እያንዳንዱ ተሳታፊ እጁን ወደ ኋላ ዘርግቶ ከጎድጓዳ ሳሕኑ ፊት እንዲንበረከክ

ጠይቅ። ምልክት በምትሰጥበት ጊዜ፣ አፋቸውን ወደ ጎድጓዳ ሳሕኖቹ ውስጥ ከተው ክፒን ነገር መፈለግ ይኖርባቸዋል። ባገኟት ጊዜ በአፋቸው ይዘው ያወጧታል።

2. የመገናኛ ብዙሐን መግለጫ። ለእያንዳንዱ ቡድን የአምስት ሰዎችን ስም እንደምትሰጥ ተናገር። የቡድኖቹ ሥራ ከሰዎቹ ስም በስተቀር ሌላ መረጃ ሳያገኙ የሚወዱትን ሀ. መዝሙር፣ ለ. መጽሔት፣ ሐ. የሙዚቃ ቡድን፣ መ. መጽሐፍ መገመት ይሆናል። የምትሰጣቸው አምስት ስሞች፡ ሀ. አንቶኒ አትሌት፣ ለ. ኬለቦጋይል ካንትሪክላብ (ሀገረሰብ የሙዚቃ ክላብ)፣ ሐ. ሚካኤል ሚሊቴሪ (ውትድርና)፣ መ. ማንክዋና ሚዩዚክ፣ ሠ ካራቦ ክርስቲያን ይሆናሉ።

3. ተማሪዎቹን በሦስት ቡድኖች ከፋፍል።

   ሀ. ቡድን አንድ፡ ይህ ቡድን አንድን ተወዳጅ የወጣቶች መጽሐፍ ወይም የቴሌቪዥን ፕሮግራም በመመርመር በውስጡ የሚገኙ ዋና ዋና ገጸባሕርያት በሙሉ ክርስቲያኖች ቢሆኑ መጽሐፉ/የቴሌቪዥኑ ፕሮግራሙ እንዴት ሊለወጥ እንደሚችል ያብራራል።

   ለ. ቡድን ሁለት፡ ይህ ቡድን አንድን ተወዳጅ የወጣቶች እንቅስቃሴ ወይም ፊልም በመገምገም በውስጡ የሚገኙ ዋና ዋና ገጸባሕርያት በሙሉ ክርስቲያኖች ቢሆኑ እንዴት ሊለወጥ እንደሚችል ያብራራል።

   ሐ. ቡድን ሦስት፡ ይህ ቡድን አንድን ተወዳጅ ዓለማዊ ዘፈን በመምረጥ ቡድኑ ክርስቲያናዊ ናቸው ብሎ ከሚያምናቸው እሴቶች ጋር የማይጣጣሙትን ቃላትና ሐረጎች ከዘፈኑ ውስጥ እያወጣ ይዘረዝራል። በነዚያ ቃላትና ሐረጎች ቦታ ክርስቲያናዊ እሳቦች ያዘሉትን ቃላትና ሐረጎች ጨምሩ።

   ሥራቸውን በሚያጠናቅቁበት ጊዜ የመጀመሪያውን ትዕይንት፣ ፊልም ወይም መዝሙር ገለጻ ወይም ቃላት፣ ከዚያም አዲሱን ገለጻ ለቡድኑ አባላት እንዲያቀርቡ አድርግ።

4. የቡድን ዝማሬ።

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው።)

እግር ኳስ፣ የወረቀት አውሮፕላን፣ ጎልፍ፣ ካምፕ፣ መዝሙር - እነዚህ ሁሉ ሰዎች የሚዝናኑባቸው የተለያዩ መንገዶች ናቸው! የዛሬዎቹ ወጣቶች ከድሮዎቹ ወጣቶች እጅግ የተሻሉ አመቺ መዝናኛዎች አሏችሁ። ዕድገትና ሥልጣኔ ውብ አይደለምን? ነገር ግን ዕድገታችን አንዳንድ ችግሮችን አስከትሏል። ለመዝናናት ሲባል በየዓመቱ (በተለይ በምዕራባውያኑ ዘንድ) ለቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፣ ፊልሞች፣ ሙዚቃና መጽሔቶች ከፍተኛ ገንዘብ ይወጣል። ከነዚህ የመዝናኛ መንገዶች ብዙዎቹ ክርስቲያናዊ እሴቶችን አያንጸባርቁም።



መዝናኛችን ከክርስቶስ ጋር ያለንን ኅብረት ከአደጋ ላይ የማይጥል ለመሆኑ ምን ማረጋገጫ አለን? ለመዝናናት ስንል እስስ ገሰሉን ሁሉ መጠቀም አለብን ወይስ ከሁሉም የሚሻለውን ለመምረጥ ልንወስን እንችላለን?

የቱሚሶን ሕይወት ለአብነት ያህል ውሰድ። ቱሚሶ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄድ ነበር። ወላጆቹ ፊልሞችን እንዳይመለከትና ዓለማዊ ሙዚቃ እንዳያዳምጥ አጥብቀው ይቃወሙ ነበር። ከሚተላለፉት ፕሮግራሞች ግብረገባዊ ብልሹነት የተነሣ ቤተሰቦቹ ቴሌቪዥን ላለመግዛት በመወሰናቸው ቤታቸው ውስጥ ቴሌቪዥን አልነበረም። ቱሚሶ በቤት ከወላጆቹ ጋር የሚስማማ ቢመስልም፣ የነሱ ስሜቶች የዕብደት ሥራዎች ናቸው ብሎ ማሰብ ጀምሯል። ስለሆነም፣ ከጓደኞቹ ጋር በሚሆንበት ጊዜ ፊልሞችን ማየት፣ ዓለማዊ ሙዚቃዎችን ማዳመጥና ቴሌቪዥን መመልከት ጀመረ።

ሌላው ደግሞ ሉቃስ ነው። ወላጆቹ በመዝናኛ ሕይወቱ ላይ ምንም ዓይነት ገደብ አልጣሉበትም። ሉቃስ ክርስቲያን ከሆነ በኋላም ሳይቀር ስለሚመለከተውም ፊልምም ሆነ ስለሚሰማው ሙዚቃ ለአፍታ እንኳዋን አያስብም። ጓደኞቹ የሚመርጧቸውን የመዝናኛ ዓይነቶች ከመጠቀም ወደኋላ አይልም። በቤተክርስቲያን ውስጥ እስካለና ችግር ከሚያስከትሉ ነገሮች እስከራቀ ድረስ፣ የመዝናኛ ምርጫው እግዚአብሔርን የሚያሳስብ አይመስለውም።

በመጨረሻም ጊልበርት የሚባለውን ልጅ የመዝናኛ ሕይወት እንመለከታለን። ወላጆቹ ለረዥም ጊዜ የቤተክርስቲያን አባላት ስለነበሩ፣ ጊልበርት ትክክለኛውን ነገር እንዲመርጥ ይፈልጋሉ። ጊልበርት ክርስቲያን ከሆነ በኋላ ብዙ ዘፈኖች፣ መጻሕፍት፣ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችና ፊልሞች እሱ እንደ ክርስቲያን ከሚያምናቸው ነገሮች የሚለዩ መሆናቸውን ተገነዘበ። ጊልበርት ሁልጊዜም ማድረግ ያለበትን በትክክል ባያውቅም፣ የሚያዳምጣቸውን ሙዚቃዎችና ፊልሞች በጥንቃቄ ይመርጣል። ስለሚያስባቸውም ነገሮች ከወላጆቹና ከቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር ይነጋገራል። ነገሩ አስቸጋሪ ነው። አንዳንድ ጊዜ የትም ባይሄድ ወይም ምንም ባያደርግ ወይም ለመምረጥ ሳይሞክር ጥሩ ስሜት ያሳደረበትን ቢያደርግ ይቀለው እንደሆን ያስባል።

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

1. ከሦስቱ ልጆቹ ከሁሉም የሚሻለውን ውሳኔ ለማድረግ የሚችለውን ጥረት ሁሉ የሚያደርገው የትኛው ይመስልሃል?
2. እያንዳንዱ ልጅ ይህንኑ ምርጫ ያደረገው ለምን ይመስልሃል?

3. ከሦስቱ መካከል ካንተ ምርጫ ጋር የበለጠ የሚቀራረበው የትኛው ነው?
4. የእያንዳንዱ ምርጫ ጥንካሬዎችና አደጋዎች ምን ምንድናቸው?
5. በመዝናኛ ውስጥ ያለውን ጥሩና መጥፎ ነገር ለመመርመር አንድ ሰው ምን ዓይነት መምሪያዎችን ሊጠቀም ይገባዋል?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)

1. ሮሜ 12:2፡ መልካም የመዝናኛ ምርጫዎችን ለማድረግ መጠቀም የሚኖርብን የመጀመሪያው መርህ፡ የመዝናኛ ምርጫዎቻችን የምናምነውን ነገር እንድናመቻምች ሊፈትኑን አይገባም የሚል ነው። ጳውሎስ የዓለምን እሴቶች ተከትለን እንዳንመላለስ መክሮናል። አንድ የቴሌቪዥን ፕሮግራም፣ ፊልም፣ መዝሙር፣ ወይም መጽሐፍ ከእግዚአብሔር መመዘኛዎች የተለየ መልእክት የሚያስተላልፍ ከሆነ፣ ልንጠቀምበት አይገባም።
2. ፊልጵስዩስ 4:8፡ ሁለተኛው መርህ፡ «የምናስበውን እንሆናለን» የሚል ነው። ስለ ሕይወት የተሳሳተ አስተሳሰብ ወደ አእምሯችን ከጨመርን፣ አኗኗራችን ሁልጊዜም ማለት ይቻላል እነዚያን የተሳሳቱ ነገሮች ማንጸባረቁ የማይቀር ነው። ብዙውን ፈተናና ለመቋቋም ኃይል የሚያጡና በኃጢአት የሚሸነፉ ወጣቶች በሚመለከቷቸው ፊልሞች፣ በሚያነቧቸው መጻሕፍትና በሚሰሟቸው ሙዚቃዎች የተዳከሙ ናቸው። ይህ፣ «...ምናለበት?» ብሎ ከመጠየቅ ያለፈ ጥረት የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። አንዳንድ ነገሮች መጥፎ ላይመስሉ ቢችሉም፣ ጥሩ ላይሆኑ ይችላሉ (1ኛ ቆሮንቶስ 6:12)። ባለማቋረጥ የምናደርገው ነገር ትክክል መሆኑን ለማብራራት በምንፈልግበት ጊዜ፣ ቀድሞውኑ መልካም የሆነውን ሆን ብሎ ከመምረጥ ይልቅ የተሳሳተውን ነገር ለመከተል ምክንያት እናገኛለን። ስለሆነም፣ መልካም የሆነውን መሻትና መምረጥ አለብን።
3. መሳፍንት 16:16፡ ደሊላ የተባለች ሴት ሳምሶን የብርታቱን ምሥጢር እንዲነግራት ፈተነችው። ሳምሶን የደሊላን ዘዴ ለመቋቋም የሚያስችል ኃይል እንዳለው ያስብ ነበር። ነገር ግን ተሳሳተ። ከእሳት ጋር በመጫወቱ እሳቱ ፈጀው። ብዙውን ጊዜ አንድን ነገር ማየት፣ ማንበብ ወይም ማዳመጥ ተጽዕኖ አያሳድርብንም ብለን እናስባለን። ነገር ግን የሳምሶን ታሪክና 1ኛ ቆሮንቶስ 10:12 ከዚህ ድርጊት እንድንቆጠብ ይመክሩናል። የመዝናኛ ምርጫዎቻችን ኃጢአትን እንድንፈጽም በሚፈትኑን ጊዜ፣ መሸሽ አለብን። መርህ ቁጥር 3፡ «መዝናኛ በጠንካራ ፈተና ውስጥ ሊከተን አይገባም» የሚል ነው።



4. ዕብራውያን 6:12፡ ክርስቶስ ሚዛናዊ የሆነ ሕይወት እንድንኖር ይፈልጋል። «መዝናናት የሌለበት ሥራ» እንደሚያሰለች ሁሉ፣ «ሥራ የሌለበት ጨዋታም» ለእግዚአብሔር መንግሥት ልናበረክት የምንችለውን አስተዋጽኦ ሊያባክን ይችላል። መዝናኛ ጊዜያችንን ሁሉ በሚወስድበት ጊዜ ክፉ ተጽዕኖ ያሳድርብናል። የመጨረሻው መርሃችን፣ «መዝናኛ ጊዜያችንን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር የለበትም» የሚል ነው።

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

ተማሪዎችህ እጅግ ተወዳጅ የወጣቶች የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች፣ ፊልሞች፣ ዘፈኖችና መጻሕፍት የትኞቹ እንደሆኑ እንዲነግሩህ ጠይቃቸውና፣ «ይኼ መዝናኛ ለእናንተ ልክ ይሆን?» ስትል አክለህ ጠይቃቸው። ከላይ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች ውስጥ የተመለከትናቸውን መርሆች ለተማሪዎችህ መለስ ብለህ አስታውሳቸው። አንዳንዶቻቸው የሚያደርጉት ነገር ለሌሎች የማይሞከር ሊሆን እንደሚችል ግለጽላቸው። በመጽሐፍ ቅዱስና በመንፈስ ቅዱስ ምሪት፣ እያንዳንዳቸው ለየራሳቸው መወሰን አለባቸው። በወሰደው የመዝናኛ ምርጫ የተሻለ ሰው ወይም ጠንካራ ክርስቲያን ለመሆን የበቃ ሰው ስለ አንድ የመዝናኛ ምርጫ ምሳሌ እንዲሰጥ አድርግ።

ሰ. መዝጊያ - የመዝናኛ ምርጫ በሚገጥመን ጊዜ አምስት ጥያቄዎችን ለራሳችን ማቅረብ ይኖርብናል፡ 1) ይህ ከክርስቶስ ጋር ያለኝን ግንኙነት ያደናቅፈዋል? 2) የመጽሐፍ ቅዱስን አስተምህሮ ይጥሳል? 3) በጌትነት ሊገዛኝ ይችላል? 4) ክርስቲያናዊ ምስክርነቴን ያበላሸዋል? 5) ጠቃሚ ነውን?

በጸሎት ፈጽም።

## እግባብነት የጎደለው የፍቅር ግንኙነት

ከኬንዶል ፍራንክሊን

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. ለፍቅር ግንኙነት የምንመርጠው ሰው ማንነት እግዚአብሔርን ያሳስበዋል::
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች ለፍቅር ግንኙነት የሚቀጥሩት ወይም የሚያጩት ሰው ማንነት አስፈላጊ መሆኑን ለማስገንዘብ::
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የተዘጋጀው ወጣቶች የፍቅር ግንኙነት በሚጀምሩበት ጊዜ የፍቅረኛቸውን ማንነት በተመለከተ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባቸው ለማሳየት ነው:: ማስታወሻ፡ የወንድና ሴት ለብቻቸው አብሮ ማሳለፍ በአንዳንድ ባሕሎች ተቀባይነት ያለውና የተመሰገነ ተግባር ቢሆንም፣ ይህ ግን በዓለምአቀፍ ደረጃ ሰዎች የሚለማመዱት ነገር አይደለም:: አንተ ባለህበት ስፍራ ሁኔታው እንደዚህ ዓይነት ከሆነ፣ ይህን ክፍል ስለ ትጭጭት እንደሚናገር አድርገህ ከአካባቢህ ጋር ልታዛምድ ትችላለህ::
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. እርሳሶች፣ ስቲኪኒዎች፣ ሁለት ትናንሽ ቀለበቶች::

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል::)

1. የምትወደኝ ከሆነ፣ የኔ ቆንጆ፣ ፈገግ በልልኝ:: አንድ ልጅ ምረጥ:: የተመረጠው ልጅ በክፍሉ ውስጥ ወደሚገኙት ልጆች በመሄድ፣ «የምትወደኝ ከሆነ፣ የኔ ቆንጆ፣ ፈገግ በልልኝ» ይላል:: የተጠየቀው ልጅ፣ «እወድሃለሁ፣ የኔ ቆንጆ፣ ግን ፈገግ ማለት አልችልም» ሲል ሳይስቅና ፈገግ ሳይል ይመልስለታል:: ፈገግ ለማስባል የሚሞክረው ልጅ ግን ጥረቱን መቀጠል ይኖርበታል::
2. የቀለበት ቅብብሎሽ:: እኩል አባላት የሚገኙባቸውን ሁለት ቡድኖች አሰልፋቸው:: ለሁለቱም ቡድኖች አባላት በሙሉ ስቲኪኒዎችን አድልና ለእያንዳንዱ ቡድን አንዳንድ አነስተኛ ቀለበቶች ስጣቸው:: ይህንን ጨዋታ ማካሄድ የሚቻለው በሁለቱም ቡድኖች ውስጥ የሚገኙት ልጆች በሙሉ ስቲኪኒዎቻቸውን በአፋቸው እንዲይዙ በማድረግ ነው:: የስቲኪኒው አብዛኛው አካል ከአፍ ውጭ ይሆናል:: ቀለበቱ በመጀመሪያው ልጅ ስቲኪኒ ላይ ይደረጋል:: እሱም እጁን ሳይጠቀም ወደሚቀጥለው ልጅ ስቲኪኒ ላይ ያስቀምጠዋል:: ሁለተኛውም ልጅ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀለበቱን ለቀጣዩ የቡድኑ አባል ያስተላልፋል:: ቀለበቱ ከወደቀ ቡድኑ ጨዋታውን እንደ አዲስ ከመጀመሪያው ልጅ ይጀምራል:: አሸናፊው ቡድን ቀለበቱን ወደ መጨረሻው የቡድኑ አባል በቀዳሚነት ያስተላለፈ ይሆናል::
3. የቡድን ዝማሬ::



ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው::)

ከጥቂት ዓመታት በፊት ሳም የሚባል የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪ ነበር:: ሳም የሁለት ሜትር ቁመትና የ120 ኪሎግራም ክብደት የነበረው ግዙፍ ወጣት ነበር:: በትምህርት ቤቱ ኮከብ የእግር ኳስ ተጨዋች ሲሆን፣ ከመሀል ወደፊት እየተመላለሰ በማጥቃት ለቡድኑ ቁልፍ ሚና ይጫወታል:: እሱ ካለበት ቡድን ጋር የሚጋጠሙ ሌሎች ቡድኖች አጥብቀው የሚፈሩት ሳም፣ በጨዋታ ችሎታው በአካባቢው ሁሉ የታወቀ ነበር:: ሳም በትምህርት ቤቱ ውስጥ ታዋቂነትን ያተረፈው በአንድ ነገር ብቻ አልነበረም:: ሳም ኃይለኛም ነበር:: ብዙ ጊዜ ጉልበቱን ጥበብ በጎደለበት መንገድ ስለሚጠቀም፣ ችግር ውስጥ ይገባ ነበር:: ፀጉሩ የተንጨባረረ ሲሆን፣ በትምህርት ቤቱ ውስጥ ከሚገኙ አብዛኞቹ ሴቶች በላይ የረዘመ ነበር:: ይህም ሆኖ ከልጁ ግዙፍነትና ጥንካሬ የተነሣ ይመስላል ማንም አይቀልድበትም::

አሠልጣኞች ከያቅጣጫው እየመጡ ችሎታውን በመመልከት ለዩኒቨርስቲው ተመርጦ እንዲጫወት ለማድረግ ያስቡ ነበር:: አንድ ቀን የሳም ትምህርት ቤት ከቀንደኛ ተፎካካሪው ጋር ግጥሚያ አደረገ:: በዚህ ጊዜ ሳም አንዲት የሌላ ትምህርት ቤት ተማሪ ተመለከተ:: ልጅቱ ውብ ነበረች! ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሳምና ልጅቱ መገናኘት ጀመሩ:: ነገር ግን ልጅቱ በሳም ላይ ያስከተለችው ተጽእኖ መልካም አልነበረም:: የሳምን ጓደኞች፣ ወላጆች ወይም የቤተክርስቲያን ቡድኖች አትወድም ነበር:: ቢሆንም ሳም አልተለያትም:: ወላጆቹ በምርጫው ደስተኞች አልነበሩም:: ከልጅቱ ጋር እንዳይገናኝ ቢጠይቁትም፣ ሊሰማቸው አልቻለም::

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ሳም የሌላ ትምህርት ቤት ተማሪ ለፍቅር መፈለግ አልነበረበትም:: ልጅቱ ሳም የሚያመልከውን አምላክ እንኳዋን አታመልክም ነበር:: እሷ የምታመልከው የዓሣ መልክ ያለው ጣዖት ነበር:: የሳምን ቅርስ፣ ሃይማኖትም ሆነ ሰዎች ከማይፈልግ ቤተሰብ ነበር የተገኘችው:: ነገር ግን ከልጅቱ ጋር የነበረውን ግንኙነት ለማቋረጥ ባለመፈለጉ የኋላ ኋላ ራሱን ጎድቷል::

የሳም ታሪክ በዚህ ብቻ አላበቃም:: በችሎታው የቀኑ የሌላ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ሊረብሹት ሲሞክሩ፣ የቡድኑ ደጋፊዎች በያዙት አሻንጉሊት መታቸው:: ይህም ሆኖ፣ ሳም ከዚህ ሁሉ ለሕይወቱ ጠቃሚ ትምህርት አልተማረም:: በቤተክርስቲያኑ ውስጥ የነበሩትን እያሌ ሴት ልጆች ንቆ፣ ደሊላ ከተባለች ልጅ ጋር መገናኘት ጀመረ::

ደሊላም በንዴት ከጠፉት አሠልጣኞችና የትምህርት ቤቷ ተጨዋቾች ጋር አንዳንድ ስብሰባዎችን ካደረገች በኋላ፣ ሳም የብርታቱን ምሥጢር እንዲያጋልጥ ልታግባባው ቆረጠች፡፡ ስለሱ ወይም ስለ ስሜቶቹ ደንታ አልነበራትም፡፡ ሳም፣ «ለዚህ ታላቅ የእግር ኳስ ችሎታህ ምሥጢሩ ምንድነው?» ስትል ጠየቀችው፡፡ ሦስት ጊዜ የውሸት መልሶችን ሰጣት፡፡ በመጨረሻም፣ ደሊላ እያለቀሰች ምሥጢሩን እንዲነግራት ስትለምነው፣ ሳም ለአምላኩ ስለገባው ቃል ኪዳን ነገራት፡፡ በዚህ ጊዜ ደሊላ ፀጉሩን ላጨችበት፡፡ ይህም ጉልበቱንና የእግር ኳስ ችሎታውን አሳጣው፡፡ ሳም ሁሉንም አጣ፡፡ ፀጉሩን፣ ከአምላኩ ጋር የነበረውን ግንኙነት፣ የኮሌጅ ስኮላርሽፑን፣ ዓይኖቹንና በመጨረሻም ሕይወቱን ሊያጣ ችሏል፡፡ ይህም የሆነው ለሱ ከማትሆን ሴት ጋር በማሳለፉና በማግባቱ ነው፡፡

*መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙ*-ባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ፡፡)

1. ክርስቲያኖች ካልሆኑ ሰዎች ጋር የፍቅር ግንኙነት *መመሥረት* ስሕተት ነውን?
2. ፍጹም ከማያውቁት ሰው ጋር የፍቅር ግንኙነት *መመሥረት* ትክክል ነውን?
3. ወላጆቻችን ለፍቅር ግንኙነት ስለምንመርጠው ሰው አስተያየት *መስጠት* አለባቸውን?
4. የፍቅር ግንኙነት *መመሥረት* ያሰብህ ልታገባ የምትፈልገውን ሰው ብቻ *መሆን* አለበትን?

*ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች*

1. ሮሜ 12:1-2፡ በሕይወታችን ገጽታዎች ሁሉ እግዚአብሔርን ማስከበር *የፍቅር ቀጠሮን/ትጭጭትንም* ይጨምራል፡፡ ለፍቅር የምንቀጥረውን ሰው ስለመምረጥ በምናስብበት ጊዜ ልናስታውሳቸው የሚገቡ መመዘኛዎች አሉ፡፡ እንደ ዓለማውያን ለተሳሳቱ ዓላማዎች ወይም ምክንያቶች ሰዎችን መቅጠር የለብንም፡፡ እኛ ከዓለም የተለየንና ከዓለም በላይ ላቅ ብለን የምንታይ ሰዎች ነን፡፡ በተቻለ አቅም እርሱን በቅርበት በምንከተልበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር *ማንን* ለዚህ ዓይነቱ ግንኙነት መምረጥ እንዳለብን ያሳየናል፡፡ ስለሆነም፣ የርሱ በረከት ከታከለበት የፍቅር ግንኙነትን *መመሥረት* መልካም አምንታዊ ገጠመኝ ሊሆን ይችላል፡፡
2. *መዝሙር* 1:1-2፡ ሁሉም ዓለማውያን ግብረገባዊነት የጎደላቸው መጥፎ ሰዎች አይደሉም፡፡ ደግ፣ ጨዋ፣ የወዳጅነት መንፈስና ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ዓለማውያን አሉ፡፡ ይህም ሆኖ፣ ክርስቶስን በማያውቁ ሰዎች ምክር ልንመላለስ አንችልም፡፡ እኛ



ከማያምኑ ሰዎች የተለየን ነን፡፡ ልክ እንደ ሳምሶን በማያምኑ ሰዎች ተጽዕኖ ሥር መውደቁ ቀላል ነው፡፡
3. 2ኛ ቆሮንቶስ 6:14-16፡ ጳውሎስ «መጠመድ» ሲል ምናልባትም «መጋባት» ማለቱ ይሆናል፡፡ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ክርስቲያኖች አብረዋቸው የሚያሳልፉትን ሰዎች የመምረጥ ሃላፊነት እንዳለባቸው ያስረዳል፡፡ ለክርስቲያኖች ዋንኛው መመዘኛ አብረው የሚያሳልፉት ሰው በክርስቶስ ማመኑ ነው፡፡ የማያምኑትን ሰዎች በወንጌል መድረስ ቢኖርብንም፣ በአብዛኛው ኅብረትን የምናደርገው በክርስቶስ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ከሆኑት ወገኖች ጋር መሆን አለበት፡፡

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ፡፡)

*1.* ከዓለማውያን ጋር አብሮ ማሳለፍ ስሕተት ነውን? *(ሁሉም ዓለማውያን አብረውን በማሳለፋቸው በብልጠት ተጠቃሚ ለመሆን የሚሞክሩ መጥፎ ሰዎች አይደሉም፡፡ ክርስቶስ እኛ «የምድር ጨው» መሆናችንን ገልጾአል (ማቴዎስ 5:13)፡፡ ስለሆነም፣ ከክርስቲያኖችም ሆነ ክርስቲያኖች ካልሆኑ ሰዎች ጋር አብረን ማሳለፍ አለብን፡፡ ይህም ሆኖ፣*

*ሀ. ተቃራኒ ጾታ ያላቸውን ሰዎች በክርስቶስ ወዳለው እምነት ለማምጣት ሲባል ለብቻ መቅጠሩ ተገቢ አይሆንም፡፡ በሌላው ሰው ላይ መንፈሳዊ ግንኙነት መጀመሩ አስተዋይነት የታከለበት ተግባር አይደለም፡፡ ብዙውን ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ግንኙነት በአሳብ አለመገናኘትን፣ በስሜት መጎዳትንና መንፈሳዊ ግድየለሽነትን ያስከትላል፡፡*

*ለ. ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፣ የተለየን ሰዎች ነን፡፡ ስለሆነም፣ ከዓለማውያን ጋር መጠመድ የለብንም (2ኛ ቆሮንቶስ 6:14)፡፡ ይህ ያላቻ ጋብቻ ነው የሚሆነው፡፡ ለዚህ ምክንያቱ እኛ ከዓለማውያን የተሻልን መሆናችን ሳይሆን፣ ሕይወታችንን የምንኖረው ከነሱ ለተለየ ዓላማ በመሆኑ ነው፡፡ እነሱ ለራሳቸው ሲኖሩ፣ እኛ ግን ለአምላካችን እንኖራለን፡፡ ከማያምን ሰው ጋር የፍቅር ግንኙነት መመሥረቱ ግራ መጋባትን፣ ሥቃይን ወይም የልብ ቁስለትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ይህንን የሚያደርጉ ክርስቲያኖች በስሜታቸው እንዳይታለሉ መጠንቀቅ አለባቸው፡፡ በዚህ ዓይነት መንገድ መታለሉ ቀላል ነው፡፡ ዓለማዊ ከሆኑት ሰዎች ጋር የፍቅር ግንኙነት የመመሥረትን ልማድ ካዳበርህ፣ የኋላ ኋላ ዓለማዊ የሆነ ሰው የማግባት ዕድልህ ሰፊ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ትክክል አይደለም (2ኛ ቆሮንቶስ 6:14)፡፡ መጥፎ ልማድ አትከተል፡፡)*

2. *ወላጆቻችን ለፍቅር ግንኙነት ስለምንመርጠው ሰው አስተያየት መስጠት አለባቸውን? (ከወላጆቻችን ጋር መልካም ግንኙነት ካለን፣ ለፍቅር ጓደኝነት ስለምንመርጠው ሰው የነሱን ምክር፣ አንዳንድ ጊዜም ድጋፋቸውን ልንጠይቅ እንችላለን:: ወላጆችህ የፍቅር ግንኙነትህን መደገፋቸው ትልቅ ነገር ነው:: ሳምሶን የወላጆቹን ፍላጎትና ተቃውሞ ጥሶ ልቡ የፈቀደውን አደርጓል:: ነገር ግን የነሱ ሰሳብ ትክክል ነበር:: ምክራቸውን ቢሰማ መልካም ነበር:: «እናትህንና አባትህን አክብር» የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አስታውስ - ዘጸአት 20:12)::*
3. *የፍቅር ግንኙነት መመሥረት ያለብህ ልታገባ ከምትፈልገው ሰው ጋር ብቻ መሆን አለበትን? (የፍቅር ግንኙነትን መመሥረት የጋብቻ ዝግጅት ነው:: የምንፈልገውን ዓይነት ሰው ከምናገኝባቸው መንገዶች አንዱ ከተለያዩ ሰዎች ጋር አብሮ በማሳለፍ ነው:: አብረን በማሳለፍ የኋላ ኋላ ማንን እንደምናገባ ብዙ ነገሮችን ልናውቅ እንችላለን:: አብረውን የሚያሳልፉትን ሰዎች ሁሉ የትዳር ጓደኞቻችን ሊሆኑ እንደሚችሉ በማሰብ በአክብሮት ማስተናገድ አለብን:: በእግዚአብሔር የተፈጠሩ በመሆናቸው እርሱ እንደሚወዳቸው አድርገን ልንወዳቸው ይገባል:: ሁሉንም በአክብሮት አስተናግድ::)*

ለ. *መዝጊያ* - ወጣቶችህ በጸጥታ ስለሚከተሉት ነገሮች እንዲጸልዩ አድርግ::

1. እግዚአብሔር የፍቅር ግንኙነታችሁ ጌታ እንዲሆን
2. እግዚአብሔር ከተቃራኒ ጾታዎች ጋር የምታሳልፏቸውን ገጠመኞች እንዲባርክ
3. እግዚአብሔር ከማን ጋር የፍቅር ግንኙነት *መመሥረት* እንዳለባችሁ እንዲያሳያችሁ
4. ምሪቱን ትቀበሉ ዘንድ እንዲያግዛችሁ
5. አብረዋችሁ ለሚያሳልፉት ሰዎች ማበረታቻ እንድትሆኑ

ለፍቅር ግንኙነት ሰዎችን በምትመርጡበት ጊዜ ጥንቃቄ አድርጉ:: ይኼ በጣም አስፈላጊ ነው! ስትል አስታውሳቸው::



## ስሜቶች፡ ጠቋሚዎች ወይስ አዛዦች?
ከአለን ስኮት

*ሀ. የመሪው መምሪያዎች*

1. ዋና አሳብ .. እግዚአብሔር ስሜቶቻችን በሕይወታችን ውስጥ ጠቋሚዎች እንጂ አዛዦች እንዳይሆኑ አድርጎ ፈጥሮናል::
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች ስሜቶቻቸው የሕይወታቸውን ተግባራትና ውሳኔዎች እንዲቆጣጠሩ መፍቀድ እንደሌለባቸው ለማስተማር::
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ወጣቶቻችን የሚኖሩት የስሜቶች መለዋወጥ በሚታይባት ዓለም ውስጥ ነው:: አንዳንድ ጊዜ የስሜትን አቀበት ይወጡና ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ ወደ ሸለቆ ይወርዳሉ:: ብዙውን ጊዜ ተግባሮቻቸውና ውሳኔዎቻቸው በፍጥነት ይለዋወጣሉ:: ብዙ ወጣቶች ስሜታቸውን ተከትለው አንድን እርምጃ መውሰድ እንደሌለባቸው አይገነዘቡም:: ብዙውን ጊዜ ወጣቶች እንደ ጌኛ ከሚጋልበው ስሜታቸው ሳቢያ በወጥመድ የመያዝ ስሜት ይጫናቸዋል:: ይህም በተደጋጋሚ ስሜቶቻቸውን እንዲፈሩ ወይም እንዲያፍሩ ያደርጋቸዋል:: ለዚህም ምክንያቱ ስሜቶቻቸው የሚያስከትሏቸውን ተግባራት ለመቆጣጠር የማይችሉ መስሎ ስለሚሰማቸው ነው:: ይህ ትምህርት ወጣቶችህ ከተገቢ ስሜቶች የሚመነጩትን ተግባራት የመቆጣጠር ኃላፊነት እንዳለባቸው ያስተምራል:: ስሜቶች ከእግዚአብሔር የተሰጡን በመሆናቸው ወጣቶች ሊክዷቸው አይገባም:: ነገር ግን ለስሜቶቻቸው ምላሽ በመስጠት በሚያከናውኗቸው ተግባራት ስሜቶቻቸውን ማምላቀቅ የለባቸውም::
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. በቦርሳ ውስጥ የተደረጉ ትናንሽ ፊኛዎች (ባሉኖች)፣ የእግር ኳስ ወይም ቮሊቦል ወይም ሌላ ክብ ለስላሳ ነገር::

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል::)

1. *ፊኛ የማፈንዳት ውድድር:: ለእያንዳንዱ ቡድን አንዳንድ ፊኛ* አድል:: የጨዋታው ዓላማ የትኛው ቡድን ፊኛውን *መጀመሪያ እንደሚያፈነዳ መመልከት ነው (ትናንሽ ፊኛዎችን*

ምረጥ)፡፡ አንድ የቡድኑ አባል ፊኛውን አንድ ጊዜ ከነፋው በኋላ ለቀጣዩ ልጅ ያስተላልፋል፡፡ ፊኛው ከሰው ወደ ሰው በሚተላለፍበት ጊዜ ከውስጡ የነበረው አየር ከቀነሰ፣ ቡድኑ ጨዋታውን እንዲቀጥል አበረታታ፡፡ የቡድኑ አባላት በሙሉ ከነፉ በኋላ ፊኛው ካልፈነዳ ከእንደገና ይጀምሩ፡፡ የማይፈነዱ ጠንካራ ፊኛዎች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ አትዘንጋ፡፡ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ካጋጠመህ ከሁሉም የሚበልጥ ፊኛ ያለው ቡድን አሸናፊ መሆኑን ተናገር፡፡

2. ቃላትን የመተወን ጨዋታ፡፡ ወጣቶቹን በትናንሽ ቡድኖች ከፋፍላቸውና ሁሉም ቡድኖች ከአንተ በእኩል ርቀት ላይ እንዲቀመጡ አድርግ፡፡ ከዚያም ከየቡድኑ አንዳንድ ሰው ወደ አንተ እንዲመጣ ጋብዝ፡፡ ሲመጡም በተግባር (በተውኔት) የሚያሳዩትን ቃል ንገራቸው፡፡ ቃሉን ከአንተ ከሰሙ በኋላ ወደ ቡድናቸው ሮጠው በመሄድ ተውኔቱን ይሠራሉ፡፡ ቡድኑ ቃሉን በትክክል ከገመተ በኋላ፣ ተውኔቱን የሠራው ልጅ ተመልሶ ወደ አንተ ሲሮጥ ይመጣል፡፡ መጀመሪያው አንተ ጋ የደረሰው ልጅ የሚገኝበት ቡድን የዙሩ አሸናፊ ይሆናል፡፡ በተውኔት የሚታዩ ነገሮች የስሜት ቃላት እንዲሆኑ አድርግ፡፡ ከነዚህም መካከል፣ *ደስታ፣ ኃዘን፣ ከመጠን ያለፈ ደስታ፣ ትካዜ፣ ቁጣ፣ ድካም፣ ፍቅርና ጥላቻ* ይገኙባቸዋል፡፡

3. ኪስን የማስተላለፍ ጨዋታ፡፡ ወንበሮችን በሁለት ረድፍ አድርገህ ደርድር (የሚቀመጡባቸው ሰዎች ፊት ለፊት እንደሚተያዩ አስተውል)፡፡ በሁለቱ ረድፎች መካከል የአንድ ሜትር ያህል ርቀት መኖር አለበት፡፡ ሁለቱ ቡድኖችህ ፊት ለፊት ተፋጠው እንዲቀመጡ አድርግ፡፡ የጨዋታው ዓላማ ቡድኖቹ ኪስ ወደ መጨረሻው የቡድናቸው አባል (ግብ) በፍጥነት ቀድመው ማድረሳቸውን መመልከት ነው፡፡ ሁሉም ሰው ክንዶቹን ከወንበሩ ኋላ ማድረግ አለበት፡፡ ኪሱን ከመስመሩ መሀል ላይ በመጣል ጨዋታውን ጀምር፡፡ ለቅድመጥንቃቄ ተማሪዎቹ ጫማቸውን እንዲያወልቁ ልታደርግ ትችላለህ፡፡

4. የቡድን ዝማሬ፡፡

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው፡፡)
ብዙውን ጊዜ ስሜቶች ግራ የሚያጋቡ ነገሮች ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ይውጡችኋል፡፡ ብዙ ጊዜ ደግሞ ያስፈሯችኋል፡፡ እንደ ደስታ፣ ሐሤት፣ ፍቅርና ፍልቅልቅታ ያሉ ጥሩ ስሜቶች አሉ፡፡ እንደ ኃዘን፣ ቁጣ፣ ቅንዓት፣ ጉዳትና ብቸኝነት የመሳሰሉ አሠቃቂ ስሜቶች አሉ፡፡ ግን ስሜቶቻችንን ምን ልናደርጋቸው ይገባል?
በስሜቶቻቸው ተሸንፈው የተወሰዱ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ከስሜታቸው ገፋፊነት የተነሣ በኋላ የሚጸጸቱባቸውን ነገሮች



ያደርጋሉ፡፡ ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፣ እግዚአብሔር ስሜቶችን ያሉን ፍጡሮች አድርጎ እንደሠራን እንገነዘባለን፡፡ ነገር ግን ብዙውን ጊዜ አሉታዊ ስሜቶች በሚደርሱብን ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታችን የተሸነፍን ይመስለናል፡፡
ጀሽዋ ክርስቲያን ቢሆንም፣ በሲልቬይን ላይ መቅናቱ ይታወቀዋል፡፡ ሲልቬይን በእግር ኳስ ቡድኑ ውስጥ አሠልጣኙ የሚወዱት ተጨዋች ነው፡፡ ሲልቬይን ጥሩ ተጨዋች ቢሆንም፣ ጀሽዋ አሠልጣኙ ለምን ያን ያህል እንደሚያንቆለጳጵሱት ሊገባው አልቻለም፡፡ ከዚህም በላይ ወጣት ሴቶች ሲልቬይን የራሳቸው ለማድረግ ይሽቀዳደማሉ፡፡ ጀሽዋ ሲልቬይን ባይኖር ኖሮ አሠልጣኙ ፓከር ለሱ የበለጠ ትኩረት ይሰጡ እንደነበር ማሰቡን ቀጠለ፡፡
ሲልቬይን አዲስ ጫማውን አድርጎ ለልምምድ በመጣ ጊዜ የጀሽዋ ትዕግሥት ተሟጠጠ፡፡ ጫማውን ሰው ሁሉ አደነቀለት፡፡ ልጆቹ ሜዳውን እያዘጋጁ ሳለ ጀሽዋ የሲልቬይንን አዲስ ጫማ ደበቀበት፡፡ ጀሽዋ ሲልቬይን የሚዋረድበትን ትምህርት ማግኘት አለበት ሲል አሰበ፡፡ ጀሽዋ ጫማዎቹን ሲልቬይን የኋላ ኋላ ሊያገኝ በሚችልበት ስፍራ አስቀመጠው፡፡ አሁን አሠልጣኙ ጀሽዋ ያለ ሲልቬይን ሊጫወት እንደሚችል ያያሉ፡፡ ይህ ለአሠልጣኙ ፍጹም ነው የተባለው ተጫዋቻቸው ጫማውን እንደሚያጠፋም የሚያሳይ አጋጣሚ ነበር፡፡ ጀሽዋ ባደረገው ነገር ደስ ተሰኘ፡፡

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ፡፡)

1. ስለ ጀሽዋ ምን ታስባለህ?
2. ጀሽዋ የሚታገለው ከምን ስሜት ጋር እንደነበርና ምን ያህል እንደተቆጣጠረው ተናገር፡፡
3. ሲልቬይን ያገኘው ነገር የሚገባው ልጅ አይደለምን?
4. ጀሽዋ የተሳሳተው ከምን ላይ ይመስልሃል?
5. ጀሽዋን ብትሆን ምን ታደርግ ነበር?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው፡፡)

1. 2ኛ ሳሙኤል 11፡2-15፡ ይህ ታሪክ ዳዊት በስሜቶችና በወሲባዊ ፍላጎት ገፋፊነት ኃጢአትን እንደፈጸመ ይናገራል፡፡ እግዚአብሔር ለሰዎች ወሲባዊ ፍላጎቶችን ቢሰጥም፣ ይህንኑ ፍላጎታቸውን ያረኩ ዘንድ የጋብቻ መቀቅር አዘጋጅቶላቸዋል፡፡ ዳዊት ኦሪዮን በጦር ሜዳ ላይ እንዲገደል በማድረግ ተግባሩን ለመሸፈን ሞክሯል፡፡ ይሁንና፣ ዳዊት በስሜት ገፋፊነት ለፈጸማቸው ተግባራት ዋጋ ከፍሏል፡፡ በኋላም ለፈጸመው ኃጢአት

እንደተጸጸተና በእግዚአብሔር ፊት ጥፋቱን እንደተናዘዘ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እናነባለን።

2. ሮሜ 6:6-7፣ 11-12፣ 14: እነዚህ ጥቅሶች የኃጢአት ፍላጎቶችንና ስሜቶችን ለመከላከል የሚያስችል ኃይል እንዳለን ያስረዳሉ። እግዚአብሔር ለጽድቅ ጸንተን እንቆም ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ኃይልን ይሰጠናል። ስለሆነም፣ የስሜቶቻችን ባሪያዎች መሆን የለብንም። ስሜቶቻችን ምን እንደምንሠራ ማዘዝ የለባቸውም። አንድ ነገር ትክክል አለመሆኑን ሊጠቁሙን ቢችሉም፣ ስሜቶቻችን ያሉትን ተግባር መፈጸም የለብንም።

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

1. የዳዊት ስሜቶች ጠቋሚዎች ነበሩ ወይስ አዛዦች?
2. ዳዊት እርምጃ እንዲወስድ ያነሣሡት ሁለት ስሜቶች ምንና ምን ነበሩ?
3. ሮሜ 6 የክፉ ምኞቶቻችን ባሪያዎች መሆን እንደሌለብን የሚያስተምረው ለምንድነው?
4. ከሮሜ 6 አንጻር፣ ጀሽዋ ምን ማድረግ ነበረበት?

ሰ. መዝጊያ

የስሜቶቻችሁና የፍላጎቶቻችሁ ባሪያዎች ሆናችሁ ታውቃላችሁ? እግዚአብሔር እርዳታውን በመጠየቅ ነጻ ልትወጡ እንደምትችሉ ይናገራል። ፈተና ስሜታችሁን መግዛት እንደማትችሉ ሲነግራችሁ፣ በሮሜ 6 የተሰፉ ቃሎች ላይ ልትደገፉ ትችላላችሁ። እነዚህን ቁልፍ እውነታዎች አስታውሱ።

1. ስሜቶች ጠቋሚዎች እንጂ አዛዦች አይደሉም። የምትወስዱትን እርምጃ የምትመርጡት እናንተው ናችሁ።
2. «እንግዲህ፣ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ» (ሮሜ 6:12)።


ለስሜታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል የጽድቅን ምላሽ ለመስጠት ምረጡ።

በጸሎት ፈጽም። ወጣቶቹ ዳዊት እንደደረገው ለእግዚአብሔር የንስሐ ጸሎት እንዲጸልዩ አበረታታቸው። ከእንግዲህ የኃጢአት ምኞቶቻቸው ባሪያዎች እንዳይሆኑ እግዚአብሔር ኃይልን ይሰጣቸው ዘንድ እንዲጠይቁ በጸሎት ምራቸው።

ሸ. ንቁ ተሳትፎ ለሚያደርግ ቡድን



ከላይ የተጠቀሰውን ቃላት የመተወን ጨዋታ ባካሄዱበት ወቅት ወጣቶቹ ስሜቶችን ለመግለጽ የተጠቀሙባቸውን እንቅስቃሴዎች እንዲነግሩህ ጠይቃቸው። ስሜቶቻችን የሚነግሩንን ተግባራዊ ማድረግ አለብን ወይ? ብለህ ጠይቃቸው። ከዚህ ቀጥሎ ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች ዝለቅ።



## ጭንቀትን መከላከል

ከሚካኤል ኤ. ፒትስ

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. ሁሉም ወጣቶች በሆነ መልኩ ጭንቀት ያጋጥማቸዋል፡፡ ጤናማና አርኪ ሕይወት ለመኖር ከተፈለገ ጭንቀትን እንዴት መረዳትና መከላከል እንደሚቻል መማሩ ጠቃሚ ነው፡፡
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች ከራሳቸውም ሆነ ከጓደኞቻቸው የጭንቀትን ምልክቶች ለይተው እንዲያውቁ ለማገዝና ከጭንቀት ለመላቀቅ የሚያስችሉትን መምሪያዎችና መረዳት ለመስጠት፡፡
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ጭንቀት ከሚያጋጥሙን ለውጦችና ስሜቶች ሳቢያ የሚከሰት ተለምዷዊ ምላሽ ነው፡፡ ከግለሰባዊ ማንነታቸው ባሻገር፣ ወጣቶች ጭንቀት ያጋጥማቸዋል ወይም ጓደኛቸው ከጭንቀት የተነሣ ከሕይወት ጋር ግብግብ እየገጠመ መሆኑን ይገነዘባሉ፡፡ ወጣቶች ጭንቀት ምን እንደሆነ፣ የጭንቀትን ምልክቶች እንዴት ለይተው እንደሚያውቁና ጭንቀትን እንዴት እንደሚከላከሉ ማወቅ አለባቸው፡፡
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. እርሳሶች፣ ወረቀት፣ የሲባጎ/የሱፍ ክር/የጥጥ ጥቅልል፡፡

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል፡፡)

1. *መዝገበ ቃላት፡፡* ተማሪዎችህ የማያውቋቸውን ከ5-10 የሚሆኑ ቃላት ከመዝገበ ቃላት ምረጥና ሁሉም ሊያዩ በሚችሉበት ስፍራ (ጥቁር ሰሌዳ ላይ) ጻፍ፡፡ ከዚያም ለእያንዳንዱ ተማሪ ወረቀቶችን አድል፡፡ ተማሪዎቹ የቃላቱ ፍች ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን ነገሮች እንዲጽፉ ንገራቸው፡፡ ወረቀቶቹን ሰብስብና ተመሳሳይ የሆኑትን ቃላት አንድ ላይ አድርግ፡፡ ከትክክለኛ ፍች ጋር ከ4-5 የሚሆኑ የነርሱን ትርጉሞች በክፍሉ ውስጥ አንብብ፡፡ ተማሪዎቹ ትክክለኛውን ፍች እንዲገምቱ ጠይቃቸው፡፡
2. የስሜት *መግለጫ፡፡* ተማሪዎችህን ከ4-6 አባላት እንዲኖራቸው አድርገህ ከፋፍል፡፡ ከዚያም አንድን ስሜት ጥቀስ (እንደ ፍቅር፣ ጥላቻ፣ ቁጣ፣ ፍርሃት ባሉት ግልጽ ስሜቶች ጀምር፡፡) እንዳንዱ ቡድን የተነገረውን ስሜት በአባላቱ ሰውነት ተጠቅሞ በቅርጻቅርጽ መልክ (አብስትራክት ወይም ግልጽ) ያሳያል፡፡ ቡድኖቹ ቅርጻቅርጻቻቸውን እንዲያሳዩ በቂ ጊዜ ስጣቸው፡፡ ከዚያም ተራ በተራ ቡድኖቹ ቅርጻቅርጻቻቸውን እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡ ከዚያም ሌላ ስሜታቸውን የሚገልጹበትን ቃል ስጣቸው፡፡ ቡድኖቹ ይህንን በማድረግ የሚደሰቱ ከሆነ፣ እንደ ምቀኝነት፣ እርካታና አለመመቸት ወዳሉት ስውር ስሜቶች እለፍ፡፡
3. የቡድን *ዝማሬ፡፡*



ሐ. *መሪው የሚያቀርበው ትምህርት* (በራስህ አገላለጽ አቅርበው፡፡)

እስካሁን ምን ደስ እንደሚያሰኘን እየተነጋገርን ነበር፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ሁላችንም አሳዛኝ ጊዜያት ያጋጥሙናል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የሳቅም ሆነ የደስታ ስሜት አይሰማንም፡፡ አንዳንድ ጊዜ እንጨነቃለን፡፡ እስኪ ስለ ጭንቀት ምንነት፣ ከራሳችንና ከጓደኞቻችን ሕይወት ጭንቀትን እንዴት ለይተን እንደምናውቅና ስለ ጭንቀት ምን ማድረግ እንዳለብን ትንሽ እንነጋገር፡፡ ጭንቀት ለተለመዱት እንቅስቃሴዎች ስሜት እንዳይኖረን የሚያደርግ የኃዘን ድባብ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የተስፋ መቁረጥ ወይም የውድቀት ስሜት ይሰማናል፡፡ ብዙውን ጊዜ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ሰው እጅግ ይከፋዋል፡፡ የጭንቀት ስሜቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ሁላችንንም ያጠቁናል፡፡ ብዙውን ጊዜ ስሜቱ ከአጭር ጊዜ በኋላ ያልፋል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ሰዎች እየተከታተለ የሚመጣ ጭንቀት ያጋጥማቸዋል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ስሜቱ ለብዙ ጊዜ ሊቆይና ሕይወትን ለራሳችንና ለሌሎችም አስቸጋሪ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በምንጨነቅበት ጊዜ ምን ይከሰታል? ጭንቀት ምን ይመስላል? የጭንቀትን ስሜት የሚያሳድር ችግር በሚደርስብን ጊዜ ምን እንደሚከሰት ለመገንዘብ እስኪ ከሕይወታችን ውስጥ አምስቱን ክፍሎች እንመልከት፡፡

1. *ስሜታዊ፡፡* ስሜታችን ይለወጣል፡፡ ኃዘን፣ ብቸኝነት፣ ዝቅተኝነት፣ በትንሹም በትልቁም የመበሳጨት፣ የመሰላቸት ስሜት ይሰማናል፡፡ ሉምበጫችንን ጥለን ኃዘን ባጠላባቸው ዓይኖቻችን ዙሪያገባውን እናማትራለን፡፡ ነገር ግን ጭንቀት የተሰማው ሰው ሁሉ እነዚህን ምልክቶች ያሳያል ማለት አይደለም፡፡ አብዛኞቹን ሊያሳይ ይችላል፡፡
2. *አስተሳሰባዊ፡፡* በምንጨነቅ ጊዜ ባብዛኛው አሉታዊ ነገሮችን እናስባለን፡፡ ጭንቀት የሚሰማቸው ሰዎች ራሳቸውን፣ ዓለማቸውንና የወደፊት ሕይወታቸውን እንደ አሉታዊ ነገሮች ያያሉ፡፡ በማንኛውም አንድ ግለሰብ ቁጥጥር ሥር ያልሆኑት ነገሮች በሚከሰቱበት ጊዜ ራሳቸውን ወይም ሌሎችን ይወቅሳሉ፡፡ ጭንቀቱ ከላቀ ደረጃ በሚደርስበት ጊዜ የምስኪንነት ወይም የተስፋ መቁረጥ ስሜቶች ሰዎች ሞታቸውን እንዲመኙና

ምናልባትም የኋላ ኋላ ራሳቸውን ለማጥፋት እንዲነሣሡ ሊያደርጉ ይችላሉ።
3. *አካላዊ፡፡* ጭንቀት የሚሰማው ሰው ከራሱ ለመሸሸ በሚያደርገው ጥረት ከተለመደው በላይ እንቅልፍ ሊተኛ ይችላል። ወይም ደግሞ ጭራሽ እንቅልፍ በዓይኑ ላይዞር ይችላል። በተጨማሪም፣ ሥቃይ፣ ሕመም፣ የራስምታት፣ የሆድ ቁርጠትና ድካም ሊያውክው ይችላል።
4. *ባሕርያዊ፡፡* ብዙውን ጊዜ የጭንቀት ስሜት የባሕርይ ለውጥ ያስከትላል። ይህም ምናልባት የማልቀስ፣ የመገለል፣ የመበሳጨት፣ የቁጣና ተስፋ የመቁረጥ ስሜቶችን ሊጨምር ይችላል።
5. *ከሰዎች ጋር የሚኖር ግንኙነት፡፡* ጭንቀት የሚሰማቸው ሰዎች ከሌሎች ይገለላሉ። አንዳንድ ጊዜ ከእውነተኛ ስብእዊ ግንኙነቶች ለመሸሽ ሲሉ በብዙ ሰዎች መካከል ትርምስ እየፈጠሩ ሊያሳልፉ ይችላሉ።

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (*መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)*
1. ከነዚህ ምልክቶች አንዳንዶቹ አጋጥመዋችሁ ያውቃሉ?
2. እስኪ አንድናዝን የሚያደርጉንን አንዳንድ ነገሮች እንዘርዝር።
3. ስለነዚህ ነገሮች ማዘን ስሕተት ነውን?
4. ክርስቲያን መቼም ቢሆን ሊያዝን ወይም ሊጨነቅ ይገባዋልን?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጭንቀት በቀጥታ ባይናገርም፣ ፍንጭ የሚሰጡን እያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። ተማሪዎቹን በአነስተኛ ቡድኖች ከከፋፈልህ በኋላ የሚከተሉትን ጥቅሶች ለየቡድኑ አድል። ቡድኖቹ ጥቅሶቹን በማንበብ በሚቀጥለው ክፍል ውስጥ የቀረቡትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ አበረታታቸው።
1. መዝሙር 69:1-5
2. መዝሙር 88:11-8
3. ማቴዎስ 26:36-38
4. 1ኛ ነገሥት 19:1-5
5. ዘኁልቁ 11:10-15

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች (*መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)*
1. ጭንቀቱን የሚያስከትለው ምን ነበር?



2. ጭንቀቶቹን እንዴት ማስወገድ ይቻል ነበር?
3. እነዚህ ጥቅሶች እንደሚያመለክቱት፣ ለጭንቀት የሚዳርጉን ነገሮች ምንድናቸው?
4. እነዚህ ጥቅሶች እንደሚያመለክቱት፣ የጭንቀት ስሜታችንን እንዴት ልናስወግድ እንችላለን?

ሰ. መዝጊያ

ኃዘን በሚሰማችሁ ጊዜ አጥብቃችሁ ካሰባችሁበት ምክንያቱን ልታውቁ ትችላላችሁ። ችግሩ ጭንቀት በአስተሳሰባችሁ ላይ ተጽዕኖ ስለሚያስከትል ይህንን ማድረግ ሊቸግራችሁ ይችላል። ስለሆነም እንደዚህ ዓይነት ስሜት በሚያድርባችሁ ጊዜ በወቅቱ ጭንቀት ላልደረሰበት ሰው ሁኔታውን ማሳወቁ መልካም ነው። ከሰው የምታገኙት ምክር ሕይወትን ይበልጥ ፊካ ባለ ብርሃን እንድትመለከቱ ሊያግዛችሁ ይችላል።

ቤተሰብና ጓደኛስ? እንደነዚህ ስላሉት ነገሮች *(ስለሚያስጨንቋቸው ነገሮች የነገሩህን ዝርዝር አስታውሳቸው)* የመጨነቅ መብት ልንሰጣቸው ይገባል አይደል? ከላይ የተነጋገርንባቸውን ስሜታዊ፣ አስተሳሰባዊ፣ አካላዊ፣ ባሕርያዊና ከሰዎች ጋር የሚያደርጓቸውን ግንኙነቶች ተመልከቱ። ከነዚህ ነገሮች ጋር በተያያዘ አንድ ፍንጭ ካያችሁ፣ ከሚከተሉት ነገሮች አንዱን ሊያመለክታችሁ ይችላል።
1. ይህ ሰው ዝም ብሎ በኔ ላይ የማይረባ ነገር ለማድረግ እየፈለገ አይደለም። በአሁኑ ሰዓት በሕይወቱ አንድ ችግር ገጥሞታል።
2. ምናልባት ይኼ ሰውዬ አንድ የሚያነጋግረው ሰው ይፈልጋል።
3. እነዚህ ምልክቶች መቀጠላቸውን ለማወቅ ምናልባትም ይኼን ሰውዬ ብከታተለው ሳይሻል አይቀርም። ከቀጠሉ፣ ምናልባት ለአንድ ሰው (ለወላጆቹ፣ ለወጣቶች መጋቢ፣ ለመጋቢ፣ ወዘተ.) መናገር ሳያስፈልገኝ አይቀርም።
4. ምናልባት ይኼ ሰውዬ የኔን እንክብካቤ ሳይፈልግ አይቀርም። ሁላችንም ከጊዜ ወደ ጊዜ የጭንቀት ስሜቶች እንደሚያጠቁን መረዳት አለብን። ስለሆነም፣ እያንዳንዳችን መተጋገዝ አለብን። ይህ ማለት ግን ጭንቀት በሚደርስብን ጊዜ ለምናሳያቸው ባሕርዮችና ለምንናገራቸው ቃላት ኃላፊነት የለብንም ማለት አይደለም። ጭንቀት የሚሰማው ደቀመዝሙር አሁንም ቢሆን ደቀመዝሙር ስለሆነ፣ የጌታን ፈለግ መከተል አለበት። ጭንቀት እንዳያጠቃን የምንከላከልባቸው መንገዶችም አሉ።
5. በእግዚአብሔር ተማመኑ። እግዚአብሔር የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ሊሰጣችሁ እንደሚችል አስታውሱ። በሁሉም ሁኔታ ውስጥ እርሱ ኃይላችሁና ድጋፋችሁ ሊሆን ይችላል። እናንተ ሁኔታዎችን በመቆጣጠር ላይ አለመሆናችሁን በምታውቁበት ጊዜ ሳይቀር እርሱ ከዙፋኑ ላይ ነው።

6. አንዳንድ ተስፋ የመቁረጥ ሁኔታዎች እንደሚጋጥሟችሁ እወቁ:: ሕይወት አስቸጋሪ መሆኗን እናውቃለን:: እግዚአብሔር ምንም ዓይነት ችግር እንደማይገጥመን ቃል አልገባልንም:: ነገር ግን ክርስቶስ በጭንቀታችን ጊዜ አብሮን እንደሚሆን ቃል ይገባልናል::
7. አስተሳሰባችሁን መርምሩ:: ስለራሳችሁ፣ ስለ ሌሎች ወይም ስለ ሁኔታዎች አሉታዊ አሳቦችን በምትሰበስብት ጊዜ፣ ለዚሁ አሳባችሁ እውነተኛ ድጋፍ መኖር አለመኖሩን አረጋግጡ::
8. ለሌሎች ድረሱላቸው:: ጭንቀት በሚሰማችሁ ጊዜ ሌሎችን አገልግሉ:: ራሳችሁንና ምናልባትም ለማድረግ የምትፈልጉት የሚመስሏችሁን ነገሮች ማግለሉ ቀላል ቢሆንም፣ የሌሎች ድጋፍ ያስፈልጋችኋል::

በጸሎት ፈጽም::



# ደኅንነትን እንዳገኘሁ እንዴት አውቃለሁ?

ከሮናልድ ኦ. ፍራይ

ሀ. የመሪው መምሪያዎች

1. ዋና አሳብ .. ደኅንነትን እንዳገኛችሁ ልታውቁና በዚሁ እውቀት ልትኖሩ ትችላላችሁ::
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች በስሜት ሳይሆን በእምነት ደኅንነታቸውን ይኖሩ ዘንድ የሚያግዟቸውን አንዳንድ መሣሪያዎች ለመስጠት::
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ስሜቶቻቸው ሳይቀበሉ ሲቀሩ፣ ሲሰናከሉ ወይም ደግሞ ሲፈተኑ ወጣቶች መዳናቸውን ወደመጠራጠሩ ያዘነብላሉ:: ጠላት አልዳናችሁም ብሎ ሊያሳምናቸው ይፈልጋል:: ይህ ትምህርት የተዘጋጀው በዕለት ተዕለት የእምነት ጉዟቸው ወጣቶችን ለመርዳት ነው::
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. መጽሐፍ ቅዱሶች::

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል::)

1. ብታምኑም ባታምኑም:: አራት ወጣቶችን ምረጥና በሦስት ደቂቃዎች ውስጥ በሕይወታቸው ውስጥ የተፈጸመውን እጅግ የማይታመን ነገር እንዲተርኩ አድርግ:: አራቱ ተማሪዎች ንግግራቸውን ሲጨርሱ፣ የክፍሉ ተማሪዎች ከሁሉም የሚበልጠውን ታሪክ በድምጽ ብልጫ እንዲመርጡ ጠይቅ:: አስገራሚው ታሪክ በድምጽ ብልጫ ከተመረጠ በኋላ፣ ተማሪዎቹ ታሪኩን አምነው የተቀበሉት ታሪኩ የሚታመን በመሆኑ ወይስ ታሪኩን የተናገረው ልጅ የሚታመን በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ ጠይቃቸው:: (ለጉዳዩ ሌላ አቅጣጫ ለማስያዝ፣ የማይታመን ታሪክ ከሚናገሩ አራት ሰዎች አንዱ መጋቢው እንዲሆን አድርግ::)
2. ከትላልቆቹ ወንዶች ልጆች አራቱ ወይም አምስቱ ክብ 1 እንዲሆኑልህ ምረጣቸው:: ከትናንሾቹ ሴቶች ልጆች አራቱ ወይም አምስቱ ክብ 2 እንዲሆኑልህ ምረጥ:: የቀሩት ልጆች ከቡድኖቹ ለአንዱ ለመገዛት የመመረጥ ዕድል እንዳላቸው ንገራቸው:: ልጆቹ ተራ በተራ እየተነሡ ከመረጡት ክብ ውስጥ ገብተው ከቆሙ በኋላ ሰውነታቸውን ቀጥ አድርገው በጀርባቸው በመውደቅ ክቡ ሊይዛቸው እንደሚችል ማመን አለባቸው:: ጨዋታው ከተካሄደ በኋላ፣ ለምን ልጆቹ የመረጡትን ክብ እንደመረጡና በተወሰነ አቅጣጫ ለመውደቅ እንደመረጡ ጠይቃቸው::
3. የቡድን ዝማሬ::

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው።)
በዕለት ተፅለት ውይይታችን አንድ አዘወትረን የምንሰማው ሐረግ አለ። አንድ ሰው የሆነ ነገር በሚናገርበት ጊዜ ሰሚው፣ «የማይቋመን ነው» ሲል ይመልሳል።

በሳይንስ ጥናት ውስጥ ንድፈአሳቦችና ሕግጋት አሉ። የንድፈአሳብን እውነትነት ማረጋገጥ አይቻልም። ከዚህም የተነሣ፣ በንድፈአሳቦች ላይ የማያቋርጡ ክርክሮች ይካሄዳሉ። በሌላ በኩል፣ በተፈጥሮ ሕግ ላይ መከራከር አይቻልም። በመሬት ስበት ሕግ ላይ የሚነሣ ክርክር ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? በቀላሉ ሊረጋገጥ ስለሚችል በመሬት ስበት ሕግ ላይ መከራከሩ ዋጋ አይኖረውም።

በሕይወታችን እርግጠኛ የምንሆንባቸውና የማንሆንባቸው ነገሮች አሉ።

1. በሕይወት ዘመናችን ሁሉ በንድፈአሳቦች ላይ ልንከራከር እንችላለን።
2. ሐቆችን የገጠመኞችን አካል አድርገን ስንለማመድ እምነቶች ይሆናሉ።
3. ስሜቶች አንዳንድ ጊዜ እምነቶቻችንን ያወሳስባሉ (ለምሳሌ፣ እየተወደዱ ባለመወደድ ስሜት መሠቃየት ይቻላል።)

እምነት ለአእምሯዊ ሂደት ሌላ ነገር ይጨምራል። እምነት ያለ መረጃ ይቀበላል። የምንኖረው በጥርጣሬ ዘመን ውስጥ ነው። በትምህርት ቤት ሁሉንም ነገር እንድንጠይቅ እንማራለን። ከዚህም የተነሣ፣ ብዙ ጥያቄዎችን እናነሣለን። ይህ መልካም ቢሆንም፣ ሽባ የሚያደርጉንን ብዙ ጥርጣሬዎች ይፈጥራል። ይህንን የታላቅ ጥርጣሬ አእምሯዊ ሂደት በክርስቶስ ወዳለው እምነታችን ካመጣን፣ ከፍተኛ ግጭት ይፈጠራል። በክርስቶስ የምንመላለስበት ሕይወት በእምነት የምንኖረው ነው። ስለ እግዚአብሔር ያለን እውቀት በእምነት ይጠቃለላል። ለእግዚአብሔርና ለቃሉ የምንታዘዘው በእምነት ነው። በእምነት መራመዳችን ከእግዚአብሔር ጋር እውነተኛ ግንኙነት እንድናደርግ በማስቻል፣ ስለ እርሱ ያለንን እውቀት እውነተኛነት ያረጋግጣል። ይህ ግን ያለ እምነት ተግባራዊ ሊሆን አይችልም። እምነት ከሌለን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት አጠራጣሪ ንድፈአሳብ ይሆንብናል። ስለሆነም፣ ስለ እግዚአብሔር የምናውቀውና ከርሱ ጋር ያለን ግንኙነት አሁንም ከእምነት የሚመነጭ ነው።

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙ ባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)



1. ራስህን የምትገልጸው የእምነት ሰው አድርገህ ነው ወይስ የጥርጣሬ? ለምን?
2. በይበልጥ የምታምነው ስሜቶችህን ነው ወይስ አእምሮህን?
3. ስሜቶችህ በሚዋሹህ ጊዜ፣ ምን ታደርጋለህ?
4. ከጥርጣሬ ወደ እምነት የምትሄደው እንዴት ነው?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)

1. ዕብራውያን 11:1: እምነት በክርስቶስ ያገኘነውን ስፍራ ይሰጠናል። ለኃጢአቶቼ ይቅርታን የማገኘው እንዴት ነው? በክርስቶስና በቃሉ በማመን። ክርስቶስ በኔ ውስጥ እንዲኖር የምጋብዘው እንዴት ነው? በክርስቶስና በቃሉ በማመን። ክርስቶስ አሁን በኔ ውስጥ እንዳለ እንዴት አውቃለሁ። በክርስቶስና በቃሉ በማመን። እምነት ዓይኖቻችን ለማየት ስለማይችሉት ነገር እርግጠኞች ያደርገናል። ምናልባትም፣ «እንዲህ ዓይነት ነገር አይገባኝም!» ልትል ትችላለህ።
2. ዕብራውያን 11:1: እምነት መረዳት ማለት ነው። እግዚአብሔርን፣ ለደኅንነታችን የወጠነውን ዕቅድ፣ ለኛ ያለውን ፍቅር፣ ፈቃድ፣ በኛ ውስጥ ያለውን መንገድ አእምሯችንን ብቻ ተጠቅመን ለመረዳት ብንሞክር፣ ብዙ ርቀን ልንሄድ አንችልም። በክርስቶስ የሚገኘውን ልምምድ ሁሉ አረጋግጠን ልንጨርስ አንችልም። ነገር ግን እግዚአብሔር በውስጣችን በአሁኑ ሰዓት አንድ ነገር እያደረገ መሆኑን በእምነት ልንረዳ እንችላለን። ለሌላ ሰው ለማብራራት በማንችልበት ጊዜ እንኳዋን በእምነት እናውቃለን።
3. ዕብራውያን 11:13: እግዚአብሔርን በሥራችን ልናስደስተው አንችልም። አንዳንድ ጊዜ ከደካማ ሥራችን የተነሣ መዳናችንን እንጠራጠራለን። የራሳችንን ተግባር በመፈጸም ወይም የእግዚአብሔርን ተግባር በራሳችን መንገድ በመፈጸም እግዚአብሔርን ደስ ልናሰኘው አንችልም። እግዚአብሔርን የምናስደስትበት ብቸኛው መንገድ እምነት ነው። ይህ የሚሆነው እንዴት ነው?

   ሀ. ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት፣ የእግዚአብሔርን ህልውት (ህልውናውን) ማመን አለብህ። ይህ ህልውናውን ብቻ ሳይሆን፣ የሚያስፈልጉንን ነገሮች ሁሉ ለማሟላት እንደሚችል ማመንን ይጠይቃል። ከእግዚአብሔር ምንም ነገር ፈልገን ብንመጣ፣ ይህንኑ የማድረግ ብቃት እንዳለው ማመን አለብን።

   ለ. ወደ እግዚአብሔር ለመምጣት፣ በትጋት ለሚሹት እርሱ ሽልማትን እንደሚሰጥ ማመን አለብን። እግዚአብሔርን

በትጋት መሻት ማለት አልፎ አልፎ ከመጸለይ፣ አልፎ አልፎ መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበብና አልፎ አልፎ ወደ ቤተክርስቲያን ከመሄድ ያለፈ ግንኙነት ነው:: የእግዚአብሔርን ሁለንተና በሁለንተናችን መሻት አለብን:: ኤርምያስ 29:13 እንደሚለው፣ *«እናንተም ትሹኛላችሁ:: በፍጹም ልባችሁ ካሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ::»* ማቴዎስ 6:33፣ *«አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ:: ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል»* ይላል::
ከራሳችን አስቀድመን በእምነት የእግዚአብሔርን መንገድ መፈለግ አለብን:: በእምነት ስንፈልገው፣ እውነተኛ በሆነ ግንኙነት በእምነት እናገኘዋለን:: በዚህም ጊዜ ክርስቶስን በግል ደረጃ እናውቀዋለን:: ይህም እርሱ ኃጢአታችንን ይቅር እንዳለና ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በውስጣችን እንደሚኖር ያረጋግጥልናል:: በዚሁ ተመሳሳይ እምነት የዘላለም ሕይወት እንዳለን ልናውቅ እንችላለን:: ዮሐንስ እንዳለው፣ «የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ» (1ኛ ዮሐንስ 5:13):: እንዲህ ዓይነቱን እምነት ከወዴት እናገኛለን?

4. ሮሜ 10:17: በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ የሚጣል እምነት መዳን አስመዳኔን የማውቅበት መንገድ ከሆነ፣ ይህንን እምነት ከየት ማግኘት እንደሚቻል ማወቁ ወሳኝ ነው:: እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ እናውቃለን:: *«ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና:: ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም»* (ኤፌሶን 2:8):: በተጨማሪም፣ የእምነታችን መሠረቱ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ከሮሜ 10:17 እንረዳለን:: ደኅንነታችንን በተጠራጣሪ ዓይኖቻችን ወይም በስሜቶቻችን ለመዳኘት በምንፈተንበት ጊዜ፣ ወደ እግዚአብሔር ቃል እውነት መመለስ አለብን:: በቃሉ ውስጥ በተገለጸው የእግዚአብሔር ማዳን መልካም የምሥራች አምነን ከዳንን ዘንዳ፣ ባለማቋረጥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተመሥርተን ልንኖር ይገባል:: መዝሙር 119:105-112 አንብብ::

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች

1. እምነት ስሜትህ የማይነግርህን ምን እውነት ይነግርሃል?
2. እምነት ከየት ይመጣል?
3. እምነት የሚኖርህ ነገር ነው ወይስ የምታደርገው?
4. መዳንህን ለመጠራጠር በምትፈተንበት ጊዜ ምን ማድረግ ይኖርብሃል?
5. የእግዚአብሔርን ቃል ሳልከተል እምነትን ሳገኝ እችላለሁን? መ[illegible]ስህን አብራራ::



6. እንደዳንህ ታውቃለህ? እንዴት?

ሰ. መዝጊያ

በእምነት መዳናችሁን ልታውቁና እንድትጠራጠሩ የሚገፋፏችሁን ስሜቶቻችሁን አሁኑኑ ልታርቁ ትፈልጋላችሁ? እግዚአብሔር በቃሉ አማካኝነት ሊመራችሁ ይፈልጋል:: እርሱ ጥርጣሬዎቻችሁንና ስሜቶቻችሁን ይረዳል:: የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም በስሜቶቻችሁና በእምነት መጓዛችሁ መካከል ያለውን ልዩነት ተረዱ:: ስለ ስሜቶቻችሁ የምትነግሩትንና በእምነት እንድትራመዱ የሚያበረታታችሁን አንድ ሰው ምረጡ:: ስሜቶቻችሁ ጦር በሚሰብቁባችሁ ጊዜ ሳይቀር በማዳን መንገዱ ትረማመዱ ዘንድ እግዚአብሔር እንዲመራችሁና የእምነትን ዓይኖች እንዲሰጣችሁ ጸልዩ::

## የተሳሳቱ ግንዛቤዎች
ከአለን ስኮት

ሀ. *የመሪው መምሪያዎች*

1. ዋና አሳብ .. በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተገለጠው እግዚአብሔር ጓደኞችን ሊሆንና ይህንኑ ጓደኝነት ሊያሳድግ ይፈልጋል።
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ብዙውን ጊዜ ወጣቶች ስለ እግዚአብሔር የሚያስቧቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ አመለካከቶች ለመመርመርና ለማረም።
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. ስለ እግዚአብሔር ያሉን አመለካከቶች በሕይወታችን ውስጥ ከሚከሰቱ ብዙ ነገሮች የተቀረጹ ናቸው። እነዚህም ነገሮች መንፈሳዊ እያታችን ከምትናገራቸው ቃላት እስከ ምርጥ ዝማሬ የሚደርሱ ናቸው። እያንዳንዱ ክርስቲያን ስለ እግዚአብሔር የያዘው አመለካከት መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው እውነት ጋር እንዲጣጣም ማድረግ አለበት።
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. ትናንሽ ኳሶች፣ የተለያየ መጠን ያላቸው ባልዲዎች፣ ትራሶች፣ ከላ፣ መቀሶች፣ ስካርፎች።

ለ. *የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል።)*

1. ኳሶችን ባልዲዎች ውስጥ ማንጠር። ከ5-6 የሚሆኑ የተለያየ መጠን ያላቸው ባልዲዎችን አሰልፍ። ከአስቸጋሪነት አንጻር ለእያንዳንዱ ነጥብ ስጥ። እያንዳንዱ ተማሪ ከባልዲዎቹ ከ2-3 ሜትር ርቆ እንዲቆም አድርግና ትንሽ ኳስ ስጠው። የጨዋታው ዓላማ ኳሱ ከባልዲዎቹ አንዱ ውስጥ ገብቶ እንዲነጥር ማድረግ ነው። ተማሪው ነጥብ የሚያገኘው ኳሱ ባልዲው ውስጥ ገብቶ ቢያንስ አንድ ጊዜ ከነጠረና እዚያው ከቀረ ብቻ ይሆናል። ኳሶቹ ተለይተው እንዲታወቁና ብዙ ልጆች በአንድ ጊዜ እንዲጫወቱ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ኳሶቹን የተለያየ ቀለም ቀባቸው። ሁሉም ትልቅ ነጥብ በሚያስገኘው ባልዳ ውስጥ ኳሱን ለማንጠር በሚጥርበት ጊዜ፣ ኳሶቻቸው እርስበርስ ይማታሉ።
2. እግዚአብሔርን መሣል። እያንዳንዱ ተማሪ እግዚአብሔር ለሱ ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ሥዕል እንዲሠራ ጠይቅ። ለተማሪዎቹ ከላ፣ መቀሶች፣ ወዘተ. በማደል ጥሩ የፈጠራ ተግባር እንዲያከናውኑ አድርግ። ሠርተው ከጨረሱ በኋላ፣ እያንዳንዳቸው ስለሠሩት ሥዕል ማብራሪያ እንዲሰጡ ጠይቅ።
3. የቡድን ዝማሬ።



ሐ. *መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው።)*

ሁላችንም ልብ ሳንል ስለ እግዚአብሔር ያለንን አመለካከት እንቀርጻለን። ከዚያ በኋላም ይህንኑ በአእምሯችን ውስጥ የፈጠርነውን ሥዕል በመጠቀም ለእግዚአብሔር ምላሽ እንሰጣለን። ኬይት ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ምን ዓይነት አመለካከት እንዳላቸው እንድትጠይቅ ተመድባ ነበር። «እግዚአብሔር ምን ዓይነት ይመስላችኋል?»

«አ፣ እኔ እንጃ... እህ... እረኛ ይመስለኛል።»

«እንዴት?»

«እረኛ። ታውቂያለሽ፣ እርሱ ሁልጊዜም ሰዎችን ሲገፋ፣ ሲገፋፋና ሲያስር ይኖራል። እኔ ሳልፈልግ ሁልጊዜም በኔ ላይ የባለቤትነት ምልክት ለማስቀመጥ እንደሚሞክር አድርጌ ነው በአእምሮዬ ውስጥ የምስለው።»

«አንዴ እመቤት፣ ስለ እግዚአብሔር ያለዎት ግንዛቤ ምንድነው?»

«አ፣ እግዚአብሔር ትልቅና ቸር አባት ነው። እርሱ ሁሉንም ነገር ስለሚያደርግ፣ እኔ ምንም ማድረግ አያስፈልገኝም። ከመጠን በላይ ስለሚወደኝ ትክክለኛ ማንነቴን ላለማየት ዓይኖቹን ይጨፍናል።»

«ይቅርታ አድርግልኝና የቅርጫት ኳስ ልምምድህን ለማቋረጥ አልፈልግም። ግን እግዚአብሔር በአንተ አመለካከት ምን ዓይነት ነው?»

«እሺ። እግዚአብሔር በሰማይ ውስጥ እንደሚገኝ ታላቅ የቅርጫት ኳስ ዳኛን ይመስላል።»

«ማለት?»

«ማለት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉ ሕጎች አሉ አይደል? እነዚህን ሕጎች በጣስሽ ጊዜ መቅጣቱ የእግዚአብሔር ድርሻ ነው። ታውቂያለሽ፣ ከጨዋታው ሊያስወጣሽ ሁሉ ይችላል!»

«ስለ እግዚአብሔር ለማደርገው ቅኝት ሊተባበሩኝ ይችላሉ? እግዚአብሔርን እንዴት ይገልጹታል?»

«ድሮ እግዚአብሔር ጠንካራ ይመስለኝ ነበር። አሁን አሁን ሳስበው እንደ የጀርባ አጥንት የሌለው ደካማ ነገር ይመስለኛል።»

«ለምን እንደዚያ አሰቡ?»

«ዓለም ያለችበትን ሁኔታ ተመልከቺ። ለምን አያስተካክላትም? ሰዎች ወደ ጎን እንዲገፉት ፈቅዶላቸዋል። ራሱን ለመከላከል አልፈለገም።»

«ስለ እግዚአብሔር ያለዎት ግንዛቤ ምንድነው?»

«አ፣ ዋዎ... እርግጠኛ አይደለሁም። አባራ የወረሰው ይመስለኛል።»

«አባራማ? ምን ማለትዎ ነው?»

«እግዚአብሔር ጥንት ለሰዎች ጠቃሚ አገልግሎት ሰጥቷል። እናም ልናከብር ይገባል። እኔ ግን እዚያው ከዕቃ መደርደሪያ ላይ ነው የማኖረው። በበዓል ቀናትና ልዩ ጊዜያት ከዚያ ላይ እንሥቼ አቧራውን እጠርግለታለሁ።»

መ. የመወያያ ጥያቄዎች (መጀመሪያ የተወሰኑ አባላት በሚገኙባቸው አነስተኛ ቡድኖች ተከፋፍለው፣ ከዚያም በአንድ ላይ እንዲወያዩ አድርግ።)

1. ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ብዙ የተለያዩ ግንዛቤዎችን የሚይዙት ለምን ይመስልሃል?
2. እነዚህ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ያላቸውን ግንዛቤ እንዴት ያገኙ ይመስልሃል?
3. ከነዚህ ግንዛቤዎች መካከል ጓደኞችህ ስለ እግዚአብሔር ያላቸውን አመለካከቶች የሚመስሉት የትኞቹ ናቸው?
4. እነዚህ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የያዙት ግንዛቤ ከእግዚአብሔር ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ የሚያሳድር ይመስልሃል? እረኛ አምላክ? ትልቅ አባት? ዳኛ አምላክ? ደካማ አምላክ? አቧራማ አምላክ?

ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው።)

1. ዮሐንስ 14:9: *«እኔን ያየ አብን አይቷል»* እግዚአብሔር ነቢያት ስለርሱ እንዲናገሩ ከመላክ የበለጠ ተግባር አከናውኗል። እግዚአብሔር የራሱን ማንነት ያሳየን ዘንድ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን ልኮልናል። እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ለማወቅ በምንፈልግበት ጊዜ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት መመልከቱ በቂ ነው። በወንጌላት ሁሉ የእግዚአብሔርን ሙሉ ምስል እንድናውቅ የሚያስችሉ የክርስቶስ ባሕርያት ተገልጸዋል። ከዮሐንስ ወንጌል የተመረጡ ጥቂት ነጥቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

   የእግዚአብሔር ልጅ 1:1-14
   አጽናኝ 14:1-3
   የኃጢአተኞች ወዳጅ 4:7-29
   መንፈስ ቅዱስን የሚሰጥ 16:1-5
   የሕይወት ውኃ 7:37-38
   ሞትን ድል የሚነሣ 20:1-31
   ሕይወት ሰጪ 11:1-44
   ባሪያ 13:1-10
   መለኮታዊ መምህር 3:1-21
   ወዳጅ 15:9-17
   የሕይወት እንጀራ 6:25-58



   ሥቃይን የመቀበል ምሳሌ 18:1-11
   መልካም እረኛ 10:1-16
   ንስሐ የሚገቡትን የሚቀበል 21:1-19
   የሰው ልጅ 2:1-10
   እውነተኛ ወይን 15:1-8
   ታላቅ ሐኪም 5:1-9
   አማላጅ 17:1-26
   የዓለም ብርሃን 8:12
   ንጉሥ 12:12-15

   እግዚአብሔርን በማንነቱ ለመረዳት እነዚህ ሁሉ ባሕርያት በአንድነት መታየት አለባቸው። ብዙውን ጊዜ ስለ እግዚአብሔር የተሳሳተ ግንዛቤ የምንይዘው ከባሕርያቱ አንዱን ብቻ (ማለትም እረኛ፣ ወዘተ.) ነጥለን በመመልከት ነው።

2. ሮሜ 1:20-23: ይህ ጥቅስ እውነተኛው የእግዚአብሔር ባሕርይ ለሰዎች ሁሉ ግልጽ እንደሆነ ይናገራል። እግዚአብሔር ከእይታችን የተሰወረ ከሆነ መደነቅ የለብንም። እግዚአብሔርን ለማወቅ የምንቸገረው ራሳችንን ለራሱ አሳልፈን ባለመስጠታችን ምክንያት ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ፣ ከራሳችን አስተሳሰብ ጋር በሚጣጣም መልኩ የራሳችንን አምላክ ወደመፍጠሩ እናዘነብላለን። ስለሆነም፣ በራሳችን አስተሳሰብ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ እገዛ ስለ እግዚአብሔር ያለንን ግንዛቤ እንደገና መቅረጽ አለብን።

ሦስት የመጽሐፍ ቅዱስ ዐበይት ነጥቦች ከዚህ በታች ተሰጥተዋል።

1. እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ራሱን ገልጧል።
2. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ሙሉ ምስል ለመስጠት ሲል የኢየሱስ ክርስቶስን ባሕርያት በርከት አድርጎ ሰጥቶናል።
3. ችግሩ እግዚአብሔር ሁልጊዜም ለኛ የማይታወቅ መሆኑ ሳይሆን፣ እኛ እግዚአብሔርን በአምሳላችን ለመቅረጽ መሻታችን ነው።

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች

1. እነዚህ ጥቅሶች እንደሚሉት፣ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል እንዴት ልናውቅ እንችላለን?
2. ብዙ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሕርያት የተገለጹት ለምንድነው?
3. ለእግዚአብሔር ያለን አመለካከት ስለርሱ ባለን ግንዛቤ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድረው እንዴት ነው?
4. በኬይት ቃለምልልስ ላይ ሰዎች እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል አስመልክተው የገለጹዋቸውን አሳቦች

1. ተመልከቱ፡፡ ከነዚህ ከእያንዳንዳቸው ምስሎች ስሕተት የሆነው ወይም የጎደለው ምንድነው?
    - እረኛ አምላክ (እግዚአብሔር ሰዎች እርሱን እንዲመርጡት ወይም እንዲተውት ነጻነት የሚሰጥም አምላክ ነው፡፡)
    - ትልቅ አባት (እግዚአብሔር ሰዎች ለሚመርጧቸው ነገሮች ኃላፊነት እንዳለባቸውም ይናገራል፡፡)
    - ዳኛ (እግዚአብሔር የጸጋም አምላክ ነው፡፡)
    - ደካማ (እግዚአብሔር መሐሪ አምላክ በመሆኑ እኛ እንደምናስበው ፈጥኖ አይፈርድም፡፡)
    - አቧራማ (እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ ለመሥራት ይፈልጋል፡፡)

ሰ. *መዝጊያ*

ስለርሱ የነበረንን ግንዛቤ ለእግዚአብሔር በግልጽ መናገር አለብን፡፡ እግዚአብሔርን በትክክል ለማወቅ ከፈለግን፣ ምንም ለውጥ ሳናደርግበት እግዚአብሔርን በማንነቱ ለመቀበል መፍቀድ አለብን፡፡ የሚከተሉትን ነገሮች አስታውሱ፡፡

1. እግዚአብሔር የበለጠ እርሱን ለማወቅ እንድንሻ ይፈልጋል፡፡
2. ስለ ክርስቶስ በምናነብበት ጊዜ፣ እግዚአብሔርን የበለጠ እያወቅነው እንሄዳለን፡፡
3. እነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ባሕርያት የእግዚአብሔርን ፍቅር ስፋትና ጥልቀት ያሳያሉ፡፡ ለዚህም ምክንያቱ እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ ነው፡፡

*(እግዚአብሔር ራሱን ስለገለጠላችሁ በማመስገን በጸሎት ፈጽሙ፡፡)*



# በአግባቡ አይሆንም ማለትን ማወቅ

ከኤድ ሮቢንሰን

ሀ. *የመሪው መምሪያዎች*

1. ዋና አሳብ .. አንድን ጉዳይ የማንደግፍ ወይም የማንስማማበት ከሆነ፣ ገንቢ የሆነ ምላሽ ልንሰጥ እንችላለን፡፡
2. የትምህርቱ ዓላማ .. ወጣቶች ከጸብ ይልቅ ለዕርቅ አስተዋጽኦ ለማድረግ እንዲችሉ ገንቢ መርሆችን በተከተለ መንገድ አንድ ነገር አለመደገፋቸውን እንዲገልጹ ለማገዝ፡፡
3. የትምህርቱ አጠቃላይ አሳብ .. በብዙ መንገዶች ወጣቶች የሚኖሩት አለመስማማት በበዛበት ዘመን ውስጥ ነው፡፡ ዕፆችን እንዳይጠቀሙ፣ የግል መብቶቻቸውን እንዲያስከብሩና ለአዋቂዎች የራሳቸውን አሳቦች እንዲገልጹ ይበረታታሉ፡፡ እነዚህ ነገሮች መጥፎዎች ባይሆኑም፣ ጥንቃቄ ካልተደረገ ያለመስማማት መንፈስ ወደ ወጣቶች ሕይወት ዘልቆ በመግባት ተከራካሪዎች፣ አክብሮት የሌላቸውና አንድን ነገር አለመቀበላቸውን በሚገልጹበት ጊዜ ክርር ብለው እንዲታዩ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይህ ክፍል ወጣቶች ከወላጆቻቸው፣ ከጓደኞቻቸውና ከሌሎችም አዋቂዎች ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ በአግባቡ ተቃውሟቸውን የሚገልጹባቸውን መርሆች ያቀርባል፡፡ ይህም ለግንኙነቶችና ለማኅበረሰቦች አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያስችላቸዋል፡፡
4. የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች .. ለእያንዳንዱ ተማሪ እርሳስና ወረቀት፡፡

ለ. የመክፈቻ እንቅስቃሴዎች (ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ከመጽሐፉ የመጨረሻ ገጾች ላይ ተዘርዝረዋል፡፡)

1. የዚፕ-ዛፕ ጨዋታ፡፡ ይህ ስም የመጥራት ጨዋታ የተዘጋጀው የቡድኑ አባላት የጓደኞቻቸውን የመጀመሪያ ስሞች መጥራት እንዲለምዱ ለማበረታታት ነው፡፡ የቡድኑ አባላት በክብ ዙሪያ ተቀምጠው ሳሉ መሪው ወደ አንድ ልጅ በማመልከት፣ «ዚፕ፣ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት» ወይም «ዛፕ፣ አንድ፣ ሁለት...» ይላል፡፡ ልጁ ከአንድ እስከ አምስት ሳይቆጠርበት «ዚፕ» ለሚለው ከበስተቀኙ ያለውን ልጅ የመጀመሪያ ስም፣ «ዛፕ» ለሚለው ከበስተግራው ያለውን ልጅ የመጀመሪያ ስም በፍጥነት መናገር አለበት፡፡ እስከ አምስት ከተቆጠረበት ግን ወደ ክቡ መሀል ይገባል፡፡ የአብዛኞቹ ልጆች ስሞች እስኪጠሩ ድረስ ጨዋታውን ቀጥል፡፡ በጨዋታው ጊዜ ለለውጥ ያህል ልጆቹ በታ ተለዋውጠው እንዲቀመጡ ልታደርግ ትችላለህ፡፡

2. ከ... በስተቀር ሁላችሁንም እወዳለሁ:: ይህ ከመጽሐፉ መጨረሻ በቁጥር 30 ከተሰጠው ጨዋታ ጋር የሚመሳሰል ነው:: የቡድኑ አባላት በክብ ዙሪያ ተቀምጠው ሳለ (ትርፍ ወንበር አይኖርም) መሪው፣«ከ... በቀር ሁላችሁንም እወዳችኋለሁ» ይላል:: ይህን ሲል ቢያንስ ከክፍሉ ተማሪዎች ሁለት ሰዎችን የሚያመለክት ባሕርይ መጥቀስ አለበት:: (ለምሳሌ፣ ካልሲ ከማያደርጉት ልጆች በቀር፣ ሰማያዊ ልብስ ከሚለብሱ ልጆች በቀር፣ ወዘተ.):: ገለጻው የሚመለከታቸው ልጆች ከመቀመጫቸው ተነሥተው ወደ ባዶ ወንበሮች ይዛወራሉ:: ከክቡ መሀል ያለውም ልጅ የሚቀመጥበትን ባዶ ወንበር ለማግኘት ይጥራል:: ወንበር ያላገኘው ልጅ፣ «ከ... በስተቀር ሁላችሁንም እወዳለሁ» በማለት ጨዋታውን ይቀጥላል:: አጫዋቹ፣ «ሁላችሁንም እወዳችኋለሁ!» በማለት ልጆቹ ወንበር እንዲቀይሩ ማድረግ ይችላል::
3. ይህ ጨዋታ በአሳቦች፣ አነጋጋሪ ጉዳዮች፣ ወይም ወጣቶች የተቃውሞ ድምጻቸውን እንዲያሰሙ በሚያደርጉ ሁኔታዎች ላይ ለማተኮር የሚያስችል መወያያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል:: ይህም ጠንካራ ውይይት ሳይሆን፣ መሪው በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ወቅት የሚጠቀምበትን የተወሰነ ፍንጭ የሚያስገኝ ነው:: ለእያንዳንዱ ተማሪ እርሳስና ወረቀት አድል:: የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማቅረብ አጫጭር መልሶችን (ከ10 ቃላት የማይበልጡ) እንዲሰጡ አድርግ::

   ሀ. በትምህርት ቤት ውስጥ ከሚያበሳጩኝ ነገሮች አንዱ...

   ለ. በቤት ውስጥ ከሚያሳጩኝ ነገሮች አንዱ...

   ሐ. ስለ አካባቢያችን/መንደራችን/ከተማችን በማስብበት ጊዜ ከሚረብሹኝ ነገሮች አንዱ...

   መ. ስለ ዓለም ሁኔታ በማስብበት ጊዜ ከሚብሹኝ ነገሮች አንዱ...

   ተማሪዎቹ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ፈጣን ምላሽ እንዲሰጡ ገፋፋቸው:: ጥያቄዎቹን ሠርተው ሲጨርሱ ስማቸውን እንዳይጽፉበት ንገራቸውና ወረቀቱን ሰብስብ:: ከዚያም ከመልሶቹ አንዳንዶቹን ለተማሪዎቹ አንብብላቸው:: በተማሪዎቹ መልሶች ውስጥ ከተገለጹት አሳቦች አንዳንዶቹን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ልትዘረዝር ትችላለህ:: በዚህ ላይ የራስህን አሳብ በማከልና ገንቢ በሆነ መንገድ ተቃውሞን ስለመግለጽ የሚያስረዳውን ትምህርት (ከዚህ በታች የቀረበውን) በማስተዋወቅ የጨዋታውን ጊዜ ፈጽም::
4. የቡድን ሥራ:: ተማሪዎቹን ከሦስት እስከ አምስት አባላት እንዲኖራቸው አድርገህ ከፋፍል:: ለእያንዳንዱ ቡድን የሚከተለውን ሥራ ስጣቸው:: «ማኅበረሰባቸውን ከሚያውኩት ወሳኝ ችግሮች አንዱን ለማስተካከል የሚውል 40,000 ብር



ተሰጥቷችኋል እንበል:: አሁን አንድ ጠቃሚ ፕሮጀክት መምረጥና ገንዘቡን እንዴት ከሥራ ላይ እንደምታውሉት መወሰን አለባችሁ:: ሥራችሁ የሚመራው በሁለት ደንቦች ነው:: ሀ. ያለምንም ተቃውሞ ሁላችሁም ተስማምታችሁ በአንድ ድምጽ መወሰን አለባችሁ:: ለ. ከቡድናችሁ አባላት ማንኛውም አንድ ሰው የፈለገሽውን አሳብ የመስጠት መብት አለው:: በአምስት ደቂቃዎች ውስጥ ውሳኔዎቻችሁንና ከዚህ ውሳኔ የደረሳችሁበትን መንገድ ትነግሩናላችሁ!»

   የሰጠሃቸው ጊዜ ሲያልቅ፣ ቡድኖቹ ከውሳኔ የደረሱባቸውን መንገዶች እንዲያብራሩ አድርግ:: በቡድኖቹ ውስጥ የሚካሄደውን የትኛውንም ዓይነት አለመስማማት በማጤን በኋላ በጥናቱ ውስጥ ልትጠቀም ትችላለህ::
5. የቡድን ዝማሬ:: •

ሐ. መሪው የሚያቀርበው ትምህርት (በራስህ አገላለጽ አቅርበው::)

በሕይወታችን ውስጥ ከሌሎች ሰዎች ጋር የማንስማማባቸው ጊዜያት አሉ:: አንዳንድ ጊዜ እንዲህ ዓይነት አለመስማማቶች የሚከሰቱት ለመመገብ የምንፈልገውን ምግብ ወይም በቤተክርስቲያን ውስጥ የምንቀመጥበትን ስፍራ በሚመለከቱ ቀላል ጉዳዮች ሳቢያ ይሆናል:: በሌሎች ጊዜያት ደግሞ አለመስማማቱ በጣም ጠቃሚ የሆኑትን ነገሮች የሚመለከት ሊሆን ይችላል:: እነዚህም ወላጆች ልጆቻቸውን የሚቀጡበት ፍትሐዊ ቅጣት ምን እንደሆነ፣ ጓደኞችህ አብረሃቸው ዕፅ እንድትወስድ በሚጠይቁህ ጊዜ ጥያቄያቸውን አለመቀበል፣ በማኅበረሰባችን ወይም በዓለም ውስጥ የሚካሄደውን ፍትሕ-አልበኝነት መቃወም የመሳሰሉት ናቸው::

አለመስማማቶች በክርስቲያኖች መካከል ጭምር የሚከሰቱ ነገሮች ናቸው:: ዮሐንስ ማርቆስን ለአገልግሎት በሚጓዘው ቡድን ውስጥ ማካተትን አስመልክቶ ጳውሎስና በርናባስ ከፍተኛ አለመስማማት ላይ ደርሰው ነበር(የሐዋርያት ሥራ 15:36-41):: ይህም ሚሲዮናውያን የሥራ ጓደኞች እንዲለያዩ አድርጓል:: በርናባስ ዮሐንስ ማርቆስን ሲመርጥ፣ ጳውሎስ ደግሞ ሲላስን ይዞ ወደ አዲስ የአገልግሎት ጉዞው አምርቷል::

ዋናው ነገር አለመስማማቶችን ብዙውን ጊዜ ማስወገድ እንደማይቻልና አለመስማማቶቹ በራሳቸው ችግር አለመሆናቸውን መገንዘብ ነው:: አለመግባባቱን የምናስተናግድበት መንገድ ግን አንዳንድ አደገኛ መዘዞችን ሊያስከትል ይችላል:: አለመስማማትን የመረጥነው የራስወዳድነትና የብቀላ አሳብ ሳይኖረን ትክክለኛ ነገሮች እንዲከናወኑ ከመቆርቆር የሆነ እንደሆነ፣ ብዙውን ጊዜ ለችግሩ ጤናማ መፍትሔ ልናመጣ እንችላለን:: ነገር ግን ሳለመስማማት የፈለግነው ከጥላቻ፣ ከመራርነትና ከራስወዳድነት አመለካከት

በመነሣት ከሆነ፣ ባመዛኙ ችግሩን የበለጠ እናወሳስባለን:: ይህ አለመስማማትን ወይም ተቃውሞን በገንቢ መንገድ የመግለጽ መርህ በትንሽ ጉዳይ ላይ ለሚከራከሩ ጓደኛሞችም ሆነ ዓለምአቀፍ ችግሮችን ለመፍታት ለሚጥሩ የዓለም መሪዎች ሊያገለግል ይችላል::

እስኪ ብዋናሊን እንመልከት:: ብዋናሊ የትምህርት ቤቱ የቅርጫት ኳስ ቡድን ኮከብ ተጫዋች ነው:: ባለፈው ሳምንት ከሩቅ ቦታ የመጣ እንግዳ በቤታቸው ውስጥ ቆይቶ ነበር:: ከእንግዳው ጋር በተያያዘ ወላጆቹ የወጠኑት ዕቅድ ሥራ ስላበዛበት፣ ብዋናሊ ትምህርቱን ብዙም ሊያጠና አልቻለም ነበር:: ከዚህም የተነሣ፣ ፈተና በመውደቁ ትምህርት ቤታቸው ከዋንኛ ተፎካካሪው ጋር በሚያደርገው ግጥሚያ ላይ እንዳይጫወት ተከለከለ::

ብዋናሊ ለዚህ ሁኔታ በተለያዩ መንገዶች ምላሽ ሊሰጥ ይችላል::

1. በውድድሩ ላይ እንዳይጫወት መወሰኑ ወላጆቹ፣ አስተማሪዎቹና የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪዎች የፈጸሙበት ፍትሐዊነት የጎደለው ተግባር እንደሆነ ለጓደኞቹ አማሮ እየተናገረ፣ የተሰጠውን ቅጣት ሊቀበል ይችላል::
2. ችግሩ በሱ ጥፋት እንዳልተፈጸመና ነገሩ ሁሉ ፍትሐዊ እንዳልሆነ በመግለጽ ፈተናውን በሰጠው አስተማሪ ላይ ተቃውሞውን ሊገልጽ ይችላል::
3. አሠልጣኙ ችግሩን እንደሚቀርፉለት ተስፋ በማድረግ፣ ቤተሰቦቹ በዚያን ሳምንት በቤተሰባዊ ጉዳዮች ውስጥ እንዲሳተፍ ማድረጋቸውና መምህሩም ለማጥናት ጊዜ አለማግኘቱን እያወቀ የማለፊያ ውጤት አለመስጠቱ ተገቢ እንዳልሆነ በመግለጽ ለአሠልጣኙ አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል::
4. ችግሩ የወላጆቹ ጥፋት እንደሆነና መጭው የትምህርት ቤቱ የቅርጫት ኳስ ወቅት በዋናነት በነሱ ላይ እንደወደቀ በመግለጽ፣ ወላጆቹን ሊያጋፍጥ ይችላል::
5. ወይም...

መ. የመወያያ ጥያቄዎች

1. የ1ኛ፣ የ2ኛ፣ የ3ኛና የ4ኛ ምላሾች ውጤት ምን የሚሆን ይመስልሃል?
2. በብዋናሊ ቦታ ብትሆን ምን ምላሽ ትሰጥ ነበር?
3. በአንተ አስተሳሰብ፣ ብዋናሊ ሁኔታውን ለማስተካከል ምን ሊያደርግ ይችላል?
4. ብዋናሊ ሊያደርግ ይችላል የምትለው ገንቢ እርምጃ ካለ፣ በችግሩ ውስጥ የተሳተፉትን ሰዎች እንዴት ሊያነጋግራቸው ይገባል?



ሠ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግኝቶች (የሚከተሉትን ምንባቦች አንብባችሁ ተወያዩባቸው::)

እስኪ በገንቢ መንገድ ተቃውሟችንን እንድንገልጽ የሚያግዙንን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እንመልከት::

1. 2ኛ ጢሞቴዎስ 2:23-24: ጉዳዩ ለክርክር የሚበቃ መሆኑን አረጋግጡ:: አንዳንድ ጊዜ የምንከራከርባቸው ነገሮች በጣም አነስተኛ ግምት የሚሰጣቸው በመሆናቸው (ጳውሎስ ይህንን ሞኝነት ሲል ይገልጸዋል)፣ በዚህ ላይ በመነጋገር ከሌሎች ጋር ያለንን ግንኙነት ማበላሸቱ አስፈላጊ አይሆንም:: የማትስማሙባቸውን ነገሮች በጥንቃቄ ምረጡ:: ምናልባትም ክርክሩን አሸንፋችሁ በጦርነቱ ልትሸነፉ ትችላላችሁ!
2. ምሳሌ 11:12፣ 13:1: ከመናገራችሁ በፊት አስቡ:: ከዚያም የምትጠቀሙባቸውን ቃላት በጥንቃቄ ምረጡ:: «ድንጋዮችና ዱላዎች አጥንቶቼን ሊሰብሩ ይችላሉ:: ቃላት ግን ሊጎዱኝ አይችሉም» ያለው ግለሰብ የቃላትን ኃይል አልተገነዘበም:: መሣሪያ ሰውነትን እንደሚጎዳ ሁሉ ቃላትም የሰውን መንፈስ በፍጥነት ሊጎዱ ይችላሉ:: የምትጠቀሙባቸው ቃላት ሰዎችን እንዳያቆስሉ በጥንቃቄ አስባችሁ ምረጡ:: የሰዎችን መንፈስ ሳትጎዱ መልእክታችሁን ለማስተላለፍ ሞክሩ::
3. ምሳሌ 18:2፣ 12-13: ተቃውሟችሁን ከመግለጻችሁ በፊት ሁኔታውን በትክክል መረዳታችሁንና በቂ መረጃ እንዳላችሁ አረጋግጡ:: አንዳንድ ጊዜ መረጃውን በሙሉ ከእጃችን ሳናስገባ ዝም ብለን እንጮሃለን:: ራሳችንን በሌሎች ሰዎች ስፍራ በማስቀመጥ አመለካከታቸውን ለመረዳት መሞከር አለብን:: ረጋ ብሎ ማሰቡ ከብዙ ሥቃዮች ይጠብቀናል:: የአንድን ጉዳይ መረጃዎች ባለማወቃችን ወይም ባለመረዳታችን የኋላ ኋላ ከአፋችን ለወጡት መጥፎ ቃላት ይቅርታ ለመጠየቅ እንገደዳለን::
4. ምሳሌ 15:1፣ 12:18፣ 25:11-12: በተቃውሟችሁ ሰላምንና ፈውስን የማምጣት ዓላማ ይኑራችሁ:: ተቃውሟችን ወይም አለመስማማታችን ምሬትና ብቀላና ከተሞላ ልብ የሚፈልቅ ከሆነ፣ ቃሎቻችን ይህንኑ አመለካከት ማንጸባረቃቸው የማይቀር ነው:: ግደዳችን ለእውነተኛ ፈውስ፣ ዕድገት ወይም እርማት ከሆነ፣ ቃሎቻችን ይህንኑ አመለካከት ማንጸባረቅ አለባቸው:: በቁጣ የተሰነዘሩ ቃላት የሚፈጽሙት መልካም ሰናይ ተግባር አይኖርም:: ነገር ግን በፍቅር አስገዳጅነት የምንናገራቸው የጨዋነት ቃላት ከፍተኛ ለውጥ ያስከትላሉ:: ይህ መርህ ለማኅረሰብ ማኅበራዊ ጉዳዮችም ይሠራል:: (ለመሪው፣ ከመግባባት መንፈስ ይልቅ በጉልበት የሚካሄድ የተቃውሞ

እርምጃ ውጤት ያሳመጣበትን አጋጣሚ በምሳሌነት አብራራላቸው::)

5. ምሳሌ 17:14፣ 17:19: የተከራካሪነትን መንፈስ አታዳብሩ:: ራሳቸውን ጥሩ ክርክር ለማካሄድ እንደተፈጠሩ አድርገው የሚቆጥሩ ሰዎች አሉ:: በሁሉም ነገር ላይ ጸብ ለመጫርና ሙግት ለመግጠም ይፈልጋሉ:: እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት አደገኛ ወጥመድ ነው! ከዚህ የማያቋርጥ ክርክር በስተጀርባ ጽልመታዊ አመለካከት እየጎለበተ ይሄዳል:: እግዚአብሔር የጠራን አስታራቂዎች፣ ተስፈኞችና በዓለም ውስጥ የሚገኙትን ሕመሞች እንድንፈውስ ነው:: የተከራካሪነት መንፈስ ይህንን እንዳናደርግ ሊያደናቅፈን ይችላል::
6. ያዕቆብ 1:19-22: ተግባራትን ከክርክር ኋላ ለማስከተል ፈቃደኛ ሁኑ:: ለውጥለማምጣት የበኩላችንን አስተዋጽኦ የማናበረክት ከሆነ፣ ዝም ብሎ መተቸቱ ብቻ በቂ አይሆንም:: ሁኔታውን ለመለወጥ የምንችለውን ሁሉ ለማድረግ ካልፈቀድን በቤት ውስጥ ስላለው ሁኔታ ማማረሩ ዋጋ የለውም:: ለትምህርት ቤቱ መሻሻል ኃላፊነታችንን የማንወጣ ከሆነ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ስላለው ሁኔታ ማማረሩ ውጤት አያመጣም:: ግንኙነቱን ለመፈወስ የመጀመሪያውን እርምጃ የማንወስድ ከሆነ፣ ስለ ጓደኞቻችን የባሕርይ ችግር መከራከሩ በቂ አይደለም:: በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ንግግር ብቻውን ውጤት አያመጣም:: ንግግራችንን ከአዎንታዊ ግንባታ ላይ ለማዋል መፍቀድ አለብን::

ረ. የመወያያ ጥያቄዎች

1. እነዚህ ጥቅሶች ብዋናሊ ለችግሩ መፍትሔ እንዲያመጣ እንዴት ይረዱታል?
2. ከነዚህ መርሆች መካከል፣ ከአለመስማማቶቻችሁ ላይ ለማዋል ከሁሉም በላይ የሚቀለው የትኛው ነው?
3. ከሁሉም በላይ የሚከብደውስ?
4. በትምህርት ቤታችሁ፣ በቤታችሁና በማኅበረሰባችሁ ስለ ጠቃሚ ጉዳዮች ለመከራከር እነዚህን መርሆች እንዴት ልትጠቀሙ ትችላላችሁ?

ሰ. መዝጊያ

አለመስማማቶችን ማስወገድ አይቻልም:: ሁላችንም ስለ አንዳንድ ጉዳዮች የየራሳችን የሆኑ አመለካከቶች አሉን:: በዓለም ውስጥ ጥላቻና አድመኛነት እስካሉ ድረስ፣ ሁልጊዜም ክርስቲያኖች የማይቀበሏቸው ነገሮች ይኖራሉ:: ነገር ግን ለመፍትሔው እንጂ ለችግሩ መባባስ አስተዋጽኦ እንዳናበረክት አለመስማማቶቻችንና ተቃውሞዎቻችንን በመልካም መንፈስ መካሄዳቸውን በጥንቃቄ ማረጋገጥ አለብን::

ተማሪዎቹ አለመስማማትን ወይም አለመቀበልን ያስከትላል ብለው የሚያስቡትን ሁኔታ እንዲያስቡ ጠይቃቸው:: በነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ መርሆች ላይ ተመሥርተው እንዴት ለአለመስማማቶቹ ምላሽ እንደሚሰጡ በዓይነሕሊናቸው እንዲያስቡ ጠይቃቸው:: የማሰቡን ሂደት ለማገዝ ዓይኖቻቸውን እንዲጨፍኑ ልትነግራቸው ትችላለህ:: የሚከተሉትን መርሆች ያስታውሷቸው ዘንድ ያልተስማሙትን ሰው ወይም ስፍራ ስም በወረቀት ላይ በመጻፍ በኪሳቸው ወይም በመጽሐፍ ውስጥ እንዲይዙ ልትጠይቃቸው ትችላለህ::

1. ጉዳዩ ለክርክር የሚበቃ መሆኑን አረጋግጡ::
2. ከመናገራችሁ በፊት አስቡ:: የምትጠቀሙባቸውን ቃላት በጥንቃቄ ምረጡ::
3. ተቃውሟችሁን ከመግለጻችሁ በፊት ሁኔታውን በትክክል መረዳታችሁንና በቂ መረጃ እንዳላችሁ አረጋግጡ::
4. በተቃውሟችሁ ሰላምንና ፈውስን የማምጣት ዓላማ ይኑራችሁ::
5. የተከራካሪነትን መንፈስ አታዳብሩ::
6. ተግባራትን ከክርክር ኋላ ለማስከተል ፈቃደኛ ሁኑ::

አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ አዎንታዊና ገንቢ በሆነ መንገድ አቋም ለመያዝ እንድትችሉ እግዚአብሔር ብርታትንና ቆራጥነትን እንዲሰጣችሁ ጸልያችሁ ፈጽሙ::